# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ረቡዕ | 81ኛ ዓመት ቁጥር 201 መጋቢት 21 ቀን 2014 ዓ.ም ዋጋ 10.00 | ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!







# ጠቅላላ ጉባዔ ያላካሄዱ ፓርቲዎች በአጭር ጊዜ ውስጥ እንዲያካሂዱ ቦርዱ አሳሰበ

- ለፓርቲዎች የሚደረገው የ50 ሚሊዮን ብር የድጋፍ ቀመር ወጥቷል

**አዲሱ ገረመው**



ፎቶ በኅይ አስፋቸው

አዲስ አበባ፡- ጠቅላላ ጉባዔ ያላካሄዱ የፖለቲካ ፓርቲዎች በአጭር ጊዜ ውስጥ እንዲያካሂዱ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ አሳሰበ። ለፓርቲዎች የሚደረገው የ50 ሚሊዮን ብር ድጋፍ ቀመርም ወጥቷል።

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ከፖለቲካ ፓርቲዎች ጋር በተለያዩ አጀንዳዎች ዙሪያ ትናንት በመከረበት ወቅት እስካሁን ጠቅላላ ጉባዔ ያላካሄዱ ፓርቲዎች በጥቂት ጊዜ ውስጥ እንዲያካሂዱ እና መተዳደሪያ ደንባቸውን እንዲያሻሽሉ የቦርዱ ሰብሳቢ ብርቱካን ሚደቅሳ አሳስበዋል።

26 የፖለቲካ ፓርቲዎች ጠቅላላ ጉባዔ ማድረግ እንዳለባቸው ቦርዱ በደብዳቤ አሳውቋል። እስካሁን ባለው ሁኔታ ጠቅላላ ጉባዔያቸውን ያላካሄዱ መኖራቸውን የቦርዱ ሰብሳቢ ጠቁመዋል። ጉባዔ ያላካሄዱ የፖለቲካ ፓርቲዎች በአጭር ጊዜ ውስጥ አካሂደው ሪፖርት ማድረግ እንዳለባቸውም አሳስበዋል።

መተዳደሪያ ደንባቸውን እንዲያሻሽሉ የተሰጠው ደብዳቤ አፈጻጸም ላይ በሚገባ ተፈጻሚ እየሆነ አይደለም ያሉት ሰብሳቢዋ፤ ጠቅላላ ጉባዔ ያላደረጉ ፓርቲዎች ከሕጉም ሆነ ከመመሪያው አንጻር መተዳደሪያ ደንብ በሚያሻሽሉበት ጊዜ ከሕጉ ጋር ሳይጣረስ መፈጸሙንም ማየት እንዳለባቸው ገልጸዋል። በዚህ ጉዳይ ላይ ወደ ፊት ሰፊ ውይይት እንደሚኖርም ጠቁመዋል።

ፓርቲዎች በሚያደርጉት የጠቅላላ ጉባዔ ላይ የቦርዱ ታዛቢዎች ሁሉንም ሂደት መያዝ እንዲችሉ ተገቢውን ትብብር ማድረግ እንዳለባቸውም አመላክተዋል። በዚህ ረገድ ከአሁን ቀደም ጠቅላላ ጉባዔ ያካሄዱ አንዳንድ ፓርቲዎች ትብብር አለማድረጋቸውን ጠቅሰዋል።

የበጀት ድጋፍን በተመለከተ ቦርዱ ለተጨማሪ በጀት 230 ሚሊዮን ብር ከመንግሥት ለማግኘት ጥያቄ አቅርቦ እንደነበር የጠቀሱት የቦርዱ ሰብሳቢ፤ ነገር ግን አገሪቷ ካለችበት ሁኔታ አንጻር ይህ ገንዘብ እንደማይፈቀድ ምላሽ እንደተሰጠው አንስተዋል።

መንግሥት ለምርጫው የወረቀት ህትመት ከሰጠው

"ጠቅላላ ጉባዔ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል







# የብረት ዋጋ፡-

- በሳምንት ውስጥ የሦስት መቶ ብር ጭማሪ አሳይቷል
- በተወሰኑ አከፋፋዮች እጅ በመውደቁ ዋጋው የሚተመነው በጥቂት ግለሰቦች ነው
- የአየር በአየር ላይ ንግድና የደረሰኝ ግብይት ችግር መኖሩን መንግሥት ያምናል

**ሞገስ ጸጋዬ**



አዲስ አበባ፡- የፌሮ ብረት ዋጋ በየቀኑ ጭማሪ እያሳየ መምጣቱ እንዳሳሰባቸው በአዲስ አበባ በመገናኛና ሳሪስ አካባቢ ያነጋገርናቸው የብረት ሻጮች አስታወቁ።

መገናኛ አካባቢ ከሚገኙ ብረት ሻጭዎች መካከል የድርጅታቸው ስም እንዳይገለጽ የፈለጉት ወይዘሮ መዓዛ ወርቁ (ስማቸው የተቀየረ) እንደገለጹት፣ የፌሮ ብረት ዋጋ በየቀኑና በየሰዓቱ ይጨምራል። ከዋጋ መጨመሩ የተነሳ ደንበኞች ዋጋውን በመፍራት መግዛት አቁመዋል።

እንደ መዓዛ ገለጻ፤ የፌሮ ብረት አከፋፋዮች በማን አለብኝነት የውጭ ምንዛሬ ጨምሯል፣ ነፃ ገበያ ነው በማለትና ምክንያት የሌላቸውን ሃሳቦች በማንሳት ደስ ባላቸው ዋጋ ይሸጣሉ። ሆኖም ችግሩን ለመንግሥትና ለሚዲያ እንኳን ለመግለጽ የአከፋፋዮቹን ተጽዕኖ እንደሚፈሩ ይናገራሉ።

ከዚህ በፊት ለአንድ የመገናኛ ብዙኃን ጣቢያ የፌሮ አከፋፋዮችን አሻጥር የገለጹት ነጋዴ ብረት እንዳያገኙ በማድረግ ከገበያው እንዲወጡ ተደርገው በአማላጅ ወደ ሥራው መመለሳቸውን አስረድተውናል።

ቤተልሔም ሙሉጌታ (ስማቸው የተቀየረ) የተባሉ የፌሮ ብረት ሻጭ በበኩላቸው ብዙ የምናገረው ቢኖረኝም መናገር አልፈልግም ካሉ በኋላ ስማቸው እንዲቀየር፣ ፎቶግራፋቸውን እንዳንጠቀምና የድርጅታቸው ስም እንዳይጠቀስ ተስማምተን ሀሳባቸውን እንደሚከተለው አካፍለውናል።

‹‹ከሦስት አመት በፊት 75 ብር ከአንድ ወር በፊት ደግሞ 200 ብር ይሸጥ የነበረው ባለ ስምንት ተብሎ የሚጠራው የፌሮ ብረት አሁን ላይ 500 ብር ገብቷል። ቀደም ሲል በቀን ውስጥ ከ3 በላይ ደንበኞችን አስተናግድ ነበር። የብረቱ ዋጋ በየዕለቱ መጨመር ከጀመረ ወዲህ በ15 ቀን ውስጥ አንድ ደንበኛ ብቻ ነው ማስተናገድ የቻልኩት። አሁን ባለው ሁኔታ የሚቀጥል ከሆነ ከሥራው ልወጣ እችላለሁ›› የሚል ስጋታቸውን አጋርተውናል።

የፌሮ ዋጋ በየጊዜው የሚጨምረው ከፋብሪካው ነው የሚሉት መረጃ ሰጪችን፤ ጠዋት ገዝተን ዕቃውን ለማስጫን ስንሄድ ጨምሯል፤ ብር ጨምሩ እንባላለን። እንዲሁም በውድ ዋጋ ከገዛን በኋላ ዕቃውን ወደ ገበያ ስናወጣ ከፍተኛ የሆነ ቅናሽ በማድረግ ኪሳራ ውስጥ እንድንገባ እንደረጋለን፤ እንዲሁም ከከፈልን በኋላ ዕቃ አልቋል በማለት እንጉላላለን ብለዋል።

ለምን ይህ ይሆናል ብለን ስንጠይቅ ‹‹ነፃ ገበያ ነው፤

"የብረት ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል






## በሕወሓት ታጣቂዎች ምክንያት የዕርዳታ እህል ወደ ትግራይ ክልል ማድረስ አለመቻሉ ተገለጸ

ገጽ 4

## ‹‹የአገራዊ ምክክሩ መስፈርቶች በትክክል ተሟልተው ከተተገበሩ ለፖለቲካ ልዩነቶቻችን መፍትሄ ይሰጣል››

ዶክተር ሰሚር የሱፍ
በደህንነት ጥናት ተቋም ውስጥ ከፍተኛ ተመራማሪ

ገጽ 4







# ባለስልጣኑ በምዘና ከፍተኛ ውጤት ላስመዘገቡ 377 መምህራንና የትምህርት ቤት አመራሮች እውቅና ሰጠ

**ሞገስ ተስፋ**



አዲስ አበባ፡- በተሰጠው ምዘና ከፍተኛ ውጤት ላስመዘገቡ 377 መምህራንና የትምህርት ቤት አመራሮች አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርትና ስልጠና ቁጥጥር ባለስልጣን እውቅና ሰጠ።

የመምህራንና የትምህርት ቤት አመራሮች የምዘና ውጤት በዘርፉ ብዙ ሥራ መሠራት እንዳለበት ያመላከተ መሆኑ ተገለጸ።

«የመምህራንና የትምህርት ቤት አመራሮች ብቃት ለትምህርት ጥራት» በሚል መሪ ቃል የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የትምህርትና ስልጠና ጥራት ቁጥጥር ባለስልጣን ትናንት የመምህራንና የትምህርት አመራሮች የሙያ ብቃት ምዘና ይፋ ያደረገ ሲሆን ከፍተኛ ውጤት ላስመዘገቡት እውቅና ሰጥቷል።

በተዘጋጀው የእውቅና መርሃግብር ላይ የባለስልጣኑ ዋና ሥራ አስኪያጅ ወይዘሮ ሕይወት ጉግሳ እንደገለጹት፤ ጥራት ያለው ትምህርት ለመስጠት ጥራት ያለው መምህርና የትምህርት ቤት አመራር ያስፈልጋል። ስለዚህ ውጤታማ የሆነ የትምህርት ጥራት ለማምጣት መምህራንና አመራሮች ራሳቸውን ብቁ ያደረጉ ሊሆኑ ይገባል።

ከ2004 ዓ.ም እስከ 2014 ዓ.ም ድረስ ባለስልጣኑ ባካሄደው የመምህራንና የትምህርት አመራሮች ምዘና ባጠቃላይ ከ17 ሺህ 849 መምህራንን እንዲሁም 712 የትምህርት አመራሮችን መዝኗል።

በርካታ መምህራንና የትምህርት ቤት አመራሮች ለመመዘን በተደረገ የተከታታይ ዓመታት የሥራ እንቅስቃሴ የተመዛኞች ፍላጎት እያደገ የመጣና ለውጥ እየታየ ስለመሆኑ ሥራ አስኪያጇ ጠቁመዋል።

እንደ ሥራ አስኪያጇ ገለጻ፤ ከተመዘኑት ከ17 ሺህ 849 መምህራንን ውስጥ አምስት ሺህ 913 (33) በመቶ ሚሆኑት በጽሑፍ ምዘና ከ62.5 በመቶ በላይ የማለፊያ ውጤት አምጥተዋል። የጽሑፍ ምዘና ከተመዘኑት ውስጥ አራት ሺ 534 (22) በመቶ የሚሆኑት መምህራን የሙያ ብቃት ማረጋገጫ ማግኘት ችለዋል። ከምዘና ውጤቱ አንጻር ብዙ ሥራ መሠራት አለበት። ለዚህም አንዱ በመምህራንና በትምህርት ቤት አመራሮች በኩል የሚሠራ ነው። የትምህርት ሥራ አንዴ ተምሬ ዲግሪዬን ይዣለሁ ተብሎ የሚቆም አይደለም፡ በተጨማሪም ጥራት የሁሉም ባለድርሻ አካል የተሳትፎ ውጤት ነው።

የልማት ሥራው የሚሠራው የትምህርት ቢሮ ለመምህራን በልዩ ትኩረት መደገፍ መቻል አለበት ያሉት ወይዘሮ ሕይወት፤ የታዩ ክፍተቶችን ማዕከል በማድረግ ሊሠራ ይገባል ብለዋል።

ከ2004 እስከ 2014 ድረስ ባለስልጣኑ ባካሄደው የመምህራንና የትምህርት አመራሮች ምዘና ባጠቃላይ ከ 17 ሺህ 849 መምህራንን እንዲሁም 712 የትምህርት አመራሮችን የማህደርና ተግባር ምዘና መስጠት መቻሉን የባለስልጣኑ የመምህራንና የሙያ ፈቃድ አሰጣጥ እድሳት ቡድን መሪ አቶ ሰንደቁ ያዛቸው ውጤቱን ይፋ ባደረጉበት ወቅት ገልጸዋል።

እንደ አቶ ሰንደቁ ገልጻ፤ ከአጠቃላይ የግልና የመንግሥት ተመዛኝ የአዲስ አበባ መምህራን ውስጥ 25 በመቶው ምዘናውን አልፈው የብቃት ማረጋገጫ ሰርተፍኬት ተሰጥቷቸዋል።

ከአጠቃላይ በከተማ አስተዳደሩ ካሉ የግልና የመንግሥት ትምህርት ቤት አንድ መቶ 90 ወይም 27 በመቶ የሚሆኑት አመራሮች ምዘናውን አልፈዋል።

# የደምቢ ዶሎ ዩኒቨርሲቲ በአገራዊ ምክክሩ ዙሪያ የምሁራን መድረክ እንደሚያዘጋጅ ገለጸ

**ገመቹ ከድር**

አዲስ አበባ፡- በአገራዊ ምክክር ጉዳይ ላይ ሁሉንም አካላት ግንዛቤ ሊያስጨብጥ የሚያስችል የምሁራን ምክክር መድረክ በቅርቡ እንደሚያዘጋጅ የደምቢ ዶሎ ዩኒቨርሲቲ አስታወቀ።

የዩኒቨርሲቲው ፕሬዚዳንት ዶክተር ለታ ተስፋዬ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ዩኒቨርሲቲው በአገር አቀፍ ደረጃ በሚካሄደው አገራዊ ምክክር ዙሪያ ለሁሉም አካላት ግንዛቤ ሊያስጨብጥ የሚያስችል የምሁራን መድረክ ለማዘጋጀት እየሠራ ነው።

መድረኩ ምሁራን ካላቸው ዕውቀት በመነሳት የአገራዊ ምክክሩን ፋይዳ ኅብረተሰቡ እንዲገነዘበው ማድረግ ያለመ መሆኑን አመልክተው፤ ምሁራን በአገራዊ ምክክሩ አስፈላጊነት መተማመን ከፈጠሩ እነሱ ያመኑበትን ጉዳይ ለሌሎች ለማስረዳትና አገራዊ ምክክር ያማከሉ ጥናቶችን በማካሄድ ጠቃሚ ሐሳቦችን በማመንጨት ለአገራዊ ምክክሩ ስኬታማነት የድርሻቸውን እንዲጫወቱ የሚያስችል መሆኑን አብራርተዋል።

ከምሁራኑ መድረክም ኅብረተሰቡም የአገራዊ ምክክር ምንነትንና አስፈላጊነት በመረዳት በባለቤትነት ስሜት እንዲሳተፍ ያደርጋል ያሉት ዶክተር ለታ፤ አገራዊ ምክክሩ በምሁራን ምክክር መታገዙ ሕዝቡ የሚያነሳቸውን ጥያቄዎች ዘላቂ መፍትሄ ለማበጀት ጉልህ ሚና እንደሚኖረው አስገንዝበዋል።

ዩኒቨርሲቲው አገራዊ ምክክሩን ስኬታማ ለማድረግ ካለው ሀብት ድጋፍ ለማድረግ ዝግጁ መሆኑን የገለጹት ዶክተር ለታ፤ ከሁሉም በላይ ምሁራንና ሚዲያዎች በገለልተኝነት ሙያዊ ግዴታቸውን መወጣት አገራዊ ምክክሩን የበለጠ ውጤታማ እንደሚያደርግ ገልጸዋል።

ምሁራንና ሚዲያዎች አገራዊ ምክክሩን ሊያደናቅፉ ከሚያስችሉ ድርጊቶች በመታቀብና በመጠንቀቅ ገለልተኛ ሆነው መዘገብ እንዳለባቸው አሳስበዋል።

እንደ አገር የጋራ ችግሮችን በምክክር ለመፍታት መስማማት በራሱ መልካም ጅማሮ ነው ያሉት ዶክተር ለታ፤ አገራዊ ምክክሩ የአገር ችግሮችን እንደሚፈታ እምነታቸው መሆኑን ገልጸዋል።




# ተቋርጦ የቆየው የጤና መድህን አገልግሎት ወደ መደበኛ ሥራው መመለሱ ተገለጸ



**አስናቀ ፀጋዬ**

አዲስ አበባ፡- አሸባሪው የሕወሓት ቡድን ባደረሰው ውድመትና ዘረፋ ምክንያት ተቋርጦ የቆየው የማኅበረሰብ ጤና መድህን አገልግሎትን በመልሶ ግንባታ ወደ መደበኛ ተግባር መመለሱን በሸዋሮቢት ከተማ አስተዳደር የቀወት ወረዳ ጤና ጽሕፈት ቤት አስታወቀ።

በሸዋሮቢት ከተማ አስተዳደር የቀወት ወረዳ ጤና ጥበቃ ጽሕፈት ቤት ኃላፊ አቶ ሰይድ ሀሰን ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለፁት፤ አሸባሪው የሕወሓት ቡድን በሸዋሮቢት ጤና አጠባበቅ ጣቢያ ላይ ባደረሰው ውድመትና ዝርፊያ የማኅበረሰብ አቀፍ ጤና መድህን አገልግሎቱ ለተወሰነ ጊዜ ተቋርጦ ቆይቷል። በማኅበረሰቡና በወረዳ አመራሩ ተሳትፎ እንዲሁም በዞንና በሚመለከታቸው አካላት ድጋፍ የማኅበረሰብ አቀፍ ጤና መድህን አገልግሎቱ በአሁኑ ጊዜ ወደ መደበኛ ተግባሩ ተመልሷል።

ጽሕፈት ቤቱ የማኅበረሰብ አቀፍ ጤና መድህን አገልግሎትን በ2006 ዓ.ም በሙከራ ደረጃ ካስጀመረ ወዲህ 15 ሺ 149 አባወራዎችን ተጠቃሚ ማድረግ መቻሉን አመልክተው፤ በዘንድሮ በጀት ዓመትም ሁለት ሺ 480 አዳዲስ አባላትን ለማፍራት እቅድ ይዞ ቢንቀሳቀስም አሸባሪው የሕወሓት ቡድን በሸዋሮቢት ጤና አጠባበቅ ጣቢያ ላይ ባደረሰው ውድመትና ዝርፊያ የማኅበረሰብ አቀፍ ጤና መድህን አገልግሎቱ ለተወሰነ ጊዜ ተቋርጦ ቢቆይም በተደረገው ርብርብ አገልግሎቱ መጀመሩን ተናግረዋል።

ጽሕፈት ቤቱ በዘንድሮው በጀት ዓመት 13 ሺ 40 አባወራዎችን የጤና መድህን አባል ለማድረግ ማቀዱን ጠቁመው፤ እስካሁን ባለው ሂደትም የእቅዱን 95 ነጥብ 9 ከመቶ ወይም 12 ሺ 518 አባወራዎችን አባል ማድረጉንም አስታውቀዋል።

ጽሕፈት ቤቱ 17 ሺ 629 አባወራዎችን አባል አድርጎ የማኅበረሰብ አቀፍ ጤና መድህን አገልግሎት እንዲያገኙ ለማድረግ አቅዶ 84 ነጥብ 1 ከመቶ ያህሉን ወይም 14 ሺ 841 አባራዎችን የአገልግሎቱ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ማድረጉንም አያይዘው ጠቁመዋል።

በጤና መድህን አገልግሎት አሰጣጥ መርሆችና እሴቶች ላይ ከማኅበረሰቡ ጋር በተለይ ደግሞ ከአርሶ አደሩ ጋር መግባባት በመቻሉና በጦርነት ውስጥም ሆኖ ለመስራት በሥነልቦና ዝግጁነት በመኖሩ አገልግሎቱ ወደ መደበኛ ተግባር እንዲመለስና ውጤት እንዲገኝ አስተዋፅኦ ማድረጉንም ኃላፊው አመልክተዋል።

# ሕዝቡ ለግድቡ የሚያደርገውን ድጋፍ ግንባታው እስኪጠናቀቅ ድረስ አጠናክሮ እንዲቀጥል ጥሪ ቀረበ

ዳግማዊት ግርማ



አዲስ አበባ፡- ሕዝቡ ለታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ግንባታ እያደረገ ያለውን ድጋፍ ግንባታው እስኪጠናቀቅ ድረስ አጠናክሮ መቀጠል እንዳለበት ጥሪ ቀረበ። ባለፉት 11 ዓመታት ለግድቡ ግንባታ ከሕዝቡ 16 ነጥብ 4 ቢሊዮን ብር ድጋፍ መሰብሰቡ ተገልጿል።

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ገዢ ዶክተር ይናገር ደሴ የታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ አገር አቀፍ የቦንድ ሽያጭ ሳምንት ትናንት ይፋ ሲደረግ እንደገለጹት፤ የኢትዮጵያ ሕዝብ ላለፉት አስራ አንድ አመታት ለግድቡ እያደረገ ያለውን ድጋፍ ግንባታው እስኪጠናቀቅ ድረስ አጠናክሮ ሊቀጥል ይገባል።

የታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ አገር አቀፍ የቦንድ ሽያጭ ሳምንት ንቅናቄ ዋና አላማ ሕዝቡ ከዚህ ቀደም በቦንድ ግዢ፣ በልገሳና በተለያየ መልኩ ለግድቡ ግንባታ እያደረገ ያለውን ድጋፍ አጠናክሮ እንዲቀጥል ለማስቻል እንደሆነ የጠቆሙት ዶክተር ይናገር፤ ሕዝቡ ለህዳሴው ግድብ ግንባታ እያደረገ ያለውን ድጋፍ አሁንም አጠናክሮ እንዲቀጥል ጥሪያቸውን በማቅረብ ንቅናቄውን አስጀምረዋል።

የታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ማስተባበሪያ ጽሕፈት ቤት ምክትል ዋና ዳይሬክተር አቶ ታገል ቀኑብህ በበኩላቸው አርሶ አደሩና አርብቶ አደሩ እስካሁን ድረስ ለታላቁ ህዳሴው ግድብ ግንባታ በጉልበት ያበረከቱት አስተዋጽኦ በገንዘብ ቢተመን ከ100 ቢሊዮን ብር በላይ እንደሚሆን ገልጸዋል።

አቶ ታገል አርሶ አደሩና አርብቶ አደሩ በገንዘብ ከመደገፍ በተጨማሪ ጉልበታቸው በየዓመቱ የተፋሰስ ሥራዎችን በማከናወን ለግድቡ የበኩላቸውን አስተዋጽኦ ማድረጋቸውን ገልጸዋል።

ባለፉት 11 ዓመታት ለግድቡ ግንባታ ከሕዝቡ 16 ነጥብ 4 ቢሊዮን ብር ድጋፍ መሰብሰቡን ገልጸው፤ በተለያዩ ሙያ መስኮች የተሰማሩ ግለሰቦችና ሲቪክ ማህበራት በሙያቸውና በዕውቀታቸው ለግድቡ ግንባታ የበኩላቸውን ድጋፍ ማድረጋቸውንም አቶ ታገል ተናግረዋል።

ዛሬ ላይ የታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ግንባታ አፈጻጸም 84 በመቶ የደረሰውና 375 ሜጋዋት ኃይል ማመንጨት የጀመረው ሁላችንም ኢትዮጵያውያን ከጫፍ ጫፍ ተነስተን በገንዘባችን፣ በጉልበታችንና በዕውቀታችን ድጋፍ በማድረጋችን ነው ያሉት አቶ ታገል፤ ድጋፉ አሁንም ግንባታው እስኪጠናቀቅ ድረስ ተጠናክሮ መቀጠል እንደሚኖርበት አመልክተዋል።

መላው ኢትዮጵያውያንና ዳያስፖራው ከገንዘብ ድጋፉ ባሻገርም በፐብሊክ ዴፕሎማሲው ረገድም በገንዘብ ሊተመን የማይችል ድጋፍ ማድረጋቸውን አመልክተው፤ ይህ ድጋፍም ተጠናክሮ ሊቀጥል እንደሚገባ አስታውቀዋል።

'ግድባችን የአንድነታችን ብርሀን' በሚል መሪ ቃል የግድቡ ግንባታ 11ኛ ዓመትና የመጀመሪያ ምዕራፍ ኃይል ማመንጨቱን ተከትሎ አገር አቀፍ የቦንድ ሽያጭ ሳምንት ይፋ ተደርጓል። የቦንድ ሽያጭ ሳምንቱ ከመጋቢት 20 እስከ ሚያዝያ 5 ቀን 2014 ዓ.ም የሚቆይ ይሆናል። የኢትዮጵያ ልማት ባንክና የታላቁ ህዳሴ ግድብ ማስተባበሪያ ጽሕፈት ቤት በጋራ ያዘጋጁት አገር አቀፍ የቦንድ ግዥ ሳምንት መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ለግድቡ ግንባታ እስኪጠናቀቅ ድረስ የሚጠበቅበትን ድጋፍ አጠናክሮ እንዲቀጥል የሚያስችል የንቅናቄ መድረክ መሆኑ ተገልጿል።

# የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል ምክር ቤት የብሔረሰብ ስያሜው «ቤኒሻንጉል» እንዲሆን ወሰነ



አዲስ አበባ፡- የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል ምክር ቤት ከዚህ ቀደም በርታ ተብሎ ሲጠራ የነበረውን የብሔረሰብ መጠሪያ «ቤኒሻንጉል» ተብሎ እንዲሰየም የቀረበለትን የብሔረሰብ መጠሪያ በሙሉ ድምጽ አጸደቀ።

የብሔረሰቡን ስያሜ በተመለከተ የብሔረሰብ ምክር ቤቱ ቀደም ሲል በኩርሙክ ወረዳ ባካሄደው ጉባዔ የብሔረሰቡን ታሪክ መሠረት ባደረገ መልኩ «ቤኒሻንጉል» ተብሎ እንዲጠራ የቀረበውን መጠሪያ ማጽደቁ የሚታወስ ነው።

በትናንትናው ዕለት የብሔረሰብ መጠሪያው «ቤኒሻንጉል ብሔረሰብ» ተብሎ እንዲጸድቅ ለክልሉ ምክር ቤት የቀረበ ሲሆን፣ ምክር ቤቱ ውይይት ካደረገ በኋላ በሙሉ ድምጽ አጽድቆታል።

በተመሳሳይ ምክር ቤቱ የክልሉን ያልተማከለ የወረዳ አካባቢ አስተዳደርን ለማጠናከር የቀረበውን የማሻሻያ አዋጅ በመመርመር የአሶሳ ወረዳ በሁለት ወረዳዎች እንዲዋቀር አጽድቋል።

ወረዳው ካለው የቆዳ፣ የቀበሌ እና የሕዝብ ብዛት፣ የአስተዳደር ምቹነት፣ ለሕዝቡ የመልካም አስተዳደር ችግሮች በወቅቱ ምላሽ ለመስጠት፣ የአገልግሎት አሰጣጥ ምቹነት አኳያ በመወያየት ወረዳው በሁለት ወረዳዎች እንዲዋቀር የቀረበው የማሻሻያ አዋጅ በሙሉ ድምጽ ጸድቋል።

በማሻሻያ አዋጁም አሶሳ ወረዳ የሚለው ቀርቶ «ኡራ ወረዳ» እና «አብርሃሞ ወረዳ» ተብሎ በሁለት ወረዳዎች የተዋቀረ ሲሆን፣ በዚህም ለሕዝብ አስተዳደር በሚመች መልኩ ኡራ ወረዳ 41 እንዲሁም አብርሃሞ ወረዳ ደግሞ 41 ቀበሌዎችን እንዲኖሯቸው በማድረግ መደራጀታቸውን ከክልሉ ኮሙኒኬሽን ጉዳዮች ቢሮ ያገኘነው መረጃ ያመለክታል።

ምክር ቤቱ የ2014 ዓ.ም የግማሽ ዓመት አፈጻጸም ሪፖርትን እና የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል ሚሊሻ ጽ/ቤትን እንደገና ለማቋቋም የወጣው አዋጅ ላይ ተወያይቶ በማጽደቅ 13ኛ መደበኛ ጉባዔውን አጠናቋል።

# የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ከውጭ ባንኮች ጋር መወዳደር የሚያስችለውን ዝግጅት እያደረገ መሆኑን ገለጸ

**ፋንታነሽ ክንዴ**



አዲስ አበባ፡- የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ መንግሥት ዘርፉን ለውጭ ባንኮች እንደሚከፍት መግለጹን ተከትሎ ዘርፉን ሊቀላቀሉ ከሚችሉ የውጭ ባንኮች ጋር መወዳደር የሚያስችለውን ዝግጅት እያከናወነ መሆኑን አስታወቀ።

የባንኩ ብራንች ኤንድ ሪቴር ባንኪንግ ምክትል ፕሬዚዳንት አቶ ፍቅረሥላሴ ዘውዱ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ባንኩ አገልግሎቱን ቀልጣፋና በቴክኖሎጂ የታገዘ ለማድረግ በትኩረት እየሠራ ነው። የባንኩ ዘርፍ ለውጭ ባንኮች ክፍት እንደሚደረግ መገለጹን ተከትሎ እነዚህ ባንኮች ወደ ሥራ ሲገቡ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ አሁን ያለውን ተወዳዳሪነትና ቀዳሚነት አስጠብቆ ለመዝለቅ የሚያስችል ዝግጅት እያደረገ ነው ብለዋል።

ባንኩ እስካሁን ድረስ በየጊዜው አሠራሩን እያዘመነ ቀዳሚነቱን አስጠብቆ እየተጓዘ ነው ያሉት ምክትል ፕሬዚዳንቱ፤ ለቀዳሚነቱም በየጊዜው በከፍተኛ ደረጃ እየጨመረ ያለው የባንኩ ደንበኞችና ነባር ደንበኞች በታማኝነት መቀጠላቸውን በማሳያነት አንስተዋል።

በቀጣይነትም ባንኩ በሁሉም መስክ ያለውን መሪነት አስጠብቆ ለመዝለቅ እየሠራን ነው ያሉት አቶ ፍቅረሥላሴ፤ ለዚህም ትልቁን ሚና የሚጫወተው ቴክኖሎጂን ማሳደግ መሆኑን በማመን ለቴክኖሎጂ ልማት ትኩረት ሰጥቶ እየሠራ ነው። በቀጣይነትም የሚጨምራቸው በቴክኖሎጂ የታገዙ አገልግሎቶች ይኖራሉ ብለዋል።

የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የቁጠባ ሒሳብ በየጊዜው በከፍተኛ ሁኔታ እያደገ መምጣቱን ጠቁመው፤ ይህም የባንኩን የፋይናንስ አቅም በማጠናከር ለተወዳዳሪነቱ ትልቅ ሚና የሚጫወት መሆኑን አስረድተዋል።

ከደንበኞች የሚሰበሰቡ ግብረ መልሶች ባንኩ የሚሰጣቸው አገልግሎቶች በየጊዜው እየተሻሻሉ መሄዳቸውን የሚያመላክት ነው ያሉት አቶ ፍቅረሥላሴ፤ ይህ ማለት ግን ባንኩ ችግሮች የሉበትም ማለት ስላልሆነ በተለያዩ መንገዶች ከደንበኞች የሚያገኛቸውን ግብረ መልሶች እንደ ግብአት በመጠቀም አገልግሎት አሰጣጡን እያሳደገ እንደሚሄድ ጠቁመዋል።

ባንኩ ከብሔራዊ ባንክ በመጣ መመሪያ መሠረት የደንበኞችን መረጃ በአዲስ መልክ እያደራጀ መሆኑን ጠቅሰው፤ ይህም ደንበኞች ማንነታቸው በአግባቡ እንዲታወቅ ስለሚያደርግ አገልግሎት ለማግኘት ወደ ባንኩ ቅርንጫፎች በሚመጡበት ጊዜም ሆነ የባንኩን የዲጅታል አገልግሎቶች ሲጠቀሙ ያለምንም ገደብ አገልግሎትን ማግኘት እንደሚያስችላቸው ጠቁመዋል።

ከተለያዩ የመንግሥት አካላት ለሚመጡት ጥያቄዎችም ባንኩ ደንበኛው የሚታወቅና ሕጋዊ ሥራ የሚሠራ መሆኑን መረጃዎችን መስጠት ስለሚያስችል ለደንበኞች መልካም አጋጣሚ መሆኑን አውቀው መረጃዎቻቸውን በወቅቱ ሊያሟሉ ይገባል ብለዋል።

በተለያዩ ምክንያቶች ለውጭ ባንኮች ዝግ ሆኖ የቆየው የባንክ ዘርፍ እንደሚከፈት በመጠቆም፤ የአገር ውስጥ ባንኮች ራሳቸውን ከእነዚህ ባንኮች ሊገጥማቸው የሚችለውን ከፍ ያለ ውድድር አሸንፈው ለመውጣት መዘጋጀት እንዳለባቸው በመንግሥት በኩል መገለጹ ይታወሳል።



# ‹‹የአገራዊ ምክክሩ መስፈርቶች በትክክል ተሟልተው ከተተገበሩ ለፖለቲካ ልዩነቶቻችን መፍትሄ ይሰጣል››

**ዶክተር ሰሚር የሱፍ**
**በደህንነት ጥናት ተቋም ውስጥ ከፍተኛ ተመራማሪ**

**ሞገስ ጸጋዬ**

አዲስ አበባ፡- የአገራዊ ምክክሩ መስፈርቶች በትክክል ተሟልተው ከተተገበሩ በትንሹ ለፖለቲካ ልዩነቶቻችንን መፍትሄ ይሰጣል ሲሉ በደህንነት ጥናት ተቋም ውስጥ ከፍተኛ ተመራማሪው ዶክተር ሰሚር የሱፍ አስታወቁ።

በትናንትናው ዕለት ‹‹የብሔራዊ ውይይት ፅንሰ-ሀሳብ እና ተግባራዊነት በኢትዮጵያ›› በሚል ርዕስ የደህንነት ጥናት ተቋምና በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የኢትዮጵያ ጥናት ኢንስቲትዩት በጋራ በመተባበር ኮንፈረንስ አካሂደዋል። በደህንነት ጥናት ተቋም ውስጥ የፖለቲካል ሳይንስ ተመራማሪው ዶክተር ሰሚር የሱፍ እንገለጹት፤ የአገራዊ ምክክሩ መስፈርቶች በትክክል ከተተገበሩ የቆዩ የኢትዮጵያን ችግሮች መፍታት ይቻላል።

አገራዊ ምክክሩ ብዙ ችግሮችን የመፍታት አቅም አለው ያሉት ምሁሩ፤ አቅሙን ወደ ትክክለኛ ብቃት መቀየርም የራሱ የሆነ ሂደት ያስፈልጋል።አገራዊ ምክክሩ መስፈርቶቹ በትክክል ተሟልተው ከተተገበሩ በትንሹ የምንለያይባቸውን የፖለቲካ ልዩነቶች መፍትሄ ይሰጣል ብለዋል።

የምንከራከርባቸው ጉዳዮች ጊዜ ሊወስዱ ስለሚችሉ በአንድና በሁለት ዓመት መፍትሄ ይሰጣል ባይባልም፤ ቢያንስ ቢያንስ ውጥንቅጡ ከወጣ የፖለቲካ አውድ አውጥቶ የምንወያይበትን አውድ፣ ተቋማትንና ባህልን ያበለጽግልናል ያሉት ዶክተር ሰሚር፤ ይህን መሰል ባህል ካዳበረልን ትልቅ የሆኑ አገራዊ ችግሮችን ለመፍታት መንገዱ ቀላል እንደሚሆን ገልጸዋል።

አገራዊ ምክክሩ የተረጋጋ የፖለቲካ ሥርዓት መፍጠርና ያልተፈቱ የፖለቲካ ልዩነቶቻችንን ለመፍታት የሚያስችል መደበኛ ሥራዎች ሂደቶችና ተቋማትን ይዘረጋሉ ብለዋል።

ኢትዮጵያ በተለምዶ ያለችው ታዳጊ በሚባለው ዓለም ውስጥ ነው ያሉት ተመራማሪው፤ የበለጸጉ አገራት የዲሞክራሲ ባህል አላቸው፤ እኛ የለንም፤ እነሱ ኢኮኖሚያቸው አድጓል፤ የእኛ አላደገም በማለት እኛ ኢትዮጵያውያን ያሉብንን ችግሮች ከበለጸጉ አገሮች ጋር የማዛመድና የመተንተን አዝማሚያዎች አሉ።ነገር ግን ኢትዮጵያ በእነሱ መንገድ የመሄድ ዕድሉ የላትም።ሌላው ዓለም ያልተጠቀመበት ኢትዮጵያ አሁን ልትጠቀምበት የምትችለው አዲስ ዕድል መፍጠር ያስፈልጋል ብለዋል።

በአገራዊ ምክክር አማካኝነት አዲስ ዕድሎችን መክፈትና ለማህበረሰባዊና ፖለቲካዊ ለውጥ እንዲውል አድርገን መቅረጽና መተግበር እንደሚያስፈልግ አመልክተው፤ አገራዊ ምክክሩ ከታላቅነቱና ከአላማው አስፈላጊነት አንጻር መቃኘት እንደሚኖርበት አስገንዝበዋል።

እንደ ተመራማሪው ገለጻ፤ የአገራዊ ምክክር መድረኮች በተለያዩ አገሮች ተካሂደዋል፤ ውጤት እንዲያገኙ ያደረጋቸው አገራዊ ምክክሩን የሚያካሂደው አካል ቅቡልነት ነው።አገራዊ ምክክር አድርገው ያልተሳኩላቸው አገሮች ብሔራዊ ምክክሩን የሚያስኬደው አካል ከኅብረተሰቡና ከምሁራን ቅቡልነት በማጣቱ ነው።

ኢትዮጵያም የተሳኩና ያልተሳኩ አገራዊ ምክክሮችን በመቃኘት ሰከን ብሎ ማሰብና መሄድ እንደሚያስፈልግ ገልጸው፤ የተቋቋመው ኮሚሽን አገራዊ ችግሮችን ለመፍታት በርካታ ተስፋዎችን አጭሯል፤ የተሰጠውን አጀንዳ እንዲያሳካም መንግሥትና የሚመለከታቸው አካላት ኮሚሽኑን በሚገባው ልክ መደገፍ እንዳለባቸው አሳስበዋል።

# በሕወሓት ታጣቂዎች ምክንያት የዕርዳታ እህል ወደ ትግራይ ክልል ማድረስ አለመቻሉ ተገለጸ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- የአብኣላ የርዕዳታ ማቅረቢያ መንገድ በሕወሓት ታጣቂዎች በመዘጋቱ ምክንያት የዕርዳታ እህል ወደ ትግራይ ክልል ማድረስ አለመቻሉን የመንግሥት ኮሙኒኬሽን አገልግሎት አስታወቀ።

የመንግሥት ኮሙኒኬሽን አገልግሎት የኢትዮጵያ መንግሥት የሰብአዊ ርዕዳታ አቅርቦት አሁናዊ ሁኔታን በተመለከተ ትናንት ባወጣው መግለጫ እንዳስታወቀው፤መንግሥት የሰብአዊ ድጋፍ አቅርቦቱን ተደራሽነት ለማስፋት በዓለም የምግብ ድርጅት በኩል 43 የከባድ መኪና ጭነት የዕርዳታ እህል በየብስ ትራንስፖርት በትግራይ ክልል የሰብአዊ ዕርዳታ ለሚያስፈልጋቸው ዜጎች በአብኣላ መንገድ በኩል እንዲቀርብ ተፈቅዷል። ይሁን እንጂ በአሁኑ ሰዓት የአብኣላ የርዕዳታ ማቅረቢያ መንገድ በሕወሓት ታጣቂዎች በመዘጋቱ ምክንያት የዕርዳታ እህል ወደ ትግራይ ክልል ማድረስ አልተቻለም። በአሁኑ ጊዜም 20 የጭነት መኪናዎችም የዕርዳታ እህሉን እንደጫኑ በአፋር ክልል በሠመራ ከተማ ቆመው ይገኛሉ ብሏል በመግለጫው።

የኢትዮጵያ መንግሥት በትግራይ ክልል ያሉ ዜጎችን ለመታደግ ሁሉንም አማራጮች በመጠቀም ርዳታውን ለማቅረብ እንቅስቃሴ ውስጥ የገባ ቢሆንም የሌላኛውን ወገን ቅን ትብብር ማግኘት አልቻለም ያለው መግለጫው፤ የዓለም የምግብ ድርጅት እንዲያጓጉዝ የተፈቀደው 43 የጭነት መኪና

በኢፌዴሪ የመንግሥት ኮሙኒኬሽን አገልግሎት
FDRE Government Communication Service

የዕርዳታ እህል ለተረጂዎች መድረስ አልቻለም። የዚህም ዋናው ምክንያት የአብኣላ የዕርዳታ ማቅረቢያ መንገድ በሕወሓት ታጣቂዎች በመዘጋቱ፣ ዕርዳታው በየብስ ትራንስፖርት ወደ ትግራይ ክልል ሊጓጓዝ አልቻለም ብሏል።

የኢትዮጵያ መንግሥት በትግራይ ክልል ሰብአዊ ድጋፍ ለሚያስፈልጋቸው ዜጎች የሰብአዊ ድጋፍ አቅርቦቱን ለማሳለጥና በከፍተኛ ችግር ውስጥ የሚገኙ ዜጎችን ለመታደግ ለሰብአዊነት ሲባል ግጭት መቆሙን ማስታወቁ የሚታወስ መሆኑን መግለጫው አመልክቶ፤ ውሳኔው ከተወሰነበት ቀን አንስቶ የኢትዮጵያ መንግሥት በርካታ ርምጃዎችን እየወሰደ ይገኛል። በሳምንት ሁለት ጊዜ ይደረግ የነበረውን የአየር በረራ በየቀኑ እንዲደረግ ለተለያዩ ዓለም አቀፍ የሰብአዊ ዕርዳታ አቅራቢ ተቋማት ፍቃድ መስጠቱን አስገንዝቧል።

በዚህም መሠረትም የመድኃኒት፣ የሕክምና መሣሪያዎች፣ ገንዘብና አልሚ ምግቦችን ረጂ ድርጅቶች በቻሉት መጠን በአየር ትራንስፖርት መጓጓዝ ጀምረዋል። ሌሎች በአየር ትራንስፖርት ሊጓጓዙ የሚችሉ የሰብአዊ ድጋፎችን እንዲያጓጉዙም የኢትዮጵያ መንግሥት ፈቃድ ሰጥቷል።ከዚህ አኳያ በረጂ ድርጅቶች አቅም ማነስ ወይም በራሳቸው አሠራር ሥርዓት የመዘግየት ሁኔታ ካልገጠመ በቀር በመንግሥት በኩል ፈጣን ርምጃ መውሰዱን መግለጫው አስታውቋል።

የኢትዮጵያ መንግሥት የሰብአዊ ርዳታ ለሚያስፈልጋቸው ዜጎች የሰብአዊ ድጋፍ አቅርቦቱን በተሟላ ሁኔታ ለማስኬድ ከተባባሪ እና ባለድርሻ አካላት ጋር ለመሥራት ዛሬም ቁርጠኛ መሆኑን በድጋሚ ያሳውቃል ያለው መግለጫው፤ የትግራይ ታጣቂዎች ልዩ ልዩ ምክንያቶች ከመደርደርና የተዛቡ መረጃዎችን ከማሠራጨት ተቆጥበው የዕርዳታ እህሉ አቅርቦት እንዲሳለጥ የበኩላቸውን ድርሻ እንዲወጡ መንግሥት ያሳስባል ብሏል።

እንዲሁም የዕርዳታ አቅርቦት ከሚተላለፍባቸውና በጉልበት ከያዟቸው የአፋርና የአማራ ክልል ወረዳዎች በመውጣት ግጭት ለማቆም የገቡትን ቃል እንዲያከብሩ የዓለም አቀፍ ተቋማት በትግራይ ታጣቂዎች ላይ ጫና እንዲያደርጉ መንግሥት ጥሪ ማቅረቡን መግለጫው ገልጾ፤ የኢትዮጵያ መንግሥት በትግራይ ክልል ውስጥ በአስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ ያሉ ዜጎችን ሕይወት ለመታደግ የትኛውንም አማራጭ በመጠቀም የዕርዳታ አቅርቦቱ እንዲሳለጥና ዜጎች በተረጋጋ ሁኔታ ኑሮአቸውን እንዲመሩ የሚመለከታቸው አካላት ሁሉ ቀና ተባባሪ ይሆናሉ ብሎ ተስፋ ያደርጋል ሲል የመንግሥት ኮሙኒኬሽን አገልግሎት መግለጫ አስታውቋል።

# «በክልሉ የዞን መዋቅር ሲዘገይ የቻለው ሕዝብን ለሚጠቅሙ የልማት ሥራዎች ቅድሚያ ስለተሰጠ ነው»

**- አቶ አብርሃም ማርሻሎ**
**የሲዳማ ክልል ብልጽግና ፓርቲ ጽሕፈት ቤት ኃላፊ**

**አምሳሉ ፈለቀ**



አዲስ አበባ፡- የሲዳማ ክልል ከተዋቀረ ወዲህ የዞን መዋቅርና አደረጃጀት ለማድረግ ቢታሰብም እስካሁን ሊዘገይ የቻለው ሕዝብን ለሚጠቅሙ የልማት ሥራዎች ቅድሚያ በመስጠት እንጂ የሕዝቡ ጥያቄ ምላሽ ላለመስጠት ተፈልጎ አይደለም ሲሉ የክልሉ ብልጽግና ፓርቲ ጽሕፈት ቤት ኃላፊ አቶ አብርሃም ማርሻሎ ገለጹ።

አቶ አብርሃም ማርሻሎ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ከክልል አደረጃጀት ቀጥሎ ለዞን መዋቅር ተብሎ 150 ሚሊዮን ብር በጀት ቢያዝም ሕዝቡ በተያዘው በጀት መንገድ፣ ውሃ፣ መብራት እንዲሁም የተለያዩ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ፋይዳ ያላቸው ፕሮጀክቶች እንዲሠራለት ይፈልጋል። የዞን መዋቅርና አደረጃጀት እስካሁን ሊዘገይ የቻለውም ሕዝብን ለሚጠቅሙ የልማት ሥራዎች ቅድሚያ በመስጠት እንጂ የሕዝቡን ጥያቄ ምላሽ ላለመስጠት ተፈልጎ አይደለም ብለዋል።

ከዞን አደረጃጀት ይልቅ ቅድሚያ ሊሠጠው የሚገባ ጉዳይ የሕዝባችን አንገብጋቢ የልማት ሥራዎች ናቸው ያሉት አቶ አብርሃም፤ የክልሉ በጀትም ከዚህ ቀደም በዞን መዋቅር ደረጃ ይበጀትለት በነበረው ልክ እንጂ ለሲዳማ ክልል በተለየ ቀመር የተሰጠ ተጨማሪ በጀት እንደሌለም ተናግረዋል።

አሁንም የዞን መዋቅር በጀት ተይዞ እስካሁን ለምን ዘገየ? የሚሉ ጥያቄዎች ከየአቅጣጫው ቢነሱም ሊዘገይ የቻለው የሕዝብን አንገብጋቢ ጥያቄዎች ለማስቀደም ሲባል መሆኑንም አስታውቀዋል።

በክልሉ ስር ዞኖች ቢደራጁም ወረዳዎችን የሚያስተባብሩና የተወሰነ ሰው ተወክሎ የሚሠሩበት እንጂ ብዙ የሰው ኃይል የሚቀጠርበት መዋቅር እንደማይኖራቸው አስረድተዋል።

ለሕዝቡ መሠረታዊና አንገብጋቢ ጉዳዮች ቅድሚያ በመስጠት በጀቱን ከመዋቅር ይልቅ ለሰፊው ሕዝብ ተጠቃሚነት እንዲውል ታስቦ የዞን አደረጃጀቱ እንዲዘገይ መደረጉንም አቶ አብርሃም አስገንዝበዋል።

በሲዳማ ክልል ስር የሚገኙ ወረዳዎችም ከሐዋሳ ብዙ ርቀት የሌላቸው በመሆኑ ሕዝባችን በክልሉ ውስጥ በየትኛውም አካባቢ ተገቢውን አገልግሎትና ፍትሕ የሚያገኝበት አግባብ መኖሩን ጠቁመው፤ ከማዕከሉ ሐዋሳ- ጭሬ፤ ከሎካ -አባያና አሮሬሳ ድረስ ብዙም የሚርቅ ባለመሆኑ ሕዝቡ አገልግሎቱን ሳይንገላታ በቀላሉ ማግኘት ይችላል። ለዚህም የክልሉ መንግሥት አስፈላጊውን ጥረት ያደርጋል ብለዋል።

«ዞኖች ቢደራጁ የሥራ አጦች ቁጥር ይቀንሳል» የሚል አስተሳሰብና ጥያቄ ከሕዝቡ እንደሚነሳ ያብራሩት አቶ አብርሃም፤ የሥራ አጥነት፣ የኢኮኖሚ፣ የማኅበራዊና የመልካም አስተዳደር ችግሮች በዞን መዋቅር ሊፈቱ እንደማይችሉና ቅድሚያ ሊሰጣቸው ለሚገቡ ጉዳዮች ቅድሚያ እየተሰጠ ጥያቄዎች በሂደት ምላሽ እንዲያገኙ ይደረጋልም ብለዋል።

የሲዳማ ሕዝብ ከዚህ ቀደም ለረጅም ዓመታት ራስን በራስ ለማስተዳደር ሲታገል መቆየቱንና በለውጡ መንግሥት ራስን የማስተዳደር መብቱን መጎናጸፉን የገለጹት ኃላፊው፤ ክልሉን በዞን ለማዋቀር እንደከዚህ ቀደሙ የሚገዳደረን አካል ስለማይኖር የያዝነውን የለውጥ ጉዞ ከግብ ለማድረስ አንገብጋቢ የሕዝብ ጥያቄዎችን እየመለስን እንሄዳለን ሲሉ የክልሉ ብልጽግና ፓርቲ ጽሕፈት ቤት ኃላፊና የፓርቲው ማዕከላዊ ኮሚቴ አባል አቶ አብርሃም ገልጸዋል።

## የብረት...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

ካዋጣችሁ መግዛት ካልሆነ መተው ትችላላችሁ » የሚል መልስ እንደሚመለስላቸው ያስረዳሉ። በአንድ ቀን ውስጥ ሦስትና ከዚያ በላይ ዓይነት ዋጋ ሊለዋወጥ እንደሚችልም ይገልጻሉ። ያለን አማራጭ አከፋፋዮች እንዳሉን መሆንና በኪሳራም መስራት ነው ብለዋል።

በገዛንበት ብር መጠን ልክ ደረሰኝ አይቆርጡልንም ያሉት ቤተልሄም፤ የአንድ ፌሮ ብረት ዋጋን የገዛንበት ገንዘብ እያለ ባልገዛንበት ብር ደረሰኝ ይጻፍልናል። በዘርፉ ያለው አደገኛ ሰንሰለት ከአከፋፋዮች ጋር የተያያዘ በመሆኑ መንግሥት ሊያስብበት ይገባል ብለዋል።

ሳሪስ ካሉ በአንዱ ፌሮ ብረት መሸጫ ሱቅ ውስጥ የሚሠራው አቶ ወሰንሰገድ አለሙ በበኩሉ የፌሮ ብረት ገበያው በአገራችን ሰላም ከደፈረሰበት ጊዜ ጀምሮ ዋጋው በየቀኑ ሲለዋወጥ ይታያል። ዋጋው በየቀኑ የሚጨምር በመሆኑ የአንድ ብረት ዋጋን ለመናገር ይከብዳል፤ ገዥም እንደበፊቱ የለም። በዘርፍ ያሉ የችርቻሮ ነጋዴዎችም ዘግተው እየወጡ ነው። ብረት አምራቾች የውጭ ምንዛሬ ጨመረ፣ ጥሬ ዕቃ ጠፋና ነፃ ገበያ ነው በማለት በፈለጉት ዋጋ ነው የሚሸጡት ሲሉ ይገልጻሉ።

በንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር የንግድና ዕቃዎች ዋጋ ጥናት ክትትልና ቁጥጥር ዳይሬክተር ወይዘሮ መስከረም ባህሩ የብረት ውድነትን በተመለከተ የአስተያየት ሰጪዎቻችንን ሀሳብ ይጋራሉ። የተወሰነ ጥናት አካሂደናል፤ ከደረሰኝ ግብይት ጋር በተገናኘ ችግሮች ስላሉ ከገቢዎችና ከፖሊስ ጋር በመሆን ተጨማሪ ጥናት ለማካሄድ አቅጣጫ ማስቀመጣቸውን ገልጸዋል።

የተወሰነ ናሙና ወስደን ባካሄድነው ጥናት መሠረት የብረት ግብይት ላይ ችግሮች እንዳሉና በየጊዜው የዋጋ ጭማሪ እንዳለው ተገንዝበናል ያሉት ዳይሬክተሯ፣ እንዲሁም የአየር በአየር ላይ ንግድና የደረሰኝ ግብይት ላይ ችግር እንዳለው ማየት ችለናል ብለዋል።

## ጠቅሳሳ ጉባዔ...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

ብር ተመላሽ የሆነውን ለፖለቲካ ፓርቲዎች ድጋፍ እንዲደረግ ቦርዱ ያስፈቀደ ሲሆን፤ በዚህም ወደ 50ሚሊዮን ብር ገዳማ በእኩልነትና ፓርቲዎች በሰጡት መረጃ እንዲሁም ከቦርዱ የተገኙ ሰነዶችን ታሳቢ በማድረግ ክፍፍል እንደሚፈጸም ገልጸዋል።

በአጠቃላይ ከሚመደበው በጀት 30 በመቶ ለአገራዊ ፓርቲዎች፤ 20 በመቶ ለክልላዊ ፓርቲዎች፤ ሌሎች ደግሞ ከሴት አባላት ብዛትና በሴት አመራር አባላት ብዛት እንዲሁም በአካል ጉዳተኛ አመራርና አባላት ብዛት በሚል ነጥብ የሚሰጥ እንደሆነ አመላክተዋል።

ከድልድሉ ጋር በተያያዘ አንዳንድ ፓርቲዎች ቅሬታ ያቀረቡ ሲሆን አሠራሩ ሕግን ተከትሎ የተፈጸመ ስለመሆኑ ሰብሳቢዋ አስረድተዋል።

በመድረኩ ቦርዱ ፓርቲዎች ያቀረቡትን አቤቱታዎች መነሻ አድርጎ «ችግር ተፈጥሯል» በተባለባቸው አካባቢዎች በመንቀሳቀስ ምርመራ አድርጎ ተገቢው ሕጋዊ መፍትሄ እንዲሰጥ ማድረጉን በሪፖርት አቅርቧል። ከዚህ ጋር ተያይዞ ቦርድ እየከፈለ ያለው ዋጋ እውቅና ሊሰጠው እንደሚገባ የፖለቲካ ፓርቲ ተወካዮች ተናግረዋል።

በውይይቱ የተሳተፉት የፖለቲካ ፓርቲዎች አባላቶቻቸው ላይ እንግልት እየተፈጸመ ስለመሆኑ፤ እንደልብ መንቀሳቀስ እንዳልቻሉና ሌሎች አሉታዊ ተጽእኖዎች እየደረሱባቸው እንዳለ የገለጹ ሲሆን፤ ቦርዱ ዝርዝር መረጃው ቀርቦለት አቤቱታቸውን መነሻ አድርጎ በቀጣይ የማጣራት ሥራውን እንደሚያከናውን ተገልጿል።

ከዚህ ቀደም ፓርቲዎች ያገኟቸውን የገንዘብ ድጋፍ በትክክል ስለመጠቀማቸው የሚያሳይ የኦዲት ሪፖርት ካልቀረበ የዘንድሮ የገንዘብ ድጋፍ ገቢ መሆን እንደማይችልም ነው ሰብሳቢዋ የጠቆሙት።

# ርዕሰ አንቀፅ

## ከኅብረተሰቡ የተነሱ ችግሮች ፈጣን መፍትሄን ይሻሉ!

ገዢው የብልግጽና ፓርቲ በአገር አቀፍ ደረጃ ከኅብረተሰቡ ጋር ባደረገው የውይይት መድረኮች በርካታ ችግሮች ተነስተዋል። ኅብረተሰቡ ለነገዬ ብሎ ሳይሰስት፣ ምን ይመጣብኝ ይሆን ብሎ ሳይፈራና ሳይሸማቀቅ የተሰማውን ቅሬታ ሁሉ በየመድረኩ በግልጽ አቅርቧል። በፓርቲውና በመንግሥት ትኩረት ይሻሉ፣ ፈጣን ምላሽ ሊሰጣቸው ይገባል ያላቸውን ጉዳዮች ሁሉ በነፃነት አንስቷል፡፡ ፈጣን ምላሽ ማግኘት እንደሚፈልግም አጽንኦት ሰጥቶ አሳስቧል።

በርግጥ ከኅብረተሰቡ የሚነሱ አስተያየቶችና ቅሬታዎች እንደየአካባቢው ነባራዊ ሁኔታ የተለያዩና ሰፊ ቢሆንም አብዛኞቹ ግን ተመሳሳይነት ያላቸው ናቸው። በተለይም ከኑሮ ውድነት፣ ከሰላምና ጸጥታ፣ ከአገልግሎት አሰጣጥ፣ ከፍትህዊ ተጠቃሚነት ወዘተ ከመሳሰሉት ጋር ተያይዞ የተነሱት ናቸው።

ገዢው ፓርቲም ሆነ መንግሥት የተነሱትን ችግሮች በየደረጃው በመለየት መፍትሄ ለመስጠት እየሠራ እንደሚሆን ገልጿል። የተለዩ ችግሮችንም እንደ ፓርቲ ፈተናዎቼ ነበሩ፤ አሁንም ፈተና ሆነው ቀጥለዋል ብሎም አስቀድሞ ለይቷል። እነዚህን ፈተናዎች ለማለፍም ጠንክሮ እንደሚሠራ ሕዝብም በዚሁ ጉዞ ተሳታፊና ተባባሪ እንዲሆን ጭምር ጥሪ አድርጓል።

እንደችግር የተነሱትን ጉዳዮች መሠረታዊ መንስኤያቸውን በመለየት ችግሮችን ከስር መሠረታቸው ለመፍታት የሚያስችል አቅጣጫ የሚከተል መሆኑን አስታውቋል። ይሄ ጥሩ ነው፤ እንደ መንግሥትም መሥራት የሚገባው ዋነኛው ጉዳይ ነው። ይሁን እንጂ በተለይ አንዳንድ መሠረታዊ የሆኑ ጉዳዮች ጊዜ የሚሰጣቸው፣ በይደር የሚቆዩ አይደሉም።

ለምሳሌ ያህል ከኑሮ ውድነት ጋር የተያያዙት ጊዜ የሚሰጣቸው አይደሉም። የተለየ ፖሊሲና ስትራቴጂዎችን አይፈልጉምም። በአገራችን ጥሩ ጥሩ የሆኑ ፖሊሲዎች አሉ። ጥሩ ጥሩ የሆኑ መመሪያዎችና ሕጎችም አሉ። ዋናው ችግር ግን ባሉን መመሪያዎች፣ ሕጎች እና ደንቦች መሠረት መሥራትና ማስፈጸም አለመቻል ነው።

ኃላፊነትና ግዴታን በተገቢው መልኩ መወጣት አለመቻል ነው። ባሉን መመሪያዎችና ሕጎች መሠረት እርምጃዎች አለመወሰዳቸው ነው። ይሄ ደግሞ ሕዝቡን ለበዝባዦች ሲሳይና የደላሎች መጫወቻ እንዲሆን ዳርጎታል። ስለዚህ ሕዝቡን ከገጠመው አስከፊ የኑሮ ጫና ለመገላገል በጣም ፈጣን፣ ግልጽ የሆነ አሠራር ዘርግቶ ወደ መፍትሄ እርምጃ መግባት ያስፈልጋል።

አሁን ባለው ሁኔታ ሸቅብ የወጣው የሸቀጦች ዋጋ ይወርዳል ተብሎ ሲጠበቅ ሕጋዊነቱን ባረጋገጠ መልኩ ባለበት ቆሞ ይቸበቸባል። ዘይት ሲባል ሲሚንቶ አሁን ደግሞ የብረት ዋጋ ሸቅብ እየሄደ ነው። ይሄ የሚሆነው በአሁኑ ወቅት ከውጭ ገብቶ ሳይሆን በአገራችን ተመርቶ ወይም በዓለም ላይ ምንም ዓይነት ችግር ሳያጋጥም በፊት አገር ውስጥ ገብቶ ተከማችቶ በየቆየው ላይ ነው።

ለዚህ ሁሉ የዋጋ መናር ታዲያ ተዋንያን መኖራቸው የአደባባይ ሀቅ ነው። ደላላ አንዱ ዋጋ ተማኝ፣ መመሪያ ሰጪና አከፋፋይ ነው። በእያንዳንዱ ጉዳይ ቀድሞ መረጃ በመልቀቅ ተገቢውን ክትትልና እርምት ባለመውሰዱ የሚመለከታቸው የመንግሥት ሠራተኞችና አመራሮችም ዓይነተኛ ሚና አላቸው። ከዚህ ውጪም አንዳንድ ነጋዴዎች እርስ በእርሱ በመነጋገርና ባልተጻፈ ሰነድ በመስማማት ሴራዎችን በአገርና በሕዝብ ላይ ይፈጽማሉ። እንዳሻቸው ዋጋ ይቆልላሉ። ከፈለጉም ምርቱን ይደብቃሉ። ከአንዱ አካባቢ ወደሌላ ቦታ ይሰውራሉ።

ሌላው ከኅብረተሰቡ የተነሳው ጊዜ ሳይሰጠው ሊሠራ የሚገባው የመልካም አስተዳደር ጉዳይ ነው። ይሄንና ሌሎችንም ችግሮች ለመፍታት በእቅድ ተካቶ የሚሠራ መሆኑ ተገልጿል። በሕዝብ የተነሱ ጥያቄዎች በአግባቡ ይታያሉ፣ ይፈታሉ፣ መፍትሄ ያገኛሉ። መቼ፤ እንዴትና በማን እንደሚፈጸሙ በግልጽ ይቀመጣል፡፡ የአካሄድ አቅጣጫ በመቀመጡም ተግባራዊ ምላሽ ለመስጠት የሚያስችል ዝግጅት እየተደረገ መሆኑን መንግሥት አስታውቋል።

ሕዝቡ በተለይ አሁን ባለው የኑሮ ውድነት ተማሯል። የዕለት ጉርስን ማግኘቱ ፈትኖታል። በመሆኑም የኑሮ ውድነትም ሆነ ሌሎች ቅሬታ የፈጠሩበት ጉዳዮች ሕዝብን ባሳተፈ መልኩ ሁነኛ መፍትሄ ሊበጅላቸውና በተደራጀ መንገድ ደረጃ በደረጃ ሊፈቱ ይገባል!

አዲስ ዘመን
ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስኪያጅ
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

ዋና አዘጋጅ
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

አድራሻ
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4240
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች
- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- አልማዝ አያሌው
- እስማኤል አረቦ
- ዘላለም ግርማ

የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15

የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል
ስልክ ቁጥር - - 011-156-98-73
ፋክስ 011-126-58-12

የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ
ስልክ - 011-1-26-43-39
ማከፋፈያ
ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70

ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡ በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## መልስ አልባ ጥያቄዎች፤ አድማጭ አልባ ንግግሮች - እንዳኖሩን

**በየኔነው ስሻው**

የትዕግስትን ከፍታ በ«መታገስ ዋጋ አለው» ቃኝቶ የትዕግስቱን ጣፋጭ ፍሬ የሚያጣጥመው ኢትዮጵያዊ፤ ትዕግስቱ እንደ ሞኝነት፣ ጊዜ መስጠቱ እንደ ዝንጋኤ ሲቆጠርበት «ትዕግስትም ልክ አለው» ይሉትን ብሂልን ፈጥሮ የትዕግስቱን ልክ ማለፍ፣ የመከፋቱን ጫፍ መውጣት በዝምታ እንደማያልፍ ያስተምራል። ለእነዚህ ሁለት ብሂሎቹ «ለሁሉም ጊዜ አለው» ብሂሉ ላይ ተመስርቶ ሁሉንም በጊዜውና በቦታው አሳምሮ እየከወነ ዘመን ተሻግሯል፤ ታሪክ ሠርቶ፣ ወግ ባህሉን መስርቶ፣ ማህበራዊ ቁርኝቱን አጽንቶ በከፍታው ላይ ኖሯል።

ይሄንንም በማህበራዊ ጉድኝቱ ብቻ ሳይሆን እንደ ጅረት ተግተልትለው ላለፉት የመንግሥት አስተዳደር ሥርዓቶች ማቅኛነትም ተጠቅሞባቸዋል። ጥያቄዎቹን መዝነው፣ ንግግሮቹንም አድምጠው መልስ ሲሰጡት ሸልሞ ማንገስን፤ ጥያቄዎቹ ምላሽ፣ ንግግሮቹም አድማጭ የተነፈጉ መስሎ ሲሰማው አዋርዶ ማውረድን ተክኖበታል። በዚህ ሂደትም ጥያቄ ጠይቆና የሚሰማውን ተናግሮ «... ቃሌን ሰማኝ፣ ጩኸቴም በፊቱ ወደ ጆሮው ገባ፤ ... እንደ እጄ ንጽህና ይመልስልኛል» ብሎ ሲጠብቅ፤ ንግግሮቹ ያለ አድማጭ፣ ጥያቄዎችም ያለ ምላሽ የቀሩ መሆናቸውን ሲገነዘብ ለሁሉም የጊዜውን ፍርድ ሰጥቶ ሸኝቷል፤ አዳዲስ ባለፍርዶችን ተክቶም ለተራ ፍርድ ሰይሟል።

ለዚህ እንደ ማሳያ ሦስት ፈርጆችን እንጥቀስ፤ አንደኛው በንጉሣውያን ሥርዓት የሚገለጸው የአፄዎቹ አስተዳደር ነው። ይህ ወቅት ኢትዮጵያዊ (በሕዝብ የወል ስም ልጠቀመው) በባላባትና ጭሰኛ የዕዝ ሰንሰለት ውስጥ እንዲገባ የሆነበት ጊዜ ነበር። በዚህም ጭሰኛውና ባላባቱ በሲሶ ልኬት ላይ ተመስርተው በኑሮ ጅረታቸው ይፈስሱ ነበር። ይሁን እንጂ ይህ አልሆንልህ ያለው እና የጭሰኝነት ቀንበሩ ጫንቃውን ያዛለው ሰፊው ሕዝብ፤ ጭሰኝነት በቃኝ፣ እኔም እንደ በአላባቱ የመሬት ባለቤት ልሁን ሲል መሞገት ጀመረ።

እናም ሰፊው ሕዝብ ከዛሬ ነገ፣ ከዘንድሮ ለቀጣይ ዓመት ጥያቄዬ መልስ ያገኛል፤ ጩኸቴም ይደመጣል በሚል ተስፋ መጠበቅ ጀመረ። ይሁን እንጂ በጪሰኛው ጉልበትና ላብ ላይ የተመሠረተው ባላባታዊ ሥርዓቱ የጭሰኛው ንግግር በጆሮው ሊገባ፤ ጥያቄውንም ሊመልስ አልቻለም። ታግሶ መጠበቅ ዋጋ እንዳለው የተገነዘበው ሕዝብም፤ መታገሱ ዋጋ እንዳልተሰጠው ሲያውቅ የትዕግስቱ ልክ አለቀ። እናም የእንቢታው ጊዜ ደርሶ የባላባትነት ዘመን፤ የጭሰኝነት ጉዞ እንዲያበቃ ለማድረግ ተነሳ ጊዜው ነበርና የራሱን ጥያቄ በራሱ መለሰ። ጭሰኝነት ከባላባትነት ተቆራረጠ፤ የጌታና ሎሌ ጉዞ ተቋጨ፤ ሁሉም ባለርስት፣ ሁሉም ባለ ቤት ሆነ።

ወቅቱ አዲስ መንገድ፣ አዲስ ቅኝት ይዞ መጣ። ጭሰኝነትና ባላባትነት መቋጫ ሲያገኝ፤ ሶሻሊዝም ለመለመ። የሠራተኛው መደብ ቦታውን ተረከበ። በ«ኢትዮጵያ ትቅደም» ቅኝት ጉዞው የሰመረ መሰለ። ይሁን እንጂ እያደር ቅኝቱ መቀየር፤ ኢትዮጵያን ማስቀደሙ መፈተን ጀመረ። መሬትን ለባለመሬቱ ያደረገው የሕዝብ እንቢታ፤ በማንነት ካባ ለመሬት ንጥቂያ ተጋበዘ። የማንነት ነፃ አውጪዎች ባነሱት ነፍጥ ሕዝቡ መታመስ ጀመረ። አገር አቅኚና የማንነት ነፃ አውጪዎች ሕዝብን ተከልለው መፋተግ፣ መዋጋት፣ ማጋደልና መገዳደል መለያቸው ሆነ።

አብዮተኞችና ብሔረተኞች የሚለው ጎራ አገርን ለከፋ ጦርነት፤ ሕዝብን ለእልቂት እና ለዴሞክራሲ ጥማት ዳረጉት። በጉሮ ወሸባዬ የተተከለው የደርጋዊ ሥርዓት የመሣሪያ ላንቃን ማዘጋትም ሆነ የሕዝቡን እንግልት ማስቆም የተሳነው መሰለ። በውስጣዊም በውጫዊም ጫናው አገርና ሕዝብ ተፈተኑ፤ መፈተናቸው ደግሞ ለጥያቄ እንዲነሱ፤ ለተቃውሞ እንዲበረቱ አደረገ። ንግግራቸው በፀረ አብዮተኝነት፤ ጥያቄያቸው በአፈሙዝ ምላሽ ማግኘት ጀመረ። ይሄም ሕዝብ ሕልውናው በለጠበትና በቃኝ ብሎ ለብሔረተኞች በር ከፈተ። እናም አብዮታዊው ጉዞ ሲገታ፤ ብሔረተኛው ፌዴራሊዝም ተተከለ።

ብሔረተኛውን ፌዴራሊዝም የወለደው ሥርዓት በልማት፣ በዴሞክራሲና በሌላውም ስም ምሎ ለሕዝብ የሚሠራ መሆኑን ሲናገር፤ ሕዝብም ተቀበለው። መተባበርና አብሮት መስራት ጀመረ። ዓመት፣ ሁለት ዓመት፣ ... አምስት ዓመት፣ አስር ዓመት፣ ሃያ ዓመት፣... ቀን ቀንን፣ ወር ወርን፣ ዓመት ዓመትን እየተካ የአብሮነት ጉዞው ቀጠለ። ሆኖም ጊዜው በረዘመና ሥርዓቱ በተደላደለ ቁጥር መሃላው ተዘነጋ፤ የሕዝብ ፍላጎቶች ቸል ተባሉ፤ ከሕዝብ ይልቅ ለእኔና ለቡድኔ የሚል አመራርና የፖለቲካ ስሪት ተተከለ።

ይህ ደግሞ ሕዝብ ቆም ብሎ እንዲያስብ፤ በራሱ ድጋፍ ራሱን እየጨቆነና እያፈነ መሆኑን እንዲገነዘብ፤ እየሆነ ስላለው እንዲናገር፤ እንዲሆን ስለሚፈልገው እንዲጠይቅ አደረገው። ንግግሮቹ ሰሚ፤ ጥያቄዎቹም ምላሽ ያገኙ እንደሁ በሚልም በትዕግስት ጠበቀ። ሆኖም ንግግሩ ከአክራሪነት፣ ከጽንፈኝነት፣ ከትምክህተኝነት፣ ከጠባብነት፣ ወዘተ ፍረጃ የዘለለ ጆሮ ሰጥቶ ያደመጠው አልነበረም። ጥያቄዎቹም ለአስቸኳይ ጊዜ አዋጅና የኮማንድ ፖስት አፈና፤ እስርና እንግልት ዳረጉት እንጂ ጠብ የሚል ምላሽ አላስገኙለትም።

ይሄኔ ሕዝብ ቆም ብሎ ማሰብ ያዘ። በኢ_ፍትሃዊ የኢኮኖሚ ክፍፍል መጎዳቱ፤ የፖለቲካ እና የማህበራዊ በደል ውስጥ መግባቱ፤ በማንነት ስም የተሰጠው ቦታ፣ የተከለለለት መሬት እርስ በእርሱ እንዲገፋፋና እንዲገዳደል የተሰመረለት መሆኑን ተረዳ። እናም መገፋፋቱን ትቶ መሳሳብ፤ መጠራጠሩን ትቶ መመካከር፤ መገዳደሉን ትቶ መተባበር ያዘ። የራሱን ዕድል በራሱ ሊወስንም ከፋፍሎ እንዳይተባበር፣ የሃሰት ትርክት ፈጥሮ እንዳይደማመጥ፣ ባደረገው ሥርዓት ላይ ሆ ብሎ ተነሳ። በዚህም ታንኩንም ባንኩንም በእጁ ይዞ የማይናወጥ የመሰለው ሥርዓት ተነቅንቆ ተነቀለ፤ ሕዝብ በለውጥ ማዕበል ከፍ አለ።

የለውጡ ማዕበል ለውጥ ወልዶ፤ የኢህአዴጋዊው ሥርዓት ከእሳቤው ብልጽግና ተተካ። የመከፋፈል ጉዞው በሕብር ወዳጌጠ አንድነት፤ የመጠራጠር ስሪቱ ወደ መተማመን ውቅር፤ የመገፋፋት ኑረቱ ወደ መተባበር እንዲለወጥ ለማድረግ ሥራ ተጀመረ። ይሁን እንጂ የኢህአዴጋዊ ለውጡ ባህሪው ሪፎርም እንጂ አብዮት ባለመሆኑ ሰርጎ ገብ ቅሬቶች እና የተገፉትም ከውጭ ሆነው ሂደቱን መነቅነቅ ጀመሩ። ለውጡ በእንቅፋት፤ ሕዝብም በፈተና እንዲታጀብም አበክረው ሰሩ።

እነዚህ የተገፉ የመሰላቸው ኃይሎች በውስጥም በውጭም ሆነው የፈጠሩት ቅንጅት እና ከቀደመው ተጠቃሚ የነበሩ አካላት ጥቅማቸውን ለማስጠበቅ ሲሉ በሚያደርጉላቸው እገዛ ታጅበው የሚፈጥሩት ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ፖለቲካዊ ችግር ቀላል አልነበረም። ኢኮኖሚው በአንድ ሰንሰለት የተያዘ እንደመሆኑ የኢኮኖሚው አሻጥር ገነገነ፤ የደህንነት መዋቅሩ በአንድ ኃይል ቁጥጥር ስር ስለነበር ይሄን ማላቀቁ ጦር እስከመማዘዝ ደርሶ ብዙ ዋጋ አስከፈለ፤ ማህበራዊ ትስስሩ ቀድሞ እንዲላላ ተደርጎ ስለነበር ሕዝቦች ብዙ ዋጋ እንዲከፍሉ አደረገ።

እናም ሰላምና ፀጥታው ከፍቶ የደህንነት ስጋትን ወለደ፤ የኢኮኖሚ ሳቦታጁ ማረፊያ ያጣ የዋጋ ንረትና የኑሮ ውድነትን ተከለ፤ ማህበራዊ ስሪቱም አለመተማመንና መገፋፋትን መገለጫው ያደረገ መሰለ። የእነዚህ ድምር ውጤት ደግሞ ሕዝብ አብዝቶ እንዲጮህ፤ አብዝቶም መፍትሄ እንዲያገኙ እንዲጠይቅ አደረገው። ሆኖም ጩኸቶቹም ሆኑ ጥያቄዎቹ ዛሬም ድረስ ከመድረክ ምላሽ የዘለለ ተጨባጭ ነገር ያሳዩት አይመስሉም። ይህ ደግሞ ሕዝብ እንደ ሕዝብ ተናግሮ ሰሚ የማጣትን፤ ጠይቆ ምላሽ የመነፈግን ስሜት የሚፈጥር ሊሆን እንደሚችል እሙን ነው። ሕዝብ ደግሞ መልስ አልባ ጥያቄዎች፤ አድማጭ አልባ ንግግሮች እንዲኖሩት አይፈልግም። በመሆኑም «ሳይቃጠል በቅጠል» ነውና የሕዝብ ንግግሮች ሊደመጡ፤ ጥያቄዎቹም ሊመለሱ ይገባል።

ፖለቲካና ወቅታዊ

# ተጠየቅ

# «በጥራት እና በፍጥነት ውጤታማ ሆኖ አገልግሎት አለመስጠት ያስጠይቃል»

*አቶ መሐመድ ሰዒድ*
*በፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን*
*የመንግስት አገልግሎት አሰጣጥ ዳይሬክተር ጀነራል*

ምሕረት ሞገስ

ሰሞኑን ከመራጭ ሕዝብ ጋር እየተካሔዱ ባሉ ውይይቶች ላይ ከሚነሱ ጥያቄዎች መካከል በዋናነት በአገልግሎት አሰጣጥ ላይ ያለ ሌብነት፣ ለውጡን የሚመጥን የሕዝብን ፍላጎት ማዕከል ያደረገ አገልግሎት እየተሰጠ አለመሆኑን የሚያመለክቱ እና የመንግሥት ሠራተኛው በኑሮ ውድነት እየተሰቃየ እንደሚገኝ የሚያመለክቱ ናቸው። በእነዚህ ጉዳዮች ላይ ቢሯችን ድረስ የፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን ምን ይላል? በማለት ጠይቁልን መባሉን ተከትሎ የኮሚሽኑን የመንግሥት አገልግሎት አሰጣጥ ዳይሬክተር ጄኔራል አቶ መሐመድ ሰዒድን ጠይቀን እንዲህ አቅርበነዋል።

**አዲስ ዘመን፡-በአገራችን የተካሄደውን ለውጥ ተከትሎ በሲቪል ሰርቪሱ ላይ የተደረገው የሪፎርም ሥራ ምን ደረጃ ላይ ነው ?**

**አቶ መሐመድ፡-** በሲቪል ሰርቪሱ እየተካሔደ ያለውን የሪፎርም ሥራ በሚመለከት ቀደም ሲል እንደሚታወቀው በአገር አቀፍ ደረጃ ባለፉት ሶስት አሥርተ ዓመታት የመንግሥትን የመፈፀም እና የማስፈፀም አቅም ክፍተትን ለመሙላት ሲተገበሩ የነበሩ የተለያዩ አሠራሮች እንደነበሩ ይታወቃል። የሲቪል ሰርቪስ ማሻሻያ ፕሮግራም ሲተገበርም አምስት ንዑስ ፕሮግራሞች ነበሩ። ፕሮግራሞቹ የራሳቸው ጥንካሬ እና ድክመት ያለባቸው መሆናቸውም የሚካድ አይደለም። በዋነኛነት የሲቪል ሰርቪስ ማሻሻያ ፕሮግራምን ውጤታማ ለማድረግ የተለያዩ የለውጥ መሣሪያዎች ተግባራዊ ተደርገዋል፤ ቢ ፒ አር፣ ቢ ኤስ ሲ፣ የለውጥ ሠራዊት ፣ የዜጎች ቻርተር እና ካይዘን መተግበራቸው አይዘነጋም።

የእነዚህ መተግበር ከነችግራቸውም ቢሆን አሁን ላለንበት ደረጃ አድርሶናል። ነገር ግን የራሳቸው በጎ አስተዋፅኦ ነበራቸው ተብሎ ቢታመንም ግን ያመጣሉ ተብሎ ከታሰበው የተገልጋይ እርካታ አንፃር እዚህ ግባ የሚባል ውጤት አላመጡም። እንደውም ችግሩ እየተባባሰ የአገልግሎት አሰጣጣችን ከጊዜ ወደ ጊዜ በቅሬታ እና በእሮሮ የተሞላ እንዲሆን አድርጓል። አሁን ላይ እንደሚሰማው የአገልግሎት አሰጣጡ ሲፈተሽ አገልግሎት በገንዘብ እየተገዛ መሆኑ እየታየ ነው።

ክፍተቱ የመጣው የለውጥ መሣሪያዎቹ ችግር የነበረባቸው በመሆናቸው ሳይሆን ምክንያቱ ሌላ ነው። አንዳንዶቹ ከውጪ የተወሰዱ ናቸው። በውጪው ዓለም ያደጉ አገሮች ተጠቅመውባቸው ውጤት ያስገኙ ናቸው። ወደ እኛ አገር ስናመጣው የፈፀምንበት አግባብ የራሱ የሆነ ውስንነት ስለነበረበት ነው። አመራሩም ሆነ ሠራተኛው ለውጡን በባለቤትነት ከመምራት አንፃር ያለ ውስንነት ነው። ለውጡ ቁርጠኝነትን፣ ለሥራው መሰጠትንና ዋጋ መክፈልን ይጠይቃል። ለውጥ የሚከብድ ነው። ይህንን አውቆ ከአመራር እስከ ፈፃሚ ድረስ በባለቤትነት ይዞ ለውጡ የታለመለትን ግብ እንዲመታ ከማድረግ አንፃር ጉድለቶች እንደነበሩበት የተለያዩ ጥናቶች ያመለክታሉ።

**አዲስ ዘመን፡- ለውጥ ሲሉ እነቢ ፒ አርን ማለትዎ እንጂ የአሁኑን ለውጥ በሚመለከት ማለትዎ አይደለም?**

**አቶ መሐመድ፡-** አዎ! 14ቱን የአቅም ግንባታ ፕሮግራሞች እና አምስቱን የሲቪል ሰርቪስ ማሻሻያ ፕሮግራሞችን ማለቴ ነው። የአገልግሎት አሰጣጥ ማሻሻያ ንዑስ ፕሮግራሙን ውጤታማ ለማድረግ ቢ ፒ አር፣ ቢ ኤስ ሲ፣ ካይዘን እና የዜጎች ቻርተር ሲተገበሩ ነበር። የመንግሥትን የማስፈፀም አቅም ስንል ሶስት ነገሮችን ነው። በአደረጃጀት፣ በአሠራር እና በሰው ኃይል ማለት ነው። ለምሰሌ ቢ ፒ አር አደረጃጀትን ይቀይራል። ለተገልጋይ ምቹ ማድረግ እና የሥራ ፍሰትን የማቀላጠፍ ሥራዎችን ያደራጃል። ቢ ኤስ ሲ ደግሞ ቆጥረን የምንሰጥበት፤ የሰጠነውን ማለትም አፈፃፀምን ወይም ፍሬውን ቆጥረን የምንረከብበት ነው። የአፈፃፀም መለኪያ መሣሪያ ነው። የተቋምን ስትራቴጂ እስከ ታች ድረስ የምናወርድበት ነው። የግንኙነት መሣሪያም ነው። ነገር ግን ይህንን ጨምሮ ሌሎችም የለውጥ መሣሪያዎች ተጠቅሞ እና በአግባቡ ይዞ ውጤት ከማምጣት አንፃር በአመራርም ሆነ በባለሙያ በኩል በርካታ ክፍተቶች በመኖራቸው ውጤታማ አላደረገንም። አሁን ደግሞ ከጊዜ ወደ ጊዜ የተገልጋይ እርካታ መጨመር ሲገባው የመቀነስ ሁኔታ እየተስተዋለ ነው።

**አዲስ ዘመን፡-የአገልግሎት አሰጣጥ ላይ የሚታዩ ችግሮች ዛሬም እንዳልተቀረፉና በተለይ በአንዳንድ ተቋማት ተባብሰው እንደቀጠሉ ይታወቃል። ለእዚህ የተለያዩ ምክንያቶች ቢኖሩም የበፊቶቹ የለውጥ መሣሪያዎች ውጤታማ ያልሆኑት ፖለቲካው እና አገልግሎት አሠጣጡ ባለመነጣጠሉ ስለመሆኑ ይገለፃል። እዚህ ላይ ምን ይላሉ?**

**አቶ መሐመድ፡-** ትክክል ነው። እነዚህ የለውጥ መሣሪያዎች ስኬታማ ያልሆኑት አተገባበር ላይ በነበረው ክፍተት ነው። በተቋም ደረጃ ለውጥ ያመጣሉ፤ ሕዝብን ያረካሉ፤ አገርን ለትልቅ ደረጃ ያደርሳሉ፤ የኢኮኖሚ ለውጡን ያሳካሉ ተብለው ቢመጡም ሲፈፀሙ ግን ከፖለቲካ ጋር መቀላቀሉ ችግር ፈጥሯል። ለምሳሌ የለውጥ ሠራዊት በሚል አንድ ለአምስት በማደራጀት ጠንካራው ደካማውን እየደገፈው በትጋት በመሥራት ውጤታማ መሆን እንዲቻል ነበር። ኮሪያ፣ ጃፓን እና ሌሎች አገሮች የለውጥ መሣሪያ በሚል አሁንም ድረስ ለውጥ ያመጡበት ነው። ካይዘንም ቢሆን ተመሳሳይ ነው። ነገር ግን ሥራን መገምገሚያ ሳይሆን እስከ ማኅበራዊ ግንኙነት ድረስ የዘለቀ የፖለቲካ መገምገሚያ መሣሪያ ሆነ።

አሁንም ድረስ በመንግሥት ተቋማት እንዲፈፀም የምናደርገው የዜጎች ቻርተር አለ። የዜጎች ቻርተር ከእንግሊዝ የተወሰደ ሲሆን፤ በ1990ዎቹ ሥራ ላይ የዋለ ነው። የመንግሥት ተቋማት አገልግሎት አሰጣጣቸውን በጊዜ፣ በመጠን፣ በወጪና በጥራት ተገማች የሚያደርግ ነው። ይህንንም ለተገልጋያቸው ቃል ይገባሉ። ይህ ዜጎች መብታቸውን የሚጠይቁበት ሥርዓት ነው። በጣም ሳይንስ ነው። ተቋማት ለይስሙላ ያዘጋጃሉ። ነገር ግን የሼልፍ ቀለብ ከመሆን የዘለለ አይደለም። ለተገልጋዩ እና ለዜጋው ጠብ የሚል መሻሻልን አልፈጠረልንም። የፈፀምንበት እና ያስፈጸምንበት ክፍተት ሊሆን ይችላል ብዬ አስባለሁ።

**አዲስ ዘመን፡- በሲቪል ሰርቪሱ ውስጥ ብልሹ አሠራርና ሌብነት መስፋፋቱን አገልግሎት ፈላጊዎች ይናገራሉ። ስመሆኑ እነዚህ ችግሮችን ለማቃለል በእናንተ በኩል ምን እየሠራችሁ ነው?**

**አቶ መሐመድ፡-** ከላይ የጠቀስኳቸው ጉዳዮች አፈፃፀም ላይ ጉድለት ነበረባቸው ያስባለው አንዱ ምክንያት ለሁሉም ተቋም አንድ አይነት የለውጥ መሣሪያ እንዲጠቀሙ በመደረጉ ነው። ሁሉም ሰው አንድ ዓይነት መጠን ያለው ጃኬት እንዲለብስ ማድረግ ማለት ነበር። ጃኬቱ ለአንዳንዱ ይጠባል፤ ለአንዳንዱ ይሰፋል፤ ለአንዱ ሲያጥር ለሌላው ይረዝማል። የተማከለ የለውጥ ሥራ ነበር። አሁን ግን በአገር ደረጃ የመጣውን ለውጥ ተከትሎ፤ ያልተማከለ የለውጥ መሣሪያ ለመተግበር ታስቧል።

ተቋማት ለሥራቸው የሚመቻቸውን የለውጥ መሣሪያ መተግበር ይችላሉ። ኮሚሽኑ ተቋማት የሚፈልጉትን እና የመረጡትን የለውጥ መሣሪያ ላይ የማማከር፣ የሥልጠና፣ የክትትል ድጋፍ እና ሌሎች የድጋፍ ሥርዓቶችን ያደርጋል። ይህ ሲባል ሁሉም መንግሥታዊ አገልግሎትን ሊያሻሽሉ የሚችሉ ሥራዎችን በኮሚሽኑ በመንግሥት ዘርፍ አገልግሎት አሰጣጥ ፍኖተ ካርታ ላይ የተቀመጡ ነገሮች መሆን እንዳለባቸው መዘንጋት የለበትም። የመንግሥት አገልግሎት አሰጣጥ ማሻሻያዎች አሉ። አንዱ የዜጎች ቻርተር ነው። ተቋማት አገልግሎት አሰጣጣቸውን ተገማች ማድረግ አለባቸው። በጊዜ፣ በመጠን እና በጥራት የሚሠሩትን ማሳወቅ አለባቸው። ከተገልጋዮቻቸው ጋር መግባባት ይጠበቅባቸዋል። ከተገልጋይ ጋር ከተግባቡ በኋላ ባስቀመጡት መሥፈርት መሠረት አገልግሎት መሥጠት አለባቸው። ባይሠጡ ተጠያቂ መሆን አለባቸው።

ዜጋው ለሚዲያ ሊያጋልጣቸው ይችላል። ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ቋሚ ኮሚቴ፣ ለእንባ ጠባቂ ለተለያዩ የዴሞክራሲ ተቋማት ሊጠቁምባቸው ይችላል። አገልግሎት አሰጣጥን በገንዘብ ለሚሰጥ ተቋም ሚዲያው ሊያጋልጠው እና ሊያሳፍረው ጥሩ የሠራውንም ሊያበረታታው ይችላል። የተለወጠ ዘመን ላይ ያለ የተለወጠ ዜጋ አዳጊ ፍላጎት ያለው በመሆኑ በቴክኖሎጂ የተደገፈ አገልግሎት ይፈልጋል። ተቋማት የሚሰጡት አገልግሎት ወደ ቴክኖሎጂ መቅረብ አለበት። አገልግሎት አሰጣጥ ላይ ተገልጋይን በትህትና እና በክብር አነጋግሮ መረጃ መሥጠት አንድ ችግር ነው። ይህን ችግር የሚፈታ የዜጎችን የአገልግሎት ቅሬታ የሚቀርብበት መመሪያ ተዘጋጅቶ የድሮ ጠቅላይ አቃቤ ሕግ የአሁኑ ፍትህ ሚኒስቴር አጣርቶት ለሁሉም ተቋማት ተልኳል። የዜጎች የአገልግሎት ቅሬታ የሚቀርብበት ሥርዓት መዘርጋት እንዳለበት ታምኖ እየተሠራ ነው።

በዚህች አገር ላይ ያለው ሌላው ትልቁ ችግር ዜጎች ሕገመንግስቱ በፈቀደላቸው የመገልገል መብታቸው

> **የተለወጠ ዘመን ላይ ያለ የተለወጠ ዜጋ አዳጊ ፍላጎት ያለው በመሆኑ በቴክኖሎጂ የተደገፈ አገልግሎት ይፈልጋል። ተቋማት የሚሰጡት አገልግሎት ወደ ቴክኖሎጂ መቅረብ አለበት**



# ተጠየቅ

በገንዘብ እየተቀየረ መሆኑ ነው። የእዚህ መንስኤው በዚህች አገር ላይ ተጠያቂነት ባለመኖሩ ነው። ያጠፋ አመራር ሲጠየቅ አይታይም። አገልጋይን ያንገላታ፣ ያለአግባብ ያመላለሰ ያመናጨቀ ባለሙያ ሲጠየቅ አይታይም። ሕጉ ይላል፤ ነገር ግን ማን ይጠይቅ? ይህ ሥርዓት መኖር አለበት እያልን ነው። ጠዋት መግባት እና ማታ መውጣት መሥራት አይደለም። ተገልጋዩን አርክቻለሁ ወይ? ብሎ ቢሮ መቀመጥ ብቻ ሳይሆን ተቋማት የተገልጋዮቻቸውን እርካታ ማስጠናት እና ጉድለቶችን ማወቅ አለባቸው። ሌላው መሠረታዊ ነገር በሥርዓት ደረጃ እየተዘረጋ ያለው ለተገልጋዩም ሆነ ለአገልጋዩ፤ ሠራተኛው ቀልጣፋ እና ውጤታማ አገልግሎት መሥጠት የሚያስችለውን ምቹ የሥራ አካባቢን መፍጠር ነው።

ይሄ የሠራተኛውን የዕውቀት እና የአስተሳሰብ ክፍተት ካለበት የክህሎት ክፍተቱን መሙላት ይጠይቃል። ለተገልጋዩ አገልግሎት ለመስጠት የሚያመች በቂ ግብዓት አለው ወይ? ብሎ ያንን መሙላት ያስፈልጋል። ለእናቶች እና ለእህቶች ሕፃን ልጆች ላላቸው ሠራተኞች የሕፃናት ማቆያ መኖር አለበት። ሠራተኛው በተመጣጣኝ ዋጋ ጥራት ያለው ቁርስ እና ምሳ የሚያገኝበት ካፍቴሪያ መኖር አለበት። ከመንግሥት የሥራ ሠዓት ቀንሶ ስኳር ፍለጋ ወረዳ ሄዶ መሠለፍ የለበትም።

እዛው አገልግሎት በሚሠጥበት ተቋም የሚሸምተውን ማግኘት አለበት። በተቋማት በተመጣጣኝ ወለድ የቁጠባ ማኅበር ማደራጀት ያስፈልጋል። የትራንስፖርት አቅርቦት መኖር አለበት። የተጀማመረ ነገር አለ። ግን አሁንም ትራንስፖርት ላይ ተጠናክሮ መቀጠል አለበት። ሌላው ትልቁ ነገር ቤት ነው። የመንግሥት ሠራተኛው አራት ሺህ ብር ተቀጥሮ ቤት ስንት ብር ይከራያል? ነባሩም ሠራተኛው ከከተማ ርቆ ስለሚከራይ አገልግሎት ሰጪው በሚፈልገው ሰዓት መገኘት አይችልም። ጠዋት ይረፍድበታል። ማታ ፈጥኖ ይወጣል። ስለዚህ ለአገልግሎት ምቹ ሁኔታ ለመፍጠር የቤት አቅርቦት መኖር አለበት።

የመንግሥት ሠራተኛው የሚከፈለው ደሞዝ አሁን ካለው የኑሮ ውድነት አንፃር በቂ አይደለም። በእርግጥ ደሞዝ መጨመር የኑሮ ውድነትን ያባብሳል። ገበያውን ለማረጋጋት ታስቦ ጭማሪ ቢቆምም ለሠራተኛው ማሰብ ይገባል ብዬ አስባለሁ። ይሄ ሲኖር ሰራተኛው ቀልጣፋ አገልግሎት ሊሰጥ ይችላል። በእነዚህ ላይ የመንግሥት አገልግሎት መስጫ ማሻሻያ እርምጃዎች ብለን በፌዴራል ተቋማት ከላይ የተጠቀሰው እንዲሠራ ክትትል እና ድጋፍ እያደረግን ነው።

**አዲስ ዘመን፡- የሲቪል ሰርቫንቱ ተገቢው አገልግሎት እንዲሰጥ በየጊዜው የሚደረጉ የአቅም ግንባታ ሥራዎች ምን ይመስላሉ?**

**አቶ መሐመድ፡-** ሠራተኛው ተገልጋይ ደሞዝ ከፋይን በሚመጥን መልኩ ቀልጣፋ አገልግሎት ለመስጠት ያለበት ክፍተት በእርግጥም መሞላት አለበት። እዚህ ላይ የአገልጋይነት ስሜት ማነስ ሊሆን ይችላል። የክህሎት ችግር ወይም የዕውቀት ውስንነት ሊኖር ይችላል። የግብዓት እጥረትም ያጋጥማል። ይህንን እየፈተሹ መሙላት ያስፈልጋል። ይህ ሲሞላ የመፈፀም እና የማስፈፀም አቅም ክፍተት እየተሞላ ሲሄድ በአደረጃጀት፣ በአሠራር እና በሰው ኃይል ላይ ትልቅ ሥራ ሲሰራ ውጤት ማምጣት ይቻላል።

የሰው ኃይል ላይ ካልተሠራ አደረጃጀት ቢያምር ቢሮ ቢሽቀረቀር ዋጋ የለውም። ተቋማት በዋናነት የሰው ኃይላቸው ላይ ኢንቨስት ማድረግ አለባቸው። ተጠያቂ መሆን ያለበትን ተጠያቂ ማድረግ ይገባል። የመንግሥት ሠራተኛ ማለት የመንግሥት ፖሊሲን አስፈፃሚ ነው። የፈለገው የፖለቲካ አመለካከት ቢኖርም ወደ መንግሥት መሥሪያ ቤት ሲገባ ገዢው ፓርቲ ወይም የወቅቱ መንግሥት የሚያወጣቸውን ፖሊሲዎች ያለምንም መሸራረፍ በውጤታማነት መፈፀም የግድ ነው። ይሔ በሲቪል ሰርቪስ መተዳደሪያ ሕግ በ1064/2010 ላይ ተቀምጧል። ሲቪል ሰርቪሱ በሚመራበት ሕግ ላይ ማንኛውም ሠራተኛ ቃለ መሐላ ፈፅሞ ሲቀጠር ማንኛውም ሠራተኛ ያለምንም አድሎ ፍትሐዊ አገልግሎት እንዲሰጥ ይጠበቃል።

ያለምንም ተጨማሪ ጥቅማ ጥቅም እና መደለያ አድሎ ሳይፈፅም የመሥራት ግዴታ አለበት። አቅም ሲባል ተቋማዊ አቅም ማለት ነው። የሠራተኛ አቅም ሲባል በክህሎትም፣ በአገልጋይነት አስተሳሰብም በሥነምግባር ማለትም የሙያዊ ሥነ ምግባር ላይ ክፍተት አለ ከተባለም ያ ተጠንቶ መሞላት አለበት። የምንዘረጋው የአሠራር ሥርዓት ያንን ክፍተት ለመሙላት የሚያግዙ ናቸው።



> **በዚህች አገር ላይ ተጠያቂነት ባለመኖሩ ነው። ያጠፋ አመራር ሲጠየቅ አይታይም። አገልጋይን ያንገላታ፣ ያለአግባብ ያመላለሰ ያመናጨቀ ባለሙያ ሲጠየቅ አይታይም**

**አዲስ ዘመን፡-ከፍ ብለው የአገልግሎት አሠጣጡ ላይ ያሉ የሌብነት እና መሠል ችግሮችን ለመከላከል አመራርም ሆነ ባለሙያን ተጠያቂ ለማድረግ ከማን ምን ይጠበቃል? ከቋሚ ኮሚቴ ግምገማ ባሻገር በሌላ በኩል ምን መሠራት አለበት? የእናንተ ሚናስ ምን ያህል ነው?**

**አቶ መሐመድ፡-** ከተጠያቂነት አንፃርም ማንም ሰው ባጠፋው ልክ መጠየቅ አለበት። ለዜጋ የሚገባውን አገልግሎት ባለመስጠት ቀርቶ በጥራት እና በፍጥነት ውጤታማ ሆኖ አገልግሎት አለመስጠት ያስጠይቃል። ነገር ግን የሚጠይቅ ስለሌለ እንጂ ያስጠይቃል። በእኛ በኩል ይሄ ሥርዓት ተግባራዊ እንዲደረግ በየደረጃው ተጠያቂ የሚያደርጉት ተቋማት ናቸው ብለን እናምናለን። ራሳቸው ተቋማት ብቻ አይደሉም፤ የዴሞክራሲ ተቋማትም ኃላፊነታቸውን መወጣት አለባቸው።

ተጠያቂነት ማለት እስርቤት ማስገባት ወይም ፍርድ ቤት መገተር ብቻ አይደለም። ያልሠራውን የበደለውን ተቋም በሚዲያ ማሳጣትም ተጠያቂነትን ማስፈን ነው። እኛ አገር ላይ ሕዝብን አስለቅሷል ተብሎ የሚነገርለት የትኛው ተቋም ነው?፤ የምናየው እኛ ይሄን ሠርተናል ጥሩ አድርገናል ሲል ብቻ ነው። ነገር ግን ያለአግባብ የእዚህ መሥሪያ ቤት ሠራተኛ ገንዘብ ጠይቋል ብሎ ማጋለጥ መለመድ አለበት። ለዚህ በዋናነት ተጠያቂ ማድረግ ያለባቸው ተቋማቱ ራሳቸው ቢሆኑም በሌላ መልኩ በአገር ደረጃ የተዘረጉት የክትትል እና የቁጥጥር አካላት የምክር ቤቱ ቋሚ ኮሚቴዎች ሚዲያውም መከታተል አለበት ብዬ አስባለሁ። እኛ የምናደርገው የአሠራር ሥርዓት መዘርጋት እና መደገፍ ነው። ችግሮችን ማጥናት ነው። ችግሮችን አጥንተን እርምጃ እንዲወሰድባቸው ለሚመለከታቸው አካላት ግብረ መልስ እንሰጣለን። ለጠቅላይ ሚኒስትር ጽሕፈት ቤት፣ ለቋሚ ኮሚቴ ለሚዲያም ግብረመልስ የመስጠት ሥራ እንሠራለን። ዋናው ሥራ የአሠራር ስርዓት የመዘርጋት የመደገፍ እና ክፍተቶችን እያጠኑ የመፍትሔ እርምጃ የማቅረብ ሥራ ላይ ነን።

**አዲስ ዘመን፡-ከለውጡ በፊት ተጀምሮ የነበረው የሲቪል ሰርቫንቱን ደሞዝና ጥቅማ ጥቅም ለማቀራረብ የተጀመረው —የሥራ ምዘና እና የደረጃ አወሳሰን“ የፖይንት ሬቲንግ ሥራ ምን ላይ ደረሰ?**

**አቶ መሐመድ፡-** ለእኩል ሥራ እኩል ክፍያ የሚለው የሥራ ምዘና እና የደረጃ አወሳሰንን በሚመለከት ሥራዎችን መዝኖ ደረጃ መሥጠት ላይ ያተኩራል። ለሠጠው ደረጃ ክፍያን ይበይናል። እርሱ ሥራ በፕሮጀክት ተይዞ ብዙ ጊዜ የቆየ አሁን ተግባራዊ እየተደረገ ያለ ሥራ ነው። ሥርዓቱ አዲስ በመሆኑ እዚህም እዚያም ቅሬታዎች ሊነሱ ይችላሉ። በአገሪቱ ውስጥ ያለውን የተዘበራረቀ የተለያዩ ስኬሎችን ወጥ ለማድረግ የተሠራ ነው። እዚህ ላይ የሚሠራው ክፍል ሌላ በመሆኑ ብዙ ለማለት እቸገራለሁ።

**አዲስ ዘመን፡- የመንግስት ሠራተኛው በተለይ አሁን ባለው ሁኔታ በኑሮ ውድነት ጉዳት እንዳይደርስበት ምን እየተሰራ ነው?**

**አቶ መሐመድ፡-** ይህም ተመሳሳይ ነው። ነገር ግን የአገር አቅም ይጠይቃል። ይህ ሲደረግ በገበያው ላይ የሚፈጥረው አሉታዊ ጫናም ይታያል። እኛ አገር ላይ ለሠራተኛው መቶ ብር ተጨምሮ፤ ነጋዴው ሁለት መቶ ብር ጨምሮ ይጠብቃል።

አንዳንዴ ከጥቅሙ ጉዳቱ የሚያመዝንበት ሁኔታ ይፈጠራል። ይህም ሆኖ ግን አያስፈልግም እያልኩ አይደለም። መንግሥት ከአገር አቅም አንፃር አይቶ መፍትሔ መሥጠት እንዳለበት በግሌ አምናለሁ። ነገር ግን ከጥቅማ ጥቅም አንፃር ይሄ ሥራ የሚሠራው በመንግሥት ነው።

መንግሥት ሲቪል ሠርቪስ ኮሚሽንን አጥና ሲለው ኮሚሽኑ ያጠናል። የአገር አቅምን እና ሁኔታዎችን አይቶ ለመንግሥት ሠራተኛው ደሞዝ መጨመር እፈልጋለሁ ሲል ሲቪል ሰርቪስ አጥንቶ ያቀርባል። ሲፀድቅ ይከፈላል። ከዛ ይልቅ ግን ቀድሞ የእርከን ጭማሪ ነበር። የእርከን ጭማሪው ከታገደ አስርተ ዓመታትን አሳልፏል።

ይሄ በሠራተኛውም ዘንድ ቅሬታን የፈጠረ ሲሆን በአገልግሎት አሰጣጡም ላይ ጫና አሳድሯል። ወደ ፊት ይታሰብበታል ብዬ እገምታለሁ።

ሌሎች በአፈፃፀም ላይ የተመሠረቱ የሠራተኛው ትጋትን የበለጠ የሚጨምር ሌሎችን ደግሞ አፈፃፀምን መሠረት ያደረገ ማበረታቻ ወደ ፊት የሚታሰብበት ይሆናል።

**አዲስ ዘመን፡- ስለነበረን ቆይታ እጅግ አመሰግናለሁ።**

**አቶ መሐመድ፡-** እኔም አመሰግናለሁ።

ፖለቲካ እና ልዩ ልዩ

# ነፃ ሃሳብ



(ጌታቸው በለጠ /ዳግላስ ጴጥሮስ)
gechoseni@gmail.com

የሥነ ጽሑፍና የኮሙዩኒኬሽን ባለሙያ ናቸው። የኢትዮጵያ ደራስያን ማኅበርን ለዘጠኝ ዓመታት ያህል በፕሬዚዳንትነት መርተዋል። ከ1977 ዓ.ም ጀምሮ በአዲስ ዘመንና የዛሬይቱ ኢትዮጵያ ጋዜጣ፤ በሀገር ውስጥና በውጭ ሀገራት ታትመው በሚሠራጩ የተለያዩ የኅትመት ውጤቶች ላይ (ዳግላስ ጴጥሮስ) በሚል የብዕር ስሙ በርካታ ጽሑፎችን አስነብበውናል። በግላቸው 12፣ ከሌሎች ጸሐፍት ጋር በርካታ መጻሕፍትን ለአንባብያን አቅርበዋል።

# አገር ጠል ባለ አገሮች

### አገሬን እንደ ተማሪ፤

ማነጻጸሪያው ይጥበቅም ይላላ አገሬን የማመሳስላት ከመደበኛ ተማሪ ጋር ነው። ተማሪ ይማራል፤ የተማረው ትምህርት ግቡን ስለመምታቱ ለማረጋገጥም በተርምና በሴሚስተር እየተፈተነ ዕውቀቱ ይረጋገጣል። አልፎ አልፎም ተማሪው ከተማረው ትምህርት ውጭ የንባብ ጥረቱንና አርቆ ገማችነቱን ለማረጋገጥ ሲፈለግ በትምህርቱ ውስጥ ያልተሸፈኑ አንዳንድ ጠጠር ያሉ ጥያቄዎች ጣል ጣል ይደረጋሉ። ይህ አካሄድ በየትኛውም መምህር ዘንድ የሚተገበር የተለመደ ተግባር ነው። ዓላማው ተማሪውን ለመጥቀም እንጂ ለጉዳት ታስቦ አይደለም።

አገሬም እንዲሁ በዘመናት ውስጥ ስትፈተን የኖረችው በገመተችውና በተለማመደቻቸው ችግሮቿ ብቻ ሳይሆን ባልጠረጠረቻቸው ሰበቦችና መንስዔዎች ጭምር ነበር/ነውም። ለምሳሌ፡- በየዘመናቱ ተላምዳው አብራው የኖረችው ድርቅ “በየምንትስ ዓመታት” ወቅት ጠብቆ በቋሚነት እንደሚከሰት በመንግሥትና በባለሙያዎች እየተነገረንና በችግሩም እየተጠበስን መኖራችን እየታወቀ እነሆ ዛሬም ድረስ ዕንቆቅልሻችንን የሚፈታ “ታዳጊ ኃይል” አጥተን ረሃብና ቸነፈር መዘመሩራችን ሆኗል።

እንኳን እኛ “ሰብዓውያን” የምንሰኝ ፍጡሮች ቀርተን አባይ፣ ዋቢ ሸበሌ፣ አዋሽ፣ ገናሌ፣ ባሮ ወዘተ. እያልን በሽንገላ የምናንቆለጳጵሳቸው ወንዞቻችን አፍ ቢኖራቸው በረሃብተኛነት በምንታወቅበት እንቆቅልሻችን ሳይሳለቁብን የሚቀሩ አይመስለንም። በተለየ ሁኔታ ግን በአርምሞ እየታዘበን እብስ የሚለው የዋቢ ሸበሌ ወንዝና ከአገር ጫፍ እስከ ጫፍ በትዝብት እየገላመጠን የሚያልፈውና በአሸዋ ውስጥ ሰምጦ የሚያንቀላፋው የአዋሽ ወንዝ ተፋሰሶች ግራና ቀኛቸው ለዘመናት በድርቅ እየተንገበገቡ ስለሚያስተውሏቸው የልባችሁን ገልጻችሁ የምር ገስጹን ብንል “ሥራ ጠሎች” ብለው እንደሚንቁን ለመገመት አይከብድም።

**የአገሬ ፈተናዋና ችግሯ ከታወቀ ስምን መልሱ ጠፋት?** በየአሥር ዓመቱም ይሁን በየአሥራ አምስት ዓመቱ ዙሩን ሳያዛንፍ እየጠበቀ ድርቅ በኢትዮጵያ እንደሚከሰት ትንቢቱን ከሚነግሩን ይልቅ ለምን ፍቺውን ጨምረው አያሳውቁንም? “ሕልሙንም ፍቺውንም አሳውቁኝ” (ትንቢተ ዳንኤል ምዕ. 2)፤ በማለት ጠቢባኑን የሞገተው የባለቢሎኑ ንጉሥ ናቡከደነፆር ለካስ ልክ እንደኛው ግራ ቢገባው ኖሯል። አሥር ዓመት ወይንም አሥራ አምስት ዓመታት ትንቢቱን ከነገሩን ጀምሮ እያንጎላጀጁ ረሃቡንና ቸነፈሩን በጉጉት የሚጠብቁ መንግሥታዊ ተቋማትስ ለምን ለመፍትሔው ሠርተው አላሰሩም? እስከ መቼ ስንዴ ለምነን፣ እስከ መቼስ የድርቅ መርዶ ለማርዳት ዓለም አቀፍ ረጂዎችንና መገናኛ ብዙኃንን በኮንፍረንስ ስም እየሰበሰብን እዬዬ እያልን እናለቅሳለን?

“ሚሊዮኖች ተራቡ፣ ሚሊዮን እንስሳት አለቁ፣ የተፈጥሮ አራዊቶች ተሰደዱ፣ ይሄን ያህል ሰው በረሃብ ምክንያት ተፈናቀለ፣ ድርቁ ሲከፋም ይህንን ያህል ሰው ሞተ ወዘተ.” የሚለው የመከራ አበሳችን መቼ ነው ከላያችን ተንከባሎ የሚወድቀው? መደበኛ ተማሪ የተርምና የሴሚስተር ፈተናዎችን ሳያሰልስ እንደሚፈተን ሁሉ ምክንያቱ በግልጽ እየታወቀ አገሬ እስከ መቼ በድርቅና በረሃብ እየተፈተነችና ለእርዳታ እጇቿን እንደዘረጋች እንድትኖር እንፈርድባታለን? በመሪር ልቅሶ እያነባችስ ዘመኗን በእህህታ እንድትጨርስ ለምን በየንባት? መልስ ባናገኝም እንጠይቃለን። ባንደመጥም እንናገራለን።

አስተያየት ስንሰጥ ከማድመጥ ይልቅ፤ “ቢጮኹና ቢጽፉ ምን ያመጣሉ”፤ እያሉ እንደ ጅል በልባቸው ቢስቁብንም ኀሊናቸውን መሞገታችን አይቀርም። ስህተትን ከማረም ይልቅ በመከላከል ተወዳዳሪ የማይገኝላቸው ሹማምንቶቻችን ቢሰሙን ይበጃቸዋል፤ ካልሰሙም ውጤቱ ይጠፋቸዋል ተብሎ አይታሰብም። “ምከረው፣ ምከረው እምቢ ያለ እንደሆነ መከራ ይምከረው” የሚለው ብሂል ለአፍ የሚቀል አባባል ብቻ ሳይሆን ለእውነትነቱ ማረጋገጫ ሊቀርብለት የሚችል የጠቢባን ምክር ጭምር ነው - ከገባቸው።

> አገር ጠል ባለ አገሮች ሁልግዜም የሚሰባሰቡትና ግምባር የሚፈጥሩት የግል ጥቅም መኖሩን ሲያረጋግጡ ነው። በአንደበታቸው ጫፍ የሕዝብን ስም ቢያንጠለጥሉም በልባቸው ሲቀምሙ ውለው የሚያድሩት ግን የክፋት አሲድ ነስንሶ ለማለያየትና ለማናቆር ነው። የሚያጅባቸውን ሠራዊት የሚያሰክሩት፣ ሸንጓቸውን የሚያወፍሩት፣ የሴራ አሸክላቸውን ዘርግተው በአገር አንገት ሸምቀቆውን ለማጥበቅ የሚሞክሩት አገር ታንቃ የምትሞት እየመሰላቸው ነው። አገር ጠል ባለ አገሮች ራሳቸው ሞተው በድናቸው በአፈሯ ውስጥ ይሸሸግ ካልሆነ በስተቀር አገር ሞታ ንፍሮ እየተቃመ በሙሾ የምትቀበር ተሰባሪ ሸክላ እንዳልሆነች እንመሰክራለን

### የአገር ጠሉች አገር፤

አገር ጠል ባለ አገሮች በሚሸርቡት ሴራ ይህቺ መከረኛ አገር እስከ መቼ ቁም ስቅሏን እንዳየች ትኖራለች? የሃሳብ ልዩነቶችን በተረጋጋ ስሜት ተነጋግሮና ተማምኖ ከመተራረም ይልቅ በትንሽ በትልቁ “ሰይፍ ለመማዘዝስ” አዚም የጫነብን ምን የሚሉት ኃይል ነው? አገርን እያዋረዱ ለአገር ተቆርቋሪ መስሎ መታየት፣ አገርን ለማፈራረስ አውታሯን እያናጉ ስለ ሕዝብ ልዕልና መስበክ፤ እኮ ምን የሚሉት ክህደት ነው? እጅግ የሚያሳዝነው ነገር በአገር ላይ እየዶለቱና ክብሯንና ሕዝቧን ዝቅ አድርገው ማዋረዳቸው እየታወቀንና እየታወቃቸው ተቆርቋሪ መስሎ ለመታየት “በእያንያዊ” ሴራ ራሳቸውን እንደ እስስት እየለዋወጡ የሚኖሩት የአገር ጠል ባለ አገሮች ጉዳይ ከመቼውም ጊዜ ይልቅ ዛሬ አሳሳቢነቱ የገዘፈ ይመስላል።

እውነቱን አፍርጠን እንምከርበት የሚል ወኔ የሚኖረን ከሆነ ይህቺ መከራ ቀለቧ የሆነው አገር ዛሬም ድረስ እየተፈተነች ያለችው ከባዕዳን ይልቅ “ባለ አገር ነን” በሚሉና ከራሷ ማህጸን በበቀሉ ልጆቿ እንደሆነ በብዙ ማሳያዎች ማመላከት ይቻላል። የምንኮራበትንና የምንኩራራበትን የነበር ታሪኮቻችንን ድርሳናት ለጊዜው ገጻቸውን አጥፈን በማቆየት የዛሬውን ገመናችንን ወደ መፈተሹ ጠንከር ብንል እውነታው ፍንትው ብሎ ሊታየን ይችላል።

አገር ጠል ባለ አገሮች ሁልግዜም የሚሰባሰቡትና ግምባር የሚፈጥሩት የግል ጥቅም መኖሩን ሲያረጋግጡ ነው። በአንደበታቸው ጫፍ የሕዝብን ስም ቢያንጠለጥሉም በልባቸው ሲቀምሙ ውለው የሚያድሩት ግን የክፋት አሲድ ነስንሶ ለማለያየትና ለማናቆር ነው። የሚያጅባቸውን ሠራዊት የሚያሰክሩት፣ ሸንጓቸውን የሚያወፍሩት፣ የሴራ አሸክላቸውን ዘርግተው በአገር አንገት ሸምቀቆውን ለማጥበቅ የሚሞክሩት አገር ታንቃ የምትሞት እየመሰላቸው ነው። አገር ጠል ባለ አገሮች ራሳቸው ሞተው በድናቸው በአፈሯ ውስጥ ይሸሸግ ካልሆነ በስተቀር አገር ሞታ ንፍሮ እየተቃመ በሙሾ የምትቀበር ተሰባሪ ሸክላ እንዳልሆነች እንመሰክራለን።

የእንሽላሊት ባህርይ የተላበሱት እኒህን መሰል አገር ጠል ዜጎች ስለ ማንነታቸው የሚያስመሰክሩት በወረቀት መታወቂያቸው እንጂ ለሕዝብ የሚጠቅም ፍሬ በማዝመራቸው አይደለም። የእንሽላሊትን ስም ካነሳን አይቀር ስለ ባህርይዋ ጥቂት ነገር መናገሩ ተገቢነት ይኖረዋል። እንሽላሊት መገኛዋ የትም ነው። ከቤተ መቅደስ እስከ ቤተ መንግሥት፣ ከገበሬው ማሳ እስከ ነጋዴው መደብር፣ ከተራ መኖሪያ ቤት እስከ “ባለጠጎች” መንደር፣ ከትምህርት ቤት እስከ ሠራዊት ካምፕ፣ ከሐኪም ቤት እስከ ፍርድ ቤት ወዘተ. ሽው እልም፣ ሽር ብትን እያለች የምትውለው በነፃነት ነው።

የአገር ጠሎች ውሎም እንዲሁ ነው። “ከዙፋን ቤት” እስከ ራስ ቤት፣ ከአደባባይ እስከ ጓዳ፣ ከቤተ መቅደስ እስከ “ቤተ-ፖለቲካ”፣ ከንግድ ዘርፉ እስከ ፍትሕ ሥርዓቱ እግራቸውንና መረባቸውን ዘርግተው በሕዝብ ስም እየማሉ አገርን ለማረድ ካራ ሲስሉ መዋላቸውን የምናስተውለው እለት በእለት ነው። በመሸንገያ ቃላት መበልጸጋቸው፣ በልባቸው ጽላት ላይ ክፋት ቀርጸው የሕዝብን ስቃይና የአገርን መፈራረስ እየቃዡ መኖራቸው ልዩ ባህርያቸውና መታወቂያቸው ነው።

በሥልጣን ላይ የተቆናጠጡትም ሆኑ በሥልጣን ቅዠት የሚናውዙት በርካቶቹ የአገሬ ፖለቲከኞች፤ አዋዋላቸው እንደ እንሽላሊቷ በሁሉም ስፍራ ሥር ሰደው፤ በሴራ ግብራቸው ደግሞ እንደ ክፉ ኮብራ ለመናደፍ አድፍጠው የሚውሉት የተመቻቹ ሁኔታዎችን በመሰለል ነው። አገር ጠል ሆኖ ስለ አገር በጎነት ለመስበክ የሚሞክሩት በውስጣቸው የሞተው ኅሊናቸው እንዳያንሰራራ አፈር በማልበስ ጭምር መሆኑ ከገባን ሰነባብቷል።

እውነቱን እንመስክር ከተባለ አንዳንዶቹ በረቀቀና በተጠና ስልት፣ ጥቂቶች በየዋህነት እየተነዱ የሚፈጽሟቸውን የአገር ጠልነት ድርጊቶች ከትዝብት አልፈን ብንገላልጠው ብዙ ማለት ብቻ ሳይሆን ብዙ ማስረጃዎችንም ማቅረብ ይቻላል። እስከ ዛሬ የኖርነው እነዚህ በአገር ላይ መሰሪ ቲያትር የሚከውኑትም ሆኑ የሚቆጣጠራቸው አካል ይሰሙናል ብለን በመገመትና “ልብ ያለው ልብ ያድርግ” በሚል ትዝብት እየገረመምናቸው ነበር። ይህን ማድረጋችን “አካፋን አካፋ” ለማለት ድፍረቱን አጥተን ሳይሆን መንግሥታዊ ሥርዓቱን በጫንቃው ላይ የተሸከመው ባለአደራ ፓርቲ ጆሮ ይሰጠናል ብለን ተስፋ በማድረግና ለጊዜ ጊዜ መስጠቱ የሚያዋጣ ስለመሰለን ነው።

አሁን ግን ብዙው መከራችን በዝቶ “የመኖር ወይንም ያለ መኖር የሞት ጥላ ስላጠላብን” ያመቅነውን ጉዳታችንን በይፋ በመግለጥ መንፈራገጡ ይበጅ መስሎናል። እንደ እውነቱ ከሆነ አገር ጠል ባለ አገሮችን የምንተቸውን ያህል አገር ወዳድ ተብዬ “ካብ አይገቡዎችም” ወደ ሕሊናቸው ተመልሰው ለእውነት እንዲቆሙ መሞገቱ ተገቢ ይመስለናል። ብዙዎቻችን አገር አለን ብለን፣ የሕዝብ አደራ ግድ ብሎን “ከባእድ ምድር ተድላ ይልቅ የአገርን ጠረን” መርጠን ወደ ምድራችን ተመልሰን ዋጋ እየከፈልን ያለነው የግፉዓንን እምባ ያበስን፣ በሰለጠንበት ትምህርት ያገዝን መስሎን ነበር። ነገሮች ሁሉ ወደ አልተፈለጉ አቅጣጫዎች ሲሄዱ እያስተዋልንም ተረጋግተን የቆምነው ነገ የተሻለ ቀን ይመጣል የሚል ጽኑ ተስፋ በመሰነቅ ነበር።

ይህ ተስፋ እየበነነና እየተነነ አገር ጠሎች የጀግና ክብር ተሰጥቷቸው ሲታመኑ አገሬ ብለው ዋጋ እየከፈሉ ያሉት ሩቅ አላሚዎች ሲገፉ ማስተዋል ይቆጠቁጣል፤ ይመራል። ሲከፋም፤ “እረ ምረር ምረር ምረር እንደ ቅል፤ ስላልኮመጠጠ ስላልመረረ ነው ዱባ ‘ሚቀቀል” አሰኝቶ ወደ አልተፈለገ ውሳኔ ይመራል። የአገራችን መከራዋ ለምን ሊበዛና ሊንዛዛ ቻለ? “ካልመራናችሁ” ብለው የወተወቱትና በዘመድም፣ በእውቂያም፣ በፖለቲካ ቤተሰባዊነትም “በትረ ሙሴውን” ከምርጫ ኮሮጆ ያፈሱት በርካቶች የፈተናችንን “ቀይ ባሕር” ከፍለው በድል እንደሚያሻግሩን በመሐላ ሳይቀር እንድናምናቸው ካስገደዱን በኋላ ይብስ ወደ ባሕሩ ውስጥ ሲዘፍቁን መመልከት ምን ይሉት አዚም ነው። በሕዝብ ስም ምለውና ተገዝተው ሕዝብ ማማረርና መናቅ፣ በአገልግሎት አሰጣጥ ማጉላላት፣ ለራስ ጓዳ ጥቅማ ጥቅሙ ላይ መራኮት፣ ለሕዝብ መብት ደንታ ማጣት የእነዚህ አገር ጠል “ባለ አገሮች” ክፉ በሽታ ነው።

ይህንን የተሸሸገ ባህርያቸውን የገለጠው የበቀደሙ የሕዝብ ውይይት የብሶት እሪታ ነው። እንደምን በመላው አገሪቱ ተመሳሳይ ድምጽ ሊሰማ ይችላል? እንደምንስ ተመካክሮ እንደገባ ጥቂት የሰው ቁጥር ሚሊዮኖች በተመሳሳይ ድምጸትና ቃላት እምባ በተቀላቀለበት ብሶት መከራቸውን ይዘረግፋሉ። ገዢው ፓርቲ ቢገባው በውይይቶቹ ላይ የተኾጎደጎዱት የሲቃ ድምጾች ለወቅታዊ አቋሙ የውሃ ልኩ ማሳያ ቱምቢ መሆናቸው ብቻ ሳይሆን በወደፊት ዕድሉም ላይ ወሳኝና ጠቋሚ መልዕክቶች የተላለፉበት ጭምር ነበር።

ሌላው የአገር ጠልነት መገለጫ እየተንጸባረቀ የሚስተዋለው የንግዱን ዘርፍ በሞኖፖል በተቆጣጠሩ በአንዳንድ “ዘረፋ አምላኩ” በሆኑ “ባለ ሀብቶች” ላይ ጭምር ነው። ጥቂት የማይባሉ የኢትዮጵያ “ባለ ሀብቶች” እንዴት ወደ ስኬት ማማ እንደተስፈነጠሩ ታሪካቸውን የሚነግሩን ከምንም ተነስተውና ከተራ ሥራ ተመንጭቀው እንደሆነ የሚመሰክሩት በንግግር ብቻ ሳይሆን መሐላም አክለው ነው። በዕለት ሕይወታቸው ላይ የሚስተዋለው ዘረፋና ማድፋፋት የሚተገበረው ደግሞ “እንደ እናንተው ነበርኩ” በሚለው ምስኪን ሕዝብ ላይ መሆኑ ተቃርኖውን ያጎላዋል። በዚህም ጉዳይ ላይ የሕዝብ አክብሮት እንኳን ቢቀር ሕሊና እንዲከበር መረር ብለን እንጠይቃለን።

መቋጫና መደምደሚያ ሃሳባችን አንድና አንድ ነው። አገር ጠል ባለ አገሮች በወንጠፍት ይፈተሹ። ድምጻቸው ሁሌም የሚሰማ የሚመስላቸውና “ሀገር አፈራርሰው” እና ሕዝብ አስመርረው ለዘላለም የሚመኙ የፖለቲካው “ደብል ፌስ” የባህርይ ተገላባጭ ጃኬት ለባሾችም አርቀው በመመልከት ወደ ቀልብያቸው ቢመለሱ ይበጃቸዋል። የበቀደሙ የሕዝብ ስብሰባ “ለገዢዎቹ ጌቶቻችን” የትናንት ትዝታ ብቻ ሳይሆን የነገ የማንቂያ ደውል ሆኖ ሊቀሰቅሳቸውም ይገባል። በፓርላማችን ወንበርተኞች አናት ላይ ድምጹን አጥፍቶ እንደተኛው ደወል ከበላይ ያለው ሕዝብም ዝምታን መርጦ በአርምሞ መቀመጡ ድምጽ አያሰማም ማለት አይደለም። የሕዝብ ድምጽ እንደ እግዜር ድምጽ “ዝግባውን ይሰነጥቃል”። የሚጠራጠር ካለ መልእክተኛውን መብረቅ ማስታወስ ይቻላል። የሕዝብ ጎርፍ ከተነደለ መገደቢያም ሆነ መከተሪያ ዘዴ አይኖረውም። “እድል አንዴ፤ ጥፋት ሁለቴ” ይላል የአገሬ ብሂለኛ። ሰላም ይሁን።

# መፍትሔ የሚያሻው ፖለቲካል ኢኮኖሚ

**ፍሬሕይወት አወቀ**

በአገሪቱ ዕለት ዕለት እየተባባሰ የመጣውን የኑሮ ውድነት በተለይም ሰው ሠራሽ የዋጋ ንረትን መቆጣጠር እየተቻለ አይደለም። ዛሬ የታየው የዋጋ ጭማሪ ነገ ከነገ ወዲያ በእጥፍ ይጨምር እንደሆን እንጂ ሲወርድ አይስተዋልም። አሁን አሁንማ «ኢትዮጵያ ውስጥ ወጥቶ የሚወርደው ባንዲራ ብቻ ነው» በሚል ቀልድ አዘል ቁምነገር ሰው ምሬቱን ያጣቅስ ጀምሯል።

የኑሮ ውድነቱ ያልነካካው ዘርፍ የለም ቢባል ማጋነን አይሆንም። መሸቶ በነጋ ቁጥር ሁሉም ነገር በአንድ ቃል ጨመረ፣ ጨመረ፣ ጨመረ... ብቻ ሆኗል ቋንቋው። እዚህ አገር ውስጥ አንድ ምርት ከገበያ ከጠፋ ወይም እጥረት መከሰቱ በተሰማ ማግስት ዋጋው በእጥፍ መጨመሩም የማይቀር ጉዳይ ከሆነ ሰነባብቷል። ለዚህ ሁሉ ታድያ በአገሪቱ ያለው የንግድ ሥርዓት ጤናማ አለመሆኑና ደላሎች ዋነኛ ችግሮች ስለመሆናቸው ባለሙያዎች ደግመው ደጋግመው ሲያነሱ ይደመጣል።

ይሁንና ጤናማ አይደለም የተባለው የንግድ ሥርዓት ጤናማ በሆነ የንግድ ሥርዓት እንዲቃኝና እሳት ከማጥፋት ባለፈ ዘለቄታዊ መፍትሔ ለማምጣት የሚደረግ ጥረት እምብዛም አይስተዋልም። እርግጥ ነው የምርት እጥረት ለዋጋ ንረት መከሰት ዋነኛ ምክንያት ነው። ለዚህም መንግሥት የተለያዩ አማራጮችን በመውሰድ መፍትሔ ለማምጣት የተለያዩ ሥራዎችን ቢሠራም ትርጉም ያለው ለውጥ ግን አልመጣም።

በአሁን ወቅት አልቀመስ ያለውን የሲሚንቶ እና የብረት ገበያ ለአብነት ብናነሳ ገበያው ፍጹም ባለመረጋጋት ውስጥ ሆኖ እነሆ ዓመታት ነጉደዋል። የገበያው መረበሽም በተለያየ መልኩ ችግር እየፈጠረ ያለ ሲሆን በተለይም ብረትን ጨምሮ ሲሚንቶ በኮንስትራክሽን ዘርፍ ላይ እያደረሰ ያለው አሉታዊ ተጽዕኖ ቀላል ግምት የሚሰጠው አይደለም። በሲሚንቶ ገበያ ላይ የሚታየው ችግር ሲንከባለል የመጣ ቢሆንም ቅሉ በአሁን ወቅት ያለው የገበያ ችግር ካለፉት ጊዜያት በእጅጉ የተለየና የተጋነነ ለመሆኑ ብዙዎች ይስማማሉ።

የሲሚንቶ ዋጋ መናር ችግርን ለመቅረፍ መንግሥት በተለያዩ ጊዜያት ጥረት ያደረገ ቢሆንም፤ ዛሬም የሲሚንቶ ገበያ ሊረጋጋ አልቻለም። አንዴ ከፍ ሌላ ጊዜ ዝቅ እያለ ቀጥሏል። በዘርፉ የተሰማሩ አካላት እንደሚገልጹት በአሁኑ ወቅት ሲሚንቶ ከ800 እስከ 1000 ብር በመሸጥ ላይ ይገኛል። በዚህም ምክንያትም የኮንስትራክሽን ዘርፉ በከባድ ረብሻ ውስጥ ነው።

የምግብ ሸቀጦችንም ስናስብ የሚነሱት ችግሮች ተመሳሳይ ናቸው። ሰዎች በየዕለቱ በሚጨምረው የምግብ ሸቀጣ ሸቀጦች ዋጋ ናላው እየዞረ ቢሆንም ከየትኛውም አካል መፍትሔ የሚሆን ጠብ ያለ ነገር አልተገኘም። ሸማቹ በኑሮ ውድነት እየተፈተነ ባለበት በዚህ ወቅት እንኳን ሕገወጥ ነጋዴና ደላሎች የፈጠሩት ችግር ነው ከማለት ባለፈ የሸማቹን ልብ የሚያሳርፍ ነገር አልታየም።

በንግዱ ዘርፉ የተሰማሩ አካላት እንደሚሉት በአምራች እና በገዥ መካከል የሚንቀሳቀሱ ደላሎች የምርቶችን ዋጋ ከፍ እንዲል እያደረጉ ነው። ከአምራቾች ተረክበው መልሰው የሚሸጡ አየር በአየር ነጋዴዎች ለዋጋ ንረቱ አይነተኛ ሚና አላቸው።

የትኛውም ገበያ ጤናማ የሆነ የግብይት ሰንሰለትን መከተል ያልቻለው በሕገወጥ ደላሎች አማካኝነትና አየር በአየር ነጋዴዎች ቢሆንም መሠረታዊ የሚባሉ ችግሮች እንዳሉም ይታመናል። ማንኛውንም ምርት በስፋት ማምረት ካልተቻለ እጥረት መፈጠሩ የሚታመን ቢሆንም የተፈጠረውን እጥረትም እንደ መልካም አጋጣሚ በመጠቀም ከተፈጠረው እጥረት በላይ ገበያውን የሚረብሹ በርካታ የዘርፉ ተዋንያኖች አሉ።

መንግሥት በየዘርፉ ውስጥ ያለውን የገበያ ችግር ለመፍታት ከወሰዳቸው እርምጃዎች መካከል የሲሚንቶ ምርት አንዱ ነው። ሲሚንቶ አምራች ፋብሪካዎች የመሸጫ ዋጋቸውን እንዲቀንሱ፣ የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ብቻ ሲሚንቶ እንዲያከፋፍሉና ሌሎች እርምጃዎችንም ሲወስድ መቆየቱ ይታወሳል። ይሁን እንጂ ይህ መፍትሔ ጊዜያዊ እፎይታን ሰጥቶ አልፏል እንጂ በዘላቂነት በገበያው ውስጥ ያለውን ቁስል ግን ሊያሽረው አልቻለም።

የምግብ ሸቀጣ ሸቀጦች ላይም እንዲሁ ከታክስ ማግኘት የሚገባውን ገቢ አጥቶ የተመረጡ ምግቦችን ከቀረጥ ነጻ ሲያስገባ መቆየቱ ይታወሳል። ይሁንና መንግሥት አማራጭ ያላቸውን መንገዶች ሁሉ ነጋዴውን ይበልጥ ፈርጣማ ከማድረግ ባለፈ የሸማቹን ሸክም ሲያቀል አልታየምና ዛሬም ሸማቹ በኑሮ ውድነት እየተፈተነ ቀጥሏል።

ገበያውን ከማረጋጋት ባለፈ የንግድ ሥርዓቱ ጤናማ በሆነ መንገድ በሕግና በመመሪያ በዘላቂነት መቀጠል የሚችለው እንዴት ነው፤ በየጊዜው የሚፈጠረውና ከወጣ የማይወርደው የዋጋ ንረትን እንዴት መቆጣጠር ይቻል ይሆን፤ለዋጋ ንረት መባባስ ዋነኛ ምክንያት የሆነውን የምርት እጥረት እንዴት ማሻሻል እንደሚቻልና ሕገወጥ ስግብግብ ነጋዴና ደላሎችስ እስከመቼ ለችግሩ መባባስ ምክንያት ይሆናሉ ስንል ላነሳነው ጥያቄ የፖለቲካል ኢኮኖሚ ተንታኙ አቶ ሸዋፈራሁ ሽታሁን የሚከተለውን ብለዋል።

> እንደ ኢትዮጵያ ባሉ ታዳጊ አገራት ኢኮኖሚውን ከፖለቲካው ነጥሎ ብቻውን መተንተን አይቻልም። ኢኮኖሚውና ፖለቲካው የማይነጣጠሉና የጠበቀ ትስስር ያላቸው ናቸው። ለዚህም ምክንያቱ ባለፉት በርካታ ዓመታት ኢኮኖሚውን ቀስፎ የያዘው ፖለቲካው ነው። ስለዚህ ፖለቲካው ሲታመም ኢኮኖሚው ይታወካል። ፖለቲካው ሰላም ሲሆን በተመሳሳይ ኢኮኖሚው ይረጋጋል

እንደ ኢትዮጵያ ባሉ ታዳጊ አገራት ኢኮኖሚውን ከፖለቲካው ነጥሎ ብቻውን መተንተን አይቻልም። ኢኮኖሚውና ፖለቲካው የማይነጣጠሉና የጠበቀ ትስስር ያላቸው ናቸው። ለዚህም ምክንያቱ ባለፉት በርካታ ዓመታት ኢኮኖሚውን ቀስፎ የያዘው ፖለቲካው ነው። ስለዚህ ፖለቲካው ሲታመም ኢኮኖሚው ይታወካል። ፖለቲካው ሰላም ሲሆን በተመሳሳይ ኢኮኖሚው ይረጋጋል።

ፖለቲካል ኢኮኖሚ ማለት ሊህቃን የሚዘውሩትና እንዳሻቸው የሚያደርጉት ሀብት እንደማለት መሆኑን የጠቀሱት ተንታኙ፤ ይህን ፖለቲካል ኢኮኖሚ በመደበኛው አካሄድ ወደታች ለማውረድ ደግሞ ግፊት፣ ትግልና ሙግት እንደሚያስፈልግ ይናገራሉ። በተለይም በመንግሥት ሚዲያዎች ወቅታዊ ፖለቲካል ኢኮኖሚውን አስመልክቶ የመንግሥት አካላት ባሉበት ባለሙያዎች የመፍትሔ ሀሳብ ማቅረብ አለባቸው። መንግሥትም ከባለሙያዎች ለሚሰነዘሩ ሃሳብና አስተያየቶች ጆሮ ሰጥቶ ተግባራዊ ማድረግ ካልቻለ በተለመደው አካሄድ ብቻ መዳዝ ችግሩን ካለመፍታት ባለፈ በእጅጉ አድካሚ ነው።

ማንኛውንም ሥራ በእጃችን ላይ ያለውን ነገር ተጠቅመን ቅድሚያ ለሚሰጠው ቅድሚያ ሰጥተን ምርጡን ነገር መሥራት ትክክለኛነት ስለመሆኑ የ11ኛ ክፍል ኢኮኖሚክስ ያስተምራል የሚሉት ተንታኙ፤ ነገር ግን አሁን ላይ እየሆነ ያለው ከፈረሱ ጋሪው አይነት እሽቅድምድም ነው። በጦርነት ምክንያት ሚሊዮኖች ተፈናቅለውና ተርበው ባሉበት አገር በሌሎች ሥራዎች ላይ ማተኮር ፖለቲካል ኢኮኖሚውን ካለማወቅና ካለመረዳት የመጣ ነው በማለት ያስረዳሉ።

ስለዚህ በቅድሚያ እንዲህ አይነቱን ስህተት ማረምና ቅድሚያ መስጠት ለሚገባው ቅድሚያ መስጠት ከተቻለና መደማመጥ ካለ ችግሩን መቅረፍ ይቻላል። ለዚህም የፖለቲካ አመራሮች ዓላማቸውና ሥራቸው ምንድን ነው ብሎ መጠየቅ ያስፈልጋል። ሕዝቡ መኖር እስኪያቅተው ድረስ የኑሮ ውድነት ጠፍንጎ በያዘበት በዚህ ወቅት ባለስልጣናቱ እንቅልፍ ይወስዳቸዋል ወይ ብሎም መሞገት ተገቢነት ያለው ጥያቄ ስለመሆኑም ያነሳሉ።

ኢትዮጵያ ብዙ ሀብት ያላትና ከ80 በመቶ በላይ የሚሆነው ሕዝቧ አርሶ አደር ስለመሆኑ ያነሱት ተንታኙ፤ ከሰሞኑ ዘይት ጠፋ ተብሎ የበዛ ጫጫታ እንደነበር ያስታውሳሉ። ጫጫታው 80 በመቶ የሚሆነውን ገበሬ የሚወክል አይደለም። ኢትዮጵያን ሊወክላት የሚችለው ገበሬ ነው። «ዘይት ማባያ እንጂ ምግብ አይደለም» በማለት ከዘይት ይልቅ ጤፍ እንዳይጠፋ ገበሬው ጋር ያለውን ሥራ አድምቶ መሥራት ተገቢ እንደሆነና የሁላችንም ጫጫታ ኢትዮጵያን የሚመስል መሆን እንዳለበት አጽንኦት ሰጥተዋል።

እርግጥ ነው ገበያው በአንድም በሌላ እየተረበሸ ነው። መረበሹ ደግሞ ጤናማ አይደለምና መስተካከል እንዳለበት ይታመናል። ነገር ግን ለገበያው መረበሽ ምክንያቱ ደላላ እና ሕገወጥ ነጋዴ እንደሆነ ይነገራል እንዲህ አይነቱ ምላሽ እስከመቼ ለሚለው ጥያቄ ተንታኙ ሲመልሱ ደላላው እራሱ ማነው በማለት ጥያቄን በጥያቄ መልሰው ያነሳሉ። ከላይ እስከ ታች በዘር የተደራጁ አመራሮች ስለመኖራቸው በማንሳት በ2000 ዓ.ም አካባቢ በባለሃብቶች ኪስ ውስጥ የገቡ ከተሞችና ወረዳዎች የነበሩ ስለመሆናቸው ለአብነት ጠቅሰዋል።

እነዚህ ባለሃብቶች ከባለስልጣን ጋር በነበራቸው የጥቅም ትስስር የፈለጉትን ያህል መሬት የሚሰጣቸው እንደሆነና የመንግሥትን መዋቅር በኪሳቸው ውስጥ ያስገቡ ባለሃብቶች ስለመሆናቸው ጠቁመዋል። ባለፈው ሥርዓት የነበረው ብልሹ አሠራር አሁንም ያለ መሆኑን ሲያስረዱም በባለሃብቱና በሹማምንቱ መካከል የነበረው ያልተቀደሰ ጋብቻ አሁንም አልፈረሰም ውሸት ነው በማለት ደላላው ማን እንደሆነ ይጠቁማሉ።

በዚህ ምክንያት አሁንም ሕዝቡ ከገባበት የፍርሃት ቆፈን ያልወጣ እንደሆነና ከገባበት የፍርሃት ቆፈን መውጣት እንዳለበት ያስረዱት ተንታኙ፤ ዛሬም ሕዝቡ ስም ጠቅሶ ለመናገር እየፈራ ያለበት ጊዜ መሆኑንና ሸብቦ ከያዘው ቆፈን መውጣት እንዳለበት በማመን ችግሩ በመንግሥት መዋቅር ውስጥ ያለ ስለመሆኑን መፍትሔ ማምጣት እንደሚቻልም አስረድተዋል።

አገሪቱ አሁን ከገባችበት የፖለቲካል ኢኮኖሚ ትርምስ ውስጥ መውጣት የምትችለው በተለይም የተረበሸውን ገበያ ማስተካከል የሚቻለው እያንዳንዱ በመንግሥት መዋቅር ውስጥ ያለው አካል ግዴታውን መወጣት ሲችል ነው። ባለፈው ዓመት በወሎና ጎንደር አካባቢ የሚገኙ አርሶ አደሮች ያመረቱት ሽንኩርትና ቲማቲም ገዢ በማጣቱ እንደበሰበሰ መሰማቱን አስታውሰው ለዚህ ችግር በአካባቢው የሚገኘው የግብርና ጽሕፈት ቤት ተጠያቂ መሆን አለበት። ጽሕፈት ቤቱ ሚናው ምንድን ነበር በማለት መጠየቅም ይገባል።

ጽሕፈት ቤቱ በአካባቢው የሚገኘው አርሶ አደር ያመረተውን ምርት በማስተዋወቅ ነጋዴውም ሆነ ሸማቹ ምርቱን ከአርሶ አደሩ መግዛት እንዲችል ማድረግ ነበረበት። ነገር ግን ይህን እጅግ ቀላል የሆነውን ሥራ ባለመሥራቱ የአርሶ አደሩ ልፋት ከንቱ መቅረቱንና ሸማቹም በምርት እጥረት ምክንያት በሚያጋጥመው የዋጋ ንረት መሰቃየቱን አስረድተው በዚህ አጋጣሚ ደግሞ በመሐል ቤት ያለው ደላላ ተጠቃሚ ይሆናል።

እንዲህ አይነት ቀላል ተግባራትን በመከወን በቀጥታ ሸማቹ ምርቱን ከገበሬ መግዛት እንዲችል ማድረግ ቢቻል በመሐል ያለውን ደላላ ቆርጦ መጣል የሚቻል መሆኑን እንደ መፍትሔ አንድ ያስቀመጡት ተንታኙ የተለያዩ ቴክኖሎጂዎችን መጠቀምም እንዲሁ ሁለተኛው መፍትሔ ማምጣት ይቻላል።

ከቴክኖሎጂ ጋር በተያያዘም 20 በመቶ የሚሆን የአንድ አገር ሕዝብ የሞባይል ስልክ ተጠቃሚ ከሆነ ያ አገር አምባገነን የሆነ መንግሥትን ሊወጣበት ዕድል የሌለው ስለመሆኑ የግብጽን አብዮት በአብነት አንስተው በማኅበራዊ ሚዲያ የተቀጣጠለ ስለመሆኑ ተናግረዋል።

በርካታ ዕድሎች ባሉበት ዓለም አማራጮችን ተጠቅመን የተሻለ ፖለቲካል ኢኮኖሚን መገንባት ለምን አልቻልንም የሚለው ሊቆጨን ይገባል የሚሉት ተንታኙ፤ እነዚህንና መሰል ችግሮችን መፍታት የሚቻለው የመንግሥት ሹማምንቶች ከባለሙያዎች ጋር በጋራ ተቀምጠው መወያየት፣ መከራከርና ወደ መፍትሔ መምጣት ሲችሉ እንደሆነ ያምናሉ። በተለይም የኢኮኖሚ ባለሙያዎች ከአማካሪዎች ጋር በጠረጴዛ ዙሪያ ተቀምጠው በሚያደርጉት ክርክር የአገሪቱን ፖለቲካል ኢኮኖሚ ማስተካከል ይቻላል። መንግሥት ያልታየውን ነገር ከባለሙያዎች ጋር በሚያደርገው ውይይት ማየትና መረዳት ይችላል።

በአሁን ወቅት በአገሪቱ ለሚስተዋለው የኢኮኖሚ ችግር የኢኮኖሚ ባለሙያዎች የመፍትሔ አካል በመሆን የፖለቲካና ኢኮኖሚ መስተጋብር ምን መምሰል እንዳለበት ለመንግሥት ስዕሉን ማሳየት እንችላለን። ለዚህም የኢኮኖሚ ባለሙያዎችና በመንግሥት መዋቅር ውስጥ ያሉ ባለድርሻ አካላት የሚወያዩበት ዕድል ይፈጠር በማለት ሀሳባቸውን ቋጭተዋል።

# ማረፊያ/ትዝብት

## ብቅ ጥልቅ የሚለው የሸገር ባቡር

**ኃይለማርያም ወንድሙ**

ከዓድዋ ድል በኋላ በኢትዮጵያ ብዙ ለውጦች ታዩ። የኢትዮጵያ ስም በአውሮፓውያን በደማቅ ቀለም ተጻፈ። ብዙ ምዕራባውያን መንግሥታት ለአገሪቱ ዕውቅና ሰጡ። በአፍሪካ ቀዳሚ የሆነውን ቆንስላዎቻቸውን በአዲስ አበባ ከፈቱ።

ኢትዮጵያ ከውጪ አገር መንግሥታት የመሠረተችው ግንኙነት ብዙ የውጪ አገር ነጋዴዎችና ባለሙያዎችን ሳቡ፤ አገር ውስጥ አስገቡ።በዚህም አዳዲስ ነገሮች ገቡ።ከነዚህ ውስጥ የምድር ባቡርና መኪኖች ይጠቀሳሉ። በተወሰነ መልኩ ታላላቅ ባላባቶች ኤምባሲዎችና ንጉሡ መኪና ያስገቡ ሲሆን ፤ባቡሩም መስመሩ የተዘረጋው ከአዲስ አበባ ድሬዳዋ ጅቡቲ እንደነበር ይታወሳል። የመጀመሪያው ባቡር አዲስ አበባ የገባው የሰርኪስ ባቡር በሚል ይታወቃል።

ባቡሩን ያስመጣው ሙሴ ሰርኪስ የሚባል ሰው ነው።ባቡሩን በመርከብ አስጭኖ እስከ ጅቡቲ ካደረሰ በኋላ የባቡር መስመር ወይም ሀዲድ እስከተዘረጋበት ኢሳ ወረዳ ድረስ አስገባው፤ ይህም በ1896 መሆኑ ነው።ከዚያም በሐረርጌ ሕዝብ እያስገፋ እስከ አዋሽ ወንዝ አስመጣው።

የምንጃር ሰዎችም መንገዱን በመደልደል እና ባቡሩን በመግፋት አዲስ አበባ አደረሱት። ሙሴ ሰርኪስ በዘመኑ ባበሩን ወደፊትና ወደ ኋላ እየነዳ ለንጉሡና ለባላባቱ ለሕዝቡ አሳየ። እንግዲህ ወገን ያ የተጀመረው ባቡር አንዴ አለ ብለን ስንሰግርበት ሌላ ጊዜ እብስ ብሎ አገልግሎቱን ሲያቆም መቶ ዓመት ተሻግሯል። የድሮ ባቡር ሂደቱ መሰናከል የጀመረበት ቦታ ወይም ባቡሩ ተሰናክሎ የቆመበት ቦታ ሰባራ ባቡር ተብሎ ይጠራል ይላሉ።

ቦታው ከአቡነ ጴጥሮስ አደባባይ ወደ ቀድሞው ኢትዮጵያ ሬዲዮ (ወደ ዮሐንስ ቤተክርስቲያን) በሚወስደው መንገድ አቅራቢያ በሚገኘው ገዳም ሰፈር ነው። በወቅቱ ድምጽ የሚያሰሙ ነገሮች በጅምላ ባቡር ተብለው ይጠሩ ነበር። ወፍጮ ቤት በአማራና በኦሮሞ ባቡር ቤት ብሎ የመጥራት ልምድ አሁንም አለ። በአፋን ኦሮሞ « መነ ባቡረ ነንዴማ» ካሉ «ወፍጮ ቤት እሄዳለሁ» ይባል ነበር። አዝማሪም ባቡሩን አስመልክቶ ሲዘፍን

**ብነገርሽ ብነገርሽ አታጠናክሪ**

**እንደ ሰርኪስ ባቡር ተገትረሽ ቅሪ** ሲል አዚሞበታል።

ያኔ የባቡሩ መሰናከል ተመልክቶ ይሄ የባቡር በየጊዜው መሰናከል ዛሬም ድረስ ቀጥሏል። ዋንኛ ማንሳት የፈለግነው ጉዳይም የዛሬውን ነው። በዘመናችን ስላለው ስለሸገር የባቡር አገልግሎት። ሰባራ ባቡርን ያነሳነው ጨዋታ ጨዋታን ያነሳዋል ብለን ነው። ንጉሡ አዲስ አበባ ሳትቆረቆር በእንጦጦ ቤተ መንግሥት እያሉ ከጅቡቲ ሐረር ከሐረር እንጦጦ ከእንጦጦ በፋና ነጭ አባይ ድረስ የምድር ባቡር ለማሠራት አስበው እንደነበር የምድር ባቡር ውል ሰነዱ ያስረዳል።

ዛሬ ምንም እንኳን እስከ ነጭ አባይ ‹የሚጠልቅ› ባቡር ባይኖረንም፤ እስከ ጅቡቲ የሚዘልቅ የኤሌክትሪክ ባቡር መዘርጋት ችለናል።

በየአዲስ አበባው ከቻይና በተገዙ 41 ባቡሮች ነው ሥራውን የጀመረው። በመዲናችን ከአራዳ ጊዮርጊስ እስከ ቃሊቲና (16 ኪሎ ሜትር) ከጦር ኃይሎች እስከ አያት (17 ኪሎ ሜትር) ሕዝቡን ለማሳፈር ብቅ ጥልቅ የምትል ባቡር በሸገር አለችን። ይሄም ባቡር እንግዲህ አካሄዱን ሳጤነው እየተውዘገዘገ ሳይሆን እንደ ኤሊ እያዘገመ ነው።የዘንድሮው ባቡር እንደ ድሮው ሰባራ ባቡር ለመሆን አንድ ሐሙስ የቀረው ይመስላል።

የአዲስ አበባ ቀላል ባቡር ለመጀመር 475 ሚሊዮን የአሜሪካ ዶላር ወጪ ሆኗል። ባቡሩ በሸገር ስምሪት ሲጀምር በቀን ከ110 ሺህ እስከ 120 ሺህ ለሚሆን ሕዝብ የትራንስፖርት አገልግሎት ይሰጡ ነበር። አሁን ላይ ግን 70 ሺህ ለሚደርስ ለሸገር ተሳፋሪ በትራንስፖርት አገልግሎት እየሰጠ ነው። ከዚህ ባስ ብሎበት በተለያየ ምክንያት አገልግሎት የሚያቆምበትም ቀን በርክቷል። አሁንም አንዳንድ መስመሮች በኬብል ዘረፋና ሌሎች ምክንያች አገልግሎቱ ቆሟል።

አገልግሎት በሚሰጥባቸው አካባቢዎችም የተሳፋሪውን ቁጥርን ማሽቆልቆሉን ስታዩት ባቡሩ እያሳፈረን ነው ወይ ? ትላላችሁ። የሸገር ባቡር ችግር የጀመረው ገና አገልግሎቱን እንደጀመረ ነው። ደከመኝ ሰለቸኝ ሳይል ያገለግለናል ያልነው ባቡር በየቦታው እየተገተረ ወገቤን ማለት ጀመረ ውሎ አደረ።

ብዙ ይጓዛል ለአነስተኛ ገቢ ያለው ማኅበረሰባችን ጥሩ መፍትሔ ይዞ ቀረበ የትራንስፖርት ችግርም እጅጉን ቀረፈ ያልንለት ባቡር ደከመኝ፤ ሰለቸኝ አበዛ። እኛንም አስቸገረ።አንድፊቱን ተቸግሬ ነው የማስቸግራችሁ ብሎ ቁርጡን ይንገረንና እንደ ሰርኪስ ባቡር ሰባራ ልንለው ምንም አልቀረ።

መቼም ሸገርን ሰንገው ካያዟት መካከል አንዱ የትራንስፖርት ችግር ነው። የአዲስ አበባ ቀላል የባቡር አገልግሎት ይህን ችግር ይፈታል ቢባልም "ሕመምና እርጅና" እየተጫጫነው በየጊዜው ሲበላሽ፣ሲዘረፍና በልዩ ልዩ ምክንያች ሲስተጓጎል እናየዋለን። ስምሪቱን ሲጀምር የነበሩት ችግሮች ባቡሮች በየጊዜው በብልሽት እና በኃይል እጥረት ቆመዋል። እናም ወገኖቼ የሸገር ባቡር ሕዝቡን ለማሳፈር አይደለም ለራሱም ለመኖር እየተቸገረ ነው። ሰሞኑን እንኳ ስምሪት ላይ የለም። የከተማይቱ የትራንስፖርት ችግር ይፈታል፤ አይነተኛም መፍትሔ ይሆናል የተባለው ባቡር ከስምሪት ቆሞ እያሳፈረን ነው።

እኔ ምለው አገልግሎት ሰጪ ተቋሙ ባቡር ኮርፖሬሽን ምነው የንብረትና የአገልግሎቱ ጉዳይ መርምሮ መፍታት ያቃተው። ካቃተው ስለምን ችግሮቹን መፍታት አልቻልኩም ብሎ በአገር ደረጃ መፍትሔ እንዲበጅለት አያደርግ? አንዴ ተሰረኩ ሌላ ጊዜ የቴክኒክ ችግር እያሉ ከጊዜ ወደ ጊዜ ችግር ሳይፈቱ መክረም ያስተዛዝባል።ሌቦቹን እንዴት ከፀጥታ ተቋማት ጋር በመሆን ሠርቶ ሊያስቆም አይሞክርም፤ የቆሙትስ ባቡሮች መፍትሔ ፈልጎ መልሶ ወደ ሥራ ስለምን አያስገባቸውም?

አገልግሎት የጀመረ ጊዜ በየፌርማታው በየ10 ደቂቃው ይደርሳል የተባለለት የአዲስ አበባ ቀላል ባቡር ሲያሻው ተሳፋሪ እየጠበቀው ዘግቶ ሁሉ ያልፋል፤ ሲያሻው አስር ሰዓት ቆይቶ ይመጣል። ሲያሻው ለአንድ ለሁለት ቀን ስምሪት ያቆማል። በዚህ ዘገምተኛ አገልግሎቱ ቢያተርፍ እንገረም ነበረ፤ ከስሬያለሁ ሲል ግን ደጋግመን እንሰማዋለን። መሥራት ይገባዋል፤ደግሞ የሠራ ነው የሚያተርፈው።

ሲጀምሩ ቁጥራቸው ከነበረበት ዛሬ ላይ ቆመው አልፎ አልፎም ቢሆን ሲፈልጉ አገልግሎት የሚሰጡት ባቡሮች ጥቂት ናቸው ብዙዎቹ በብልሽት ምክንያት መሥራት ያቆሙ ናቸው። በጉዞ ላይ እያሉ በየጊዜው ወገቤን የሚሉ ባቡሮች ተበራከቱ፤ ተሳፋሪው አያስደስቱ ፤ በኑሮ መወደድ ለተማረረው ነዋሪም አንድ ችግር ሆኑ። የሸገር ባቡር የትራንስፖርት ችግር እናቃልላለን ብሎ በየቦታው እየቆመ በየምክንያቱ ተስተጓጎለ። የችግሮቹ መንስኤዎች የኃይል መቆራረጥ እና የመለዋወጫ ዕቃዎች እጥረት ሲባል የነበረ ቢሆንም አመራሮቹና ትራንስፖርት ቢሮ ችግሩን ለመፍታት ጥረት አለማድረጋቸውን ያሳየናል። ወይ ካልሆነ ከአየር መንገድ አመራሮችና ሠራተኞች ልምድ ቢቀስሙ ጥሩ ነው።

ሰሞኑን ደግሞ ይሄ ቀላል ባቡር ድርጅት በተደጋጋሚ እየገጠመው ባለው የኬብል ዘረፋ ከ18 ሚሊዮን ብር በላይ ኪሳራ እንደደረሰበት አረዳን። በዚህም ሳቢያ ለትራንስፖርት አገልግሎት መቆራረጥ አጋጠመኝ ይላል።ኬብሎቹ ደግሞ ባቡሩን ለማንቀሳቀስ፣ ለመቆጣጠርና ለመምራት የሚረዳ ነው። ባቡሩ መረጃውን ሲሰጥ የኃይል ማስተላለፊያ ኬብሎች ተደጋጋሚ ዘረፋ እየተባባሰ ነው ማለቱም ፖሊስ ሆይ ንቃ ያስብለናል።

18 ሚሊዮን ብር ኪሣራ ደረሰብኝ ብሎ መረጃ ከመስጠት መጀመሪያ ችግሩን ማስረዳት አይሻልም ነበር? ወይስ ስለባቡር ችግር ለመናገር 18 ሚሊዮን ብር ምናምን መዘረፍ አለበት? ይህ ሁሉ ብር እስኪዘርፍ ጠብቆ መረጃ መስጠት ምን ይባላል? ለነገሩ ኬብሉን ሲዘርፉ ነበሩ የተባሉ ተጠርጣሪዎች መያዛቸውን ሰሞኑን የአዲስ አበባ ፖሊስ በሰጠው መግለጫ አይቻለሁ፤ እነሱ ደግሞ በተከታታይ የሚሰጡት መረጃ የሚያሳየን ፍንጭ ይኖራል። ነገር ግን የአዲስ አበባ ቀላል ባቡር ትራንስፖርት ችግሮቹን የሚያቃልልበት ምንገድ ቢፈልግ መልካም ይመስለኛል። እንደ ተቋም ችግሮችን ለይቶ የሚጠበቅበትን ኃላፊነት መቀጣት እንዲችል መስራት ይገባዋልና ትኩረት ለባቡሩ ይሰጥ ብለናል።

# ዓለም አቀፍ

## በዘይት እጦት እየተንገፈገፉ ያሉት አልጄሪያውያን

በሰሜናዊቷ አፍሪካ አገር አልጄሪያ የምግብ ዋጋ በከፍተኛ ደረጃ እየጨመረ ሲሆን ለዚህም የአንበሳ ድርሻውን የያዘው በአገሪቱ የተከሰተው የዘይት እጥረት ነው።

በገበያ ውስጥ ያለው ዘይትና እና ወተት ምርቶች በጣም አናሳ በመሆኑ ምክንያት ሸማቾች በመደብሮች ውስጥ በሚገበዩበት ወቅት ነጋዴዎችን መለማመጥ እንዲሁም ማሞካሸት ይጠበቅባቸዋል።

የኮሮና ቫይረስ ወረርሽኝን ለመግታት ተጥለው የነበሩ መመሪያዎች እንዲሁም በቅርቡ የተከሰተው የዩክሬን ጦርነት ተደማምሮ እጥረቱን ያባባሰው ሲሆን ለሸማቾችም ሕይወትን ፈታኝ አድርጓታል።

"መድኃኒት የመግዛት አይነት ስሜት አለው" ትላለች የ31 ዓመቷ ሳሚሃ ሳመር በንዴትና በምጸት በተቀላቀለው ድምጸት።

ለቤተሰቦቿና ጓደኞቿ ኬክ መሥራት ትወድ የነበረችው ሳሚሃ በዚህም ገቢም ታገኝ ነበር በአሁኑ ወቅት ግን ለኬክ የሚያስፈልጉ ግብዓቶችን ማግኘት አልቻለችም።

"ከየትኛውም መደብር ዘይት ለመግዛት የሱቁ ባለቤት ጋር ወዳጅነት ወይም ትውውቅ መኖር አለበት" በማለት ሁኔታውን ታስረዳለች።

የግብይይት ሁኔታውም የሚከናወነው ሚስጢራዊ በሆነ ሁኔታ ነው። ዘይት እንደማንኛውም እቃ መደብሩ መደርደሪያ ፊት ለፊት ላይ አይታይም፤ ሻጮች መደብሮች ውስጥ ደብቀው ነው የሚያስቀምጡት።

እንደ በርካታ አልጄሪያውያን የኮሮና ቫይረስ መመሪያዎች ከፍተኛ ጫና ሲያደርሱና በርካታ ነገሮችን ሲቀይሩ የተመለከተችው ባለፈው ዓመት ነበር።

የሙስሊሞች ረመዳን ፆም ሊጀምር በተቃረበበት በአሁኑ ወቅትና ቅዱስ ወር ተብሎ በሚጠራው በዚህ ወር ለሚሠሩ የተለያዩ ዓይነት ምግቦች ግብዓት የሚሆነውን ዘይት ለመሸመት ነዋሪዎች ፍለጋቸውን አጠናክረው ቀጥለዋል።



ሳሚሃ አንዳንድ ጊዜ ፍራፍሬ እና አትክልቶችን ለመግዛትም ከምትኖርበት ከተማ ቢልዳ ረከስ ወዳለባትና ወደ አቅራቢያዋ ወደምትገኘው ኮሊያ ሄዳ መሸመት ይኖርባታል።

ሌሎች የምግብ ሸቀጦችም እንዲሁ ዋጋቸው ንሯል። ለምሳሌ ድንችን ብንወስድ ከጥቂት ወራት በፊት ከነበረው ከ30 በመቶ በበለጠ አሻቅቧል። ወተት ለመግዛት ነዋሪዎች ፀሐይ ከመውጣቷ በፊት ወደ መደብሮች በማቅናት ረጅም ወረፋ መጠበቅ ይኖርባቸዋል።

"ወተት ለማግኘት የተሰለፉ ሰዎችን መግፋት አንዳንዴም መጣላት ስለሚያጋጥም አሁን አቁሜያለሁ" በማለት የአስተዳደሩ ጸሐፊ ይናገራሉ። "በጣም የሚያዋርድ ተግባር ነው " የሚሉት ጸሐፊዋ እነዚህን ሰልፎች መራቅ ግን ዋጋ አስከፍሏቸዋል።

ከሕዝብ ጋር እየተገፋፉና ረጅም ወረፋ መጠበቅንም በመተው ከውጭ አገር ለሚገባ አንድ ኪሎ የዱቄት ወተት 2.90 ዶላር አካባቢ መክፈል ይጠበቅባቸዋል። በመንግሥት ድጎማ የሚደረግለት ወተት ዋጋ 17 ሳንቲም ዶላር ነው።

አልጄሪያ ወተት ብታመርትም ነገር ግን መጠኑ በጣም አናሳ ነው። ለዓመታትም ከፈረንሳይ፣ ከሌሎች የአውሮፓ ሕብረት አገራት እንዲሁም በቅርብ ጊዜ ከተባበሩት አረብ ኤምሬቶች በሚመጣ ወተት ጥገኛ ናት። የሚገባው ወተት በዱቄት መልክ ሲሆን ለሸማቾች ከመድረሱ በፊት ፋብሪካዎች ወደ ፈሳሽነት ይቀይሩታል።

ወተት እጥረት ቢኖርም በርካታ አልጄሪያውያንን እያስጨነቀ ያለው የዘይት ዋጋ መናር ነው።

እንደ ወተት ዘይትም ቢሆን በመንግሥት ድጎማ ቢደረግለትም በቅርቡ ከተከሰተው ቀውስ በፊትም ቢሆን ውድ ነበር። በዚያን ጊዜም የአምስት ሊትር ዘይት ዋጋ 4.20 ዶላር ወይም 216 ብር ነበር።

የአልጄሪያውያን ወርሐዊ ደመወዝ በአማካይ በግሉ ዘርፍ 240 ዶላር እንዲሁም የመንግሥት ሠራተኞች ደግሞ 410 ዶላር ሲሆን ባለስልጣናቱም በናረው የሸቀጥ ዋጋ ላይ እርምጃ እንዲወስዱ ጫና ቢፈጠርባቸው ብዙም አያስገርምም።

በአገሪቷ ኢኮኖሚ ሳቢያ ምግብ ማከማቸት እንዲሁም ሙስና በከፍተኛ ሁኔታ ማንሰራራቱን የፓርላማው ኮሚቴ በሪፖርቱ ይፋ አድርጓል።

በፓርላማው የተመረጠው ኮሚቴ አባል የሆኑት ሂሻም ሳፋር ለቢቢሲ እንደተናገሩት የዘይት ነጋዴዎች ከመንግሥት ተጨማሪ ገንዘብን ለመጠየቅ በሚል ድጎማ የተደረገለት ዘይት ላይ ሰው ሰራሽ የሆነ የዋጋ ንረት እየፈጠሩ ይገኛሉ።

ባለፈው ዓመት ወደ 150 ሺህ የሚጠጉ ጥሰቶች ለባለስልጣናቱ ሪፖርት የተደረጉ ሲሆን አብዛኞች ፍርድ ቤት ቀርበዋል እንዲሁም በሺዎች የሚቆጠሩ የንግድ ፈቃዶች ተነጥቀዋል።

ከዚህም ጋር በተያያዘ በአገሪቷ ድጎማ የተደረገላቸው ሸቀጦች በደቡባዊ ድንበር አቋርጦ በጎረቤት አገራት በሕገወጥ መንገዶች እየተሸጡ ይገኛሉ። ይህም መጠነ ሰፊ እንደሆነ የፓርላማ ኮሚሽኑ መጠነ ሰፊ እንደሆነም አመልክቷል።

ምንም እንኳን ይፋ የሆነ አኃዝ ባይኖርም ምንጮች ለቢቢሲ እንደተናገሩት 12 የሚሆን የጭነት መኪና ዘይት ወደ ማሊና ኒጀር በድብቅ ይወሰዳል።

ሕገወጥ ነጋዴዎቹ በመንግሥት ድጎማ የተደረገለትን ዘይት በመቸብቸብ በአንድ ጭነት መኪና እስከ 17 ሺህ 800 ዶላር ትርፍ እንደሚያገኙም ምንጮቹ ለቢቢሲ ተናግረዋል።

በዚህ ወር መጀመሪያ ላይ ፕሬዚዳንት አብደልማጂድ ቴቡኔ ከውጭ የመጡ ምርቶች ወይም ግብዓታቸው ከውጭ የመጣ እንደ ዘይት፣ ስኳር፣ ፓስታ፣ ሰሞሊና እና የስንዴ ምርቶች ወደ ውጭ እንዳይላኩ አግደዋል።

ሪፖርቶች እንደሚጠቁሙት ፕሬዚዳንቱ መሰል ድርጊቶች ሆን ብሎ የአገሪቱ ምጣኔን ሆን ብሎ ለማደናቀፍ የተሸረበ ሴራ ስለሆነ ከፍተኛ ቅጣት እንዲጣልባቸው ይፈልጋሉ።

ነገር ግን በአልጄሪያ ለተነሳው ቀውስ ጥልቅ መንስኤዎችን ለማወቅ ወደ ኋላ መለስ ብሎ መመልከት እንደሚያስፈልግ ባለሙያዎች ይናገራሉ።

**ምንጭ ቢቢሲ**

# ባለውለታዎቻችን

## ተሰማ እሸቴ - ባለብዙ ሙያው የአገር ባለውለታ

**አንተነህ ቸሬ**

ምዕራባውያን የብዙ ሙያዎችና ተሰጥኦዎች ባለቤት የሆነን ግለሰብ ለመግለፅ «A Jack of All Trades» የሚል አገላለፅ ይጠቀማሉ። «ለዚህ አገላለፅ ተገቢ (እውነተኛ ምሳሌ) የሆነ ኢትዮጵያዊ ማነው?» ተብሎ ቢጠየቅ ነጋድራስ ተሰማ እሸቴ አንዱና ዋነኛው ስለመሆናቸው ብዙም ክርክር የሚያስፈልገው ጉዳይ አይደለም።

ስመጥር አዝማሪ፣ ባለቅኔ፣ ቀራቂ፣ ሰዓሊ፣ ነጋዴ፣ መኪና አሽከርካሪ፣ መካኒክ፣ ፖለቲከኛ፣ ፎቶ አንሺ ... የነበሩት ነጋድራስ ተሰማ እሸቴ፤ የበርካታ ሙያዎችና ተሰጥኦዎች ባለቤት ሆነው ሳለ የአበርክቷቸውን ያህል ግን ታዋቂነትና ውለታ አላገኙም። ብዙ ነገር የተነፈጋቸው ሰው ናቸው።

ነጋድራስ ተሰማ ከአባታቸው ከአቶ እሸቴ ጉቤ እና ከእናታቸው ከወይዘሮ ወለተየስ ሐብቱ ሐምሌ 20 ቀን 1869 ዓ.ም ምንጃር ውስጥ ቀርሾ አጥር በተባለ ስፍራ ተወለዱ። አባታቸው አቶ እሸቴ ጉቤ በመሰንቆ ተጫዋችነታቸው ተወዳጅነትን ያተረፉ አዝማሪና የራስ መኮንን ባለሟል ነበሩ። ራስ መኮንን ወደ ሐረር በዘመቱበት ወቅት እርሳቸውን ተከትለው ወደሐረር የዘመቱት አቶ እሸቴ፤ ኑሯቸውን በዚያው በሐረር አድርገው ሳለ ሕይወታቸው አለፈ።

የአባቱን ማረፍ ተከትሎ ወደ አዲስ አበባ የመጣው ታዳጊው ተሰማ፣ ገና በልጅነታቸው በስዕል ችሎታቸው ተደናቂ መሆን ቻሉ። ለሙዚቃም የተለየ ፍቅር ነበራቸው። ይህ የሙዚቃ ፍቅር ያደረባቸው ከአባታቸው ወርሰውት ሳይሆን እንደማይቀር ይገመታል። በችሎታውም በወቅቱ አዲስ አበባ ውስጥ የነበሩ የአውሮፓውያንን ጭምር ቀልብ ለመግዛት ብዙም አልተቸገረም።

ሙሴ አርኖልድ ሆልስ የተባለ ጀርመናዊ በአዲስ አበባ የነበረውን ቆይታ ጨርሶ ወደ አገሩ ለመመለስ ለስንብት ወደ ዳግማዊ አፄ ምኒልክ ዘንድ ሲቀርብ ለንጉሡ ነገሥቱ አንድ ጥያቄ አቀረበላቸው። ሦስት ኢትዮጵያውያን ወጣቶችን ወደ ጀርመን ወስዶ በማስተማር ወደ ኢትዮጵያ ሊመልሳቸው እንደሚፈልግ ተናገረ። ንጉሠ ነገሥቱም ተሰማን በጥሩ ሰዓሊነቱና ቀራፂነቱ ያመሰግኑት ነበርና «ያ ተሰማ እሸቴ እጁ ብልህ ስለሆነ መኪና መንዳትና መጠገን እንዲማር እርሱም ይሂድ» ብለው ከሦስቱ ወጣቶች መካከል አንዱ ተሰማ እሸቴ እንዲሆኑ ፈቀዱ። ወደ ጀርመን ሄደውም ለሁለት ዓመታት ያህል የአውቶሞቢልን አሠራር (መኪና መንዳትና መጠገን) አጥንተው ተመለሱ።

በጀርመን ቆይታቸው በንጉሡ ነገሥቱ ከተፈቀደላቸው ትምህርት በተጨማሪ በራሳቸው ተነሳሽነት «ሂስ ማስተር ቮይስ» ከሚባለው ኩባንያ ጋር በመዋዋል 17 የዘለሰኛና የመዲና ዘፈኖቻቸውን በሸክላ ላይ አስቀርፀዋል። ይህም ሙዚቃን በሸክላ ላይ ያስቀረጹ የመጀመሪያው ኢትዮጵያዊ እንዲሆኑ አስቻላቸው። ሁለቱ ሙዚቃዎቻቸው በግዕዝ ቋንቋ የተሰሩ ነበሩ። በሙዚቃ ሥራዎቻቸው ግጥሞች ላይ ያነሷቸው ጉዳዮች ሰውየው በወቅቱ የነበራቸው የዕይታ አድማስ ሰፊ እንደነበር የሚያመለክቱ ናቸው።

በግጥሞቻቸው ላይም በጊዜው በኢትዮጵያ ስለነበረው ፖለቲካዊ ሁኔታ በድፍረት አመልክተዋል። እቴጌ ጣይቱንና የወቅቱን ታላላቅ መኳንንት ጭምር ወቅሰዋል፤አስጠንቅቀዋል፤መክረዋል። ሥራዎቻቸውን ላስቀረፁበትም 17ሺ የጀርመን ማርክ ተከፍሏቸዋል። ከዚያ በፊት ዘፈኖችና የአዝማሪዎች ሥራዎች የሚደመጡት በግራማ ፎን ነበር። ሌሎች ዘፋኞች ዘፈኖቻቸውን በዲስክ ማስቀረፅ እስከቻሉበት እስከ 1925 ዓ.ም. ድረስ ለ20 ዓመታት ያህል በአዲስ አበባና በሌሎች ትልልቅ የኢትዮጵያ ከተሞች ይደመጡ የነበሩት የነጋድራስ ተሰማ እሸቴ ሥራዎች ብቻ እንደነበሩ ታሪካቸው ያስረዳል።

ከጀርመን እንደተመለሱም የቤተ-መንግሥት መኪናዎች ኃላፊ ሆኑ። ኢትዮጵያውያን የመኪና አሽከርካሪዎችንም አሰለጠኑ። በዚህ ሙያቸውም ከፍተኛ ተወዳጅነትንም አተረፉ። ባሳዩት የስራ ትጋት የአዲስ አበባ ፍል ውሀ ድርጅትን እንዲመሩ ተሾሙ። የራስ ካሣን እህት ወይዘሮ ፀሐይወርቅ አንዳርጌን አገቡ። ከወይዘሮ ፀሐይወርቅ ጋር የነበራቸው ትዳር ሊሰምር ባለመቻሉ ወይዘሮ ሙላቷ ገብረሥላሴን አገቡ። ከትዳራቸውም ሰባት ልጆችን አፍርተዋል።

ከልጆቻቸው መካከል አንዱ «የአፍሪካ እግር ኳስ አባት» በመባል የሚታወቁት ታዋቂው የስፖርት ሰው አቶ ይደነቃቸው ተሰማ ናቸው። ልጆቻቸውንም ዘመናዊ ትምህርት እንዲማሩ አድርገዋል። ቁጥራቸው በርከት ያሉ ታክሲዎችን ከውጭ በማስመጣትና የሕዝብ ትራንስፖርት በማቋቋም በርካታ ኢትዮጵያውያን ሹፌሮችን አሰልጥነዋል።

ነጋድራስ ተሰማ እሸቴ ከሙዚቃ ችሎታቸው በተጨማሪ በግጥም ችሎታቸውም እጅግ የተደነቁ ነበሩ። ብዙዎቹ ግጥሞቻቸው የሰምና ወርቅ ፍችዎች ያሏቸው፣ የሚያስተላልፉት መልዕክት ጠንካራ እና በአፃፃፍ ቴክኒካቸው የተዋጠላቸው ናቸው። በወቅታዊ ማኅበራዊና ፖለቲካዊ ጉዳዮች ላይ የተመሠረቱም ሲሆኑ፤ የተችነት ባህርይም ይንፀባረቅባቸዋል። ቀጥለው የተጠቀሱት ሶስት ምሣሌዎች የነጋድራስ ተሰማን የግጥም ርዕሰ-ጉዳዮችና የግጥሞቹን ደረጃዎች ሊያመለክቱ ይችላሉ።

**« የአገሬ ወንዞች መጥኔውን ይስጣችሁ፣**
**ክረምት ሲመጣ እየጨነቃችሁ፣**
**ዋጋ አትቀበሉ አስታዋሽ የላችሁ፣**
**ከአዳም ጀምሮ እስከአሁን እድሜያችሁ፣**
**ሰውንም ከብቱንም እቃ እንዳጋዛችሁ፣**
**የማትታመኑ በዋል ፈሰስ ናችሁ፣**
**ለውቅያኖስ ዓሣ እያስረከባችሁ፣**
**አንድ እንኳ አታመጡ ወዲህ መልሳችሁ።**

***

**አገሬ ታውቂያለሽ እንደምንወድሽ፣**
**በታመምሽ ጊዜ ተዘግቶ ጆሮሽ፣**
**በነፃነት ፀጋ እስክትፈወሺ፣**
**በአራቱ ማዕዘን ዓለም ሲጠራሽ፣**
**ያምላክ ውለታ ምነው ማጥፋትሽ፣**
**አትናገሪም ወይ ተሰማ ብለሽ?**

***

**የወዲያ ሰዎች ክፋታቸው፣**
**ሬሳ አጋድመው መብላታቸው፣**
**የሸዋ ሰው መልካም፣**
**ወዳጁን ሳይቀብር አይበላም። »**

ነጋድራስ ተሰማ እሸቴ በዳግማዊ አፄ ምኒልክ፣ በልጅ ኢያሱ፣ በንግሥት ዘውዲቱና በቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ዘመነ መንግሥታት ሲኖሩ በበርካታ ሙያዎቻው የሚታወቁትን ያህል በቀልድ አዋቂነታቸውም የተደነቁ ነበሩ። ነጋድራስ ተሰማ እሸቴን በቅርብ እናውቃለን የሚሉ ወገኖች ከወቅታዊ ሁኔታ በመነሳት የሚያመነጯቸው ቀልዶች ከአለቃ ገብረሃና ቀልዶች ጋር ተመሳሳይነት እንዳላቸው ሲናገሩ ይስተዋላል። ነጋድራስ ተሰማ በሕይወት ዘመናቸው ከቀለዷቸው አሽሙሮች መካከል ሁለቱን ቀጥሎ እንመልከታቸውና ምላተ-ጉድለታቸውን እንመርምር።

ሀ) ነጋድራስ ተሰማ በአንድ ወቅት ከመኳንንቱ ጋር ቁጭ ብለው ሲጫወቱ «አሁን ሁላችሁም በሆዳችሁ የምታስቡትን አውቃለሁ» በማለት ተናገሩ። መኳንንቱም «አያውቁም» ሲሉ ተከራከሯቸው። ከመኳንንቱ አንዱ «አያውቁም» ብለው በመቶ ብር ተወራረዷቸው። እርሳቸውም «ሁላችሁም ለንጉሡ ነው የምታስቡት። በሆዳችሁ ያለው ይህ ነው» ብለው ተናገሩ። በዚህ ጊዜ ደፍሮ «አይደለም» ብሎ የሚከራከር በመጥፋቱ ውርርዱን ረቱ።

ለ) በአንድ ወቅት ደግሞ ንጉሠ ነገሥቱ ባሉበት የኢላማ ተኩስ ሲደረግ እልፍኝ አስከልካዩ በመጀመሪያ ጥይት ተኩሶ ዒላማውን መታ። በዚህ ጊዜ ነጋድራስ ተሰማ ቀስ ብለው «ባንዴ ቡን አደረጋት!» ሲሉ ተናገሩ። የእልፍኝ አስከልካዩ በፋሺስት ኢጣሊያ የወረራ ዓመታት ባንዳ ስለነበር ያንን በአሽሙር ለመንካት ሲሉ የተናገሩት ጣምራ ትርጉም ያለው ንግግር ነበር።

ነጋድራስ ተሰማ እሸቴ በኢትዮጵያ ባልተለመደ መልኩ ሃሳብን በነፃ መግለፅና መንግሥታትንና መሪዎችን በመተቸት ባህርያቸው ነበር።

**« ባለስልጣኖቹ እስኪ አስቡበት፣**
**መናገራችሁን እንዳትተውት ።»** ብለው የገጠሙት የዚሁ ማሳያ ነው።

ነጋድራስ ተሰማ እሸቴ በልጅ ኢያሱ ዘመን ጉልህ ፖለቲካዊ ተሣትፎ ነበራቸው። ለልጅ ኢያሱም የተለየ አክብሮት ነበራቸው። በልጅ ኢያሱ የአስተዳደር ዘመንም ሰይድ ባዝራ ከተባለ ግለሰብ ጋር በመሆን ከብት ወደ ውጭ አገራት ይልኩና ወደአገር ውስጥ ደግሞ ፈቃድ ጠይቀው የጦር መሳሪያ ያስመጡ ነበር።

አብዛኛው በአዲስ አበባ ከተማ የነበረው የመሐል አገሩ መኳንንት ልጅ ኢያሱን ከሥልጣን ለማውረድ በተሰለፈ ጊዜ ሁሉ ነጋድራስ ተሰማ ግን የልጅ ኢያሱ ታማኝ ባለሟል ሆነው እስከ መጨረሻው ድረስ ዘለቀዋል። ልጅ ኢያሱ ከዙፋን ሲወርዱም የልጅ ኢያሱ ወዳጆችና ደጋፊዎች ለግዞትና ለእንግልት ተዳረጉ። ነጋድራስ ተሰማም ጅማ ውስጥ በግዞት ተቀምጠው ቆዩ። ከልጆቻቸው መካከል አራቱ የተወለዱት በግዞት ላይ ሳሉ ነው። ነጋድራስ ተሰማ በአባ ጅፋር ግቢ ለሰባት ዓመታት ቆይተው ወደ አዲስ አበባ ተመለሱ።

**« አታበሉኝም ወይ ከጨማው ቆርጣችሁ፣**
**አታጠጡኝም ወይ ከጥሩ ጠጃችሁ፣**
**ሰባት ዓመት ሙሉ ተስፋሁሳችሁ።»** ብለው ስሜታቸውን ገለፁ።

ከግዞት በተጨማሪም ብዙ ንብረቶቻቸው ተወርሰውባቸው ነበር። ሳይወረስ የቀረው አዲስ አበባ ከተማ ራስ መኮንን ድልድይ (ፒያሳ አካባቢ) የሚገኘው ቤታቸው ብቻ ነበር። በጉምሩክ መሥሪያ ቤትና በአንድ ግሪካዊ ነጋዴ ቤት ያስቀመጡት 300ሺ ብር የሚያወጣ ጠበንጃና ጥይትም ሳይመለስላቸው ቀረ።

የማይጨው ዘመቻ እንደተጀመረ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ አፄ ኃይለሥላሴ ወደ ዘመቻው ከማምራታቸው በፊት የልጅ ኢያሱ ደጋፊዎች ዝም ብለው አይቀመጡም ብለው በማሰብ ከአዲስ አበባ ያርቋቸው ጀመር። ነጋድራስ ተሰማም በነጋድራስነት ሹመት ሰበብ ወደ ወላይታ ግዛት እንዲርቁ ተደረገ። በዚህ ወቅትም፣ የጠላት ወረራ የፈጠረው የብጥብጥ ስሜት በግዛቱ ውስጥ የእርስ በእርስ ግጭት እንዳያስነሳ የፀጥታ ኃይል አቋቁመው ሕግና ሥርዓት እንዲጠበቅ አድርገዋል።

የፋሺስት ኢጣሊያ አስተዳደር ከንጉሠ ነገሥቱ ጋር የተጣሉ ሰዎችን ሰብስቦ አክብሮት መለገስ ጀምሮ ስለነበር ነጋድራስ ተሰማም የተወረሰው ቤታቸው ተመለሰላቸው። ቤታቸውን አከራዩት። ይሁን እንጂ ቤታቸውን የተከራዩት ጣሊያኖች ለነጮች እንጂ ለጥቁሮች ቦታ ስላልነበራቸው ነጋድራስ ተሰማ ከዕለታት አንድ ቀን ምግብ ለመብላት ወደአከራዩት የራሳቸው ቤት ሲገቡ በጥቁርነታቸው መገለል ደረሰባቸው። ቀደም ሲል ወደ ወላይታ እንዲርቁ መደረጋቸውና አሁን ደግሞ በጥቁርነታቸው ምክንያት የደረሰባቸው አድልኦ ያበሳጫቸው ነጋድራስ ተሰማ እንዲህ ብለው ተቀኙ።

**« ታሪኬ ብዙ ተሰማ እሸቴ፣**
**ተደብቄያለሁ በገዛ ቤቴ ።»**

ወደ ፋሺስት አስተዳደር አለቃው ማርሻል ሩዶልፎ ግራዚያኒ ሄደው «ልናሰለጥናችሁ መጣን ብላችሁ የዘር ልዩነት ልትመሠርቱና ከሰው በታች ልታደርጉን ነው?» ብለው ጠየቋቸው። ግራዚያኒም «አዝናለሁ፤ ከሙሶሊኒ የመጣ ትዕዛዝ ነው» ብለው መለሰውላቸዋል። ነጋድራስ ተሰማ በነገር የሚሸነቁጡት ምዕራባውያንንም ጭምር ነበርና

**« የሰላም አለቆች እንግሊዝ ፈረንሳይ፣**
**እግዜር እንዳይገድለኝ የእናንተን ጉድ ሳላይ »**
በማለት እንግሊዝና ፈረንሳይ በወቅቱ በኢትዮጵያ ላይ ይሸርቡት የነበረውን ሴራ ጠቁመዋል።

ፋሺስት ኢጣሊያ ተሸንፎ ንጉሠ ነገሥቱ አዲስ አበባ ሲገቡ ነጋድራስ ተሰማ «ከፋሺስት ኢጣሊያ ጋር ተባብረው መሥራታቸውን እናውቃለን» የሚሉ ከሳሾች በዙና ወሊሶ አካባቢ ለስድስት ዓመታት በግዞት እንዲቆዩ ተደረገ። ይሁን እንጂ ፋሺስት ኢጣሊያ በሰሜን ሸዋ አካባቢ ከሚንቀሳቀሱት አርበኞች ከነራስ አበበ አረጋይ ጋር እንዲያስታርቁት ሽምግልና ልኳቸው ነበር። ነገር ግን አርበኛውን የሚጠቅምና ጠላትን የሚጐዳ ድርድር አድርገው መመለሳቸው ስለታወቀ ለተወሰነ ጊዜ ችግር አጋጥሟቸው ነበር። ነጋድራስ ተሰማ እሸቴ ፋሺስት ኢጣሊያንን የሚቃወሙና የሚተቹ ብዙ ግጥሞችን ገጥመዋል።

**« እገበያ መሀል ፈስ እያንዛረጡ፣**
**አውራ ጐዳና ሳይ ዳቦ እየገመጡ፣**
**ቤተ-ክርስቲያን ውስጥ ትምባሆ እየጠጡ፣**
**እንዲህ ነው ወይ ጣልያን አልጋ ላይ ሲወጡ »**
ብለው ነበር።

የጣሊያንን ክፋትና አደገኛነት ለኅብረተሰቡ ለማሳወቅና በጀግንነት እንዲመክተው ለማድረግም ይህን ብለዋል።

**« እናንት ገበሬዎች በፊት ተማከሩ**
**አረማሞ እንክርዳድ ሲናር እንዳትዘሩ**
**ገና በሸፍኑ ፍሬ ሳያፈራ ጨፍጭፎ ቆራርጦ**
**መጣል ነው ለአሞራ።**
**ይህን የመጥፎ ዘር የባህር ማሽላ**
**ነቃቅሎ ማጥፋት ነው መቼም አይበላ።»**



ከግዞት እንደተፈቱም የሻሸመኔ የእንጨት ፋብሪካና የቲማቲም ድልህ ፋብሪካ ዳይሬክተር ሆነው ተሾሙ። በወንጂ ስኳር ፋብሪካ ሸንኮራ አገዳ መትከል የጀመሩት እርሳቸው ነበሩ። አገራቸው በግብርና ዘርፍ ታዋቂ እንድትሆንና የውጭ አገራት ጎብኚዎችን ዓይን እንድትስብም ጥረት ያደርጉ ነበር። በሶደሬ፣ በወንጂ፣ በወሊሶ ፍልውሃና በቦኮ እንፋሎት ላይ ያከናወኗቸው ተግባራት ለዚህ ምስክሮች ናቸው። በቱሪዝም ረገድ ለአገራቸው የነበራቸውን ስሜትም በዚህ ስንኝ ገልጸውታል።

**« ከዓባይ ኢንዱስትሪ ከአዶላም ከወርቁ፣**
**ከዋቢ ሸበሌም አትክልቶች ሲፀድቁ፣**
**የዓለም ቱሪስቶች እኛን እንዲያደንቁ፣**
**ደስም እንዲላቸው ሲመጡ ከሩቁ።**
**ይህ ነው የኔ ምኞት ጥንትም ሆነ ዛሬ፣**
**እንዲህ ሆና እንዳያት ኢትዮጵያ አገሬ።»**

የኢትዮጵያ ሕዝብ የኑሮ ሁኔታ እንዲሻሻል አጥብቀው ይጥሩ እንደነበር የሚነገርላቸው ነጋድራስ ተሰማ እሸቴ፣ በየጊዜው አዳዲስ ሃሳቦችን በማፍለቅ እርሻና ኢንዱስትሪ እንዲስፋፋ ለንጉሠ ነገሥቱ ሃሳብ እያቀረቡ የውሀ ግድቦችና ሰፋፊ እርሻዎች እንዲሠሩ አድርገዋል። በፍል ውሃ ድርጅት ዳይሬክተርነትና በፖስታ ሚኒስትርነትም አገልግለዋል። የሕዝብን መንፈስ የሚያዳክሙ ነገሮችን በፅኑ ይቃወሙ ስለነበር ከልክ ያለፈ የመጠጥ፣ የትምባሆና የጫት ተጠቃሚነት አመል እንዲጠፋ በምሳሌነትም ሆነ በምክር ከፍ ያለ ትግል አድርገዋል። የእርሳቸውም አመጋገባቸውና የመጠጥ አወሳሰዳቸው በጥብቅ ፕሮግራምና ስርዓት ይከናወን እንደነበር ታሪካቸው ያስረዳል።

ከመንግሥታዊ አገልግሎታቸው በተጨማሪም፣ በተለያዩ ጊዜያት ከግሪካውያን ጋር በመሆን የሸክላ ጣሪያ በማምረትና በእርሻ ስራ ላይ ተሰማርተው እንደነበር ታሪካቸው ያስረዳል። ማኅበራዊ ኃላፊነታቸውን ለመወጣት አዲስ አበባ ከተማ ራስ መኮንን ድልድይ አካባቢ አለቃ ነገደ እስራኤል የተባሉ መምህር ቀጥረው ከመንደሩ ለተውጣጡ ልጆች ነፃ የአማርኛ ትምህርት እንዲሰጥ አድርገዋል።

ሎሬት ጸጋዬ ገብረመድኅን «ነጋድራስ ተሰማ የአማርኛን ውበትና ውስጠ ምስጢር በተሰጥኦ የተካኑ፣ የቋንቋውን ብልት ተንትነው የበለቱ፣ ሰዋሰውስ ሸዋ ሰው የሚያሰኙ ነበሩ» በማለት አድናቆታቸውን ገልጸውላቸዋል። የበርካታ ሙያዎች ባለቤት የነበሩት ነጋድራስ ተሰማ እሸቴ አማርኛ፣ ኦሮምኛ፣ አደርኛ፣ ጀርመንኛ፣ ፈረንሳይኛ፣ ጣሊያንኛና አረብኛ ቋንቋዎችን ይናገሩ ነበር።

የአየር ኃይል አብራሪ የነበረው ልጃቸው መቶ አለቃ ኤልያስ ተሰማ በአውሮፕላን አደጋ መሞቱን ሰምተው ደንግጠው ሲታከሙ ቆዩ። በአንጎላቸው ውስጥ ደም በመፍሰሱና የልሳን ማዕከላቸው በመጎዳቱ የመናገር ችሎታቸው ቀንሶ ለአምስት ዓመታት በሕክምና ላይ ከቆዩ በኋላ ጥቅምት 3 ቀን 1957 ዓ.ም ከዚህ ዓለም በሞት ተለዩ።

# ስፖርት



## በክብረወሰኖች የደመቀው የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ሻምፒዮና

**ቦጋለ አበበ**

የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ሻምፒዮና ለ51ኛ ጊዜ በሐዋሳ ከተማ ከትናንት በስቲያ ተጀምሯል። የሻምፒዮናው ጅማሬም በሜዳ ተግባራትና ረጅም ርቀት ውድድሮች ክብረወሰን ደምቋል። የሻምፒዮናው የመጀመሪያ ቀን ውሎ በበርካታ ውድድሮች የፍጻሜና የማጣሪያ ፉክክር የታጀበ ሲሆን ሁለት የሜዳ ተግባራትና አንድ የረጅም ርቀት ውድድሮች የኢትዮጵያ ክብረወሰን የተሰበረባቸው ሆነዋል።

የሴቶች አሎሎ ውርወራ ውድድር አዲስ ክብረወሰን የተሰበረበት የመጀመሪያው ፉክክር ነው። ከሶስት ዓመት በፊት በ2011 ሻምፒዮና አዲስ አበባ ላይ በመከላከያዋ አትሌት ዙርጋ ኡስማን 13.55 ሜትር ሆኖ የተመዘገበው የኢትዮጵያ ሴቶች አሎሎ ውርወራ ክብረወሰን ዘንድሮ 13.56 ሜትር ሆኖ ተሻሽሏል። ክብረወሰኑን ያሻሻለችውም የቀድሞዋ ባለክብረወሰን ራሷ ዙርጋ ኡስማን ናት። የመከላከያዋ አትሌት በክብረወሰኑ ታጅባ ያሸነፈችውን ውድድር የኢትዮጵያ ንግድ ባንኳ አትሌት መርሃዊት ጸጋዬ 12.24 ሜትር በመወርወር ሁለተኛ ሆና አጠናቃለች። ሌላኛዋ የመከላከያ አትሌት አመለ ይበልጣል ደግሞ 12.16 ሜትር በመወርወር የነሐስ ሜዳሊያ አሸናፊ በመሆን አጠናቃለች።

የውድድሩን መክፈቻ በክብረወሰን ያደመቀው ሌላኛው ውድድር የወንዶች ስሉስ ዝላይ ነው። የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አትሌት የሆነው ክችማን ኡጅሉም የውድድሩ አዲሱ የኢትዮጵያ ባለክብረወሰን ነው። ክችማን 16.03 በመዝለል አዲስ ክብረወሰን ሲያስመዘግብ፣ የኢትዮጵያ ንግድ ባንኩ አትሌት ዶል ማች 15.79 ሜትር በመዝለል የብር ሜዳሊያ ተሸላሚ ሆኗል። 15.54 ሜትር የዘለለው የኦሮሚያ ክልል አትሌት በቀለ ጅሎ ሶስተኛ ደረጃን ይዞ ውድድሩን ፈጽሟል። የቀድሞው የኢትዮጵያ የወንዶች ስሉስ ዝላይ ክብረወሰን በ2011 አዲስ አበባ ላይ እንደተመዘገበ የሚታወስ ሲሆን የመከላከያው አትሌት አዲር ጉር 15.88 ሜትር በመዝለል ነበር ያስመዘገበው።



በ51ኛው የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ሻምፒዮና በተለያዩ ውድድሮች ክብረወሰኖች እየተሻሻሉ ይገኛሉ፣

በሻምፒዮናው ሳይጠበቅ የተሻሻለው ትልቅ ክብረወሰን የወንዶች አስር ሺ ሜትር ነው። ይህን ክብረወሰን ትልቅ ያደረገውም ባለፉት አስራ ስምንት ዓመታት ሳይሰበር መቆየቱ ነው። በ1996 አም አዲስ አበባ ላይ ጀግናው አትሌት ስለሺ ስህን ለፌደራል ማረሚያ ቤት እየሮጠ ያስመዘገበው 28:16:23 ሰዓት ላለፉት ሁለት አስርት ዓመታት ገደማ ሳይሰበር ቆይቷል። ዘንድሮ ግን ይህን ክብረወሰን የሚደፍር አትሌት ከደቡብ ፖሊስ ክለብ ተገኝቷል። አትሌት ታደሰ ወርቁ የርቀቱ የዘንድሮው የኢትዮጵያ ሻምፒዮን ብቻም ሳይሆን ያስመዘገበው 28:11:92 ሰአት አዲስ ክብረወሰን መሆን ችሏል። ታደሰን ተከትሎ በቶኪዮ 2020 ኦሊምፒክ ኢትዮጵያን ወክሎ በአምስት ሺ ሜትር ብቸኛ የፍጻሜ ተፋላሚ የነበረው አትሌት ሚልኬሳ መንገሻ 28:27:26 በሆነ ሰዓት ኦሮሚያ ክልልን የብር ሜዳሊያ ባለቤት አድርጓል። ገመቹ ዲዳ ከኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ በ28:29:93 በማጠናቀቅ የነሐስ ሜዳሊያው አሸናፊ ሆኗል።

በተመሳሳይ አስር ሺ ሜትር ሴቶች ትናንት አዲስ የኢትዮጵያ ክብረወሰን መመዝገቡ የዘንድሮው ሻምፒዮና በክብረወሰን እንዲደምቅ ካደረጉ ምክንያቶች ዋነኛው ነው። ከቅርብ ዓመታት ወዲህ በተለይም በርካታ የአገር ውስጥ ውድድሮችን በማሸነፍ አስደናቂ ብቃት እያሳየች የምትገኘው የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አትሌት ግርማዊት ገብረእግዚያብሔር 31:21:48 በሆነ ሰዓት ስታሸንፍ የርቀቱ የኢትዮጵያ ክብረወሰን ባለቤትም ሆናለች። ቀደም ሲል የርቀቱ ክብረወሰን በትራንስ ኢትዮጵያዋ አትሌት ለተሰንበት ግደይ በ2011 አም አዲስ አበባ ላይ የተመዘገበ ሲሆን ሰአቱም 32:10:13 ነበር። ባለክብረወሰኗ ግርማዊት ኮከብ በሆነችበት ውድድር የመከላከያዋ አትሌት ሃዊ ፈይሳ 31:21:48 በማጠናቀቅ የብር ባለቤት ስትሆን አበራሽ ማናስቦ ከኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ በ32:10:74 ሶስተኛ ሆና አጠናቃለች።

የሻምፒዮናው ሁለተኛ ቀን በሌሎች ክብረወሰኖች ደምቆ ሲውልም የሴቶች ዲስከስ ውርወራ አዲስ ክብረወሰን ተመዝግቦበታል። የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ አትሌት የሆነችው መርሃዊት ጸሐዬ 45.40 ሜትር በመወርወር የአዲሱ ክብረወሰን ባለቤት ሆናለች። ከተመሳሳይ ክለብ አለሚቱ ተክለስላሴ 41.60 ሜትር ወርውራ የብር ሜዳሊያ አሸናፊ ስትሆን፣ዙርጋ ኡስማን 40.14 ሜትር በመወርወር ለመከላከያ ነሐስ አስመዝግባለች። የውድድሩ የቀድሞ ክብረወሰን በ2007 አም በመከላከያዋ አትሌት አልማዝ ንጉስ በ42.83 ሜትር አዲስ አበባ ላይ እንደተመዘገበ ይታወሳል።

የሴቶች መቶ ሜትር ውድድርም አዲስ ክብረወሰን ያገኘ ርቀት ነው። የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ አትሌት የአብስራ ጃርሶ ከአስራ ስድስት ዓመት በፊት በሌላኛዋ የንግድ ባንክ አትሌት አታክልቲ ውብሸት በ1998 አዲስ አበባ ተይዞ የቆየውን 11.55 ሰከንድ አሻሽላዋለች። የአብስራ አዲሱን ክብረወሰን በዘጠኝ ማይክሮ ሰከንዶች በማሻሻል 11.46 ሰከንድ የወርቅ ሜዳሊያ ስታጠልቅ ባይቱላ አላዮ በ11.89 ሰከንድ ከደቡብ ፖሊስ የብር ሜዳሊያ አሸንፋለች። ራሄል ተስፋዬ ከመከላከያ በ11.90 ሰከንድ የነሐስ ሜዳሊያው ባለቤት ነች።


## የጨረታ ማስታወቂያ

### ግጨ.ቁ ESLSEKBPT/002/2014

የኢትዮጵያ ባህር ትራንስፖርትና ሎጅስቲክስ አገልግሎት ድርጅት ቃሊቲ ወደብና ተርሚናል ቅ/ጽ/ቤቱ ከዚህ በታች የቀረቡትን የተለያዩ የወደብ ማሽን የመለዋወጫ እቃዎች እና ጎማዎች ማቅረብ ከሚችሉ ድርጅቶች አወዳድሮ መግዛት ይፈልጋል።

**በመሆኑም በጨረታው ለመሳተፍ የሚፈልጉ በዘርፉ የተሰማሩ ድርጅቶች ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ሁኔታዎች በማሟላት መጫረት የሚችሉ መሆኑን ይገልጻል።**

1. በዘርፉ የተሰማሩ ድርጅቶች የታደሰ የንግድ ፈቃድ ፤ የተ.እ.ታ ሰርተፊኬት ፤ የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር እና የዘመኑን ግብር የከፈሉ ለመሆናቸው የሚያሳይ መረጃ ማቅረብ አለባቸው፤
2. ተጫራቾች የጨረታውን ሰነድ ዋና እና ኮፒ በሰም በታሸገ ኢንቨሎፕ በአንድ ፖስታ ማቅረብ ይኖርባቸዋል ፤
3. የጨረታ ማስከበሪያ ዋስትና የጠቅላላ ዋጋውን 2% ያላነሰ በሲ.ፒ.ኦ ወይም በባንክ ጋራንቲ ‹‹የኢትዮጵያ ባህር ትራንስፖርትና ሎጅስቲክስ አገልግሎት ድርጅት ቃሊቲ ቅ/ጽ/ቤት (Ethiopian shipping and logistics service enterprise kality branch office) በሚል ስም በማሰራትና በማቅረብ መጫረት ይችላሉ ፤
4. የጨረታ ሰነዱን የማይመለስ ብር 200.00 (ሁለት መቶ ብር) በመክፈል ቃሊቲ ወደብና ተርሚናል ቅ/ጽ/ቤት ቅጥር ግቢ በሚገኘው የምድር ሚዛን መስተናገጃ ገንዘብ መቀበያ ቢሮ መውሰድ ይቻላል ፤
5. ጨረታው ‹‹ የኢትዮጵያ ባህር ትራንስፖርትና ሎጅስቲክስ አገልግሎት ድርጅት ቃሊቲ ወደብና ተርሚናል ቅ/ጽ/ቤት ግዥና ንብረት አስተዳደር ክፍል ጨረታው ከወጣበት ቀን ጀምሮ 16ኛ ቀን ከረፋዱ በ4፡00 ሰዓት ተዘግቶ በዚሁ ዕለት በ4፡30 ሰዓት ተጫራቾች ወይም ሕጋዊ ወኪሎቻቸው ባሉበት ፖስታው ይከፈታል ፤
6. ከጨረታው መክፈቻው ቀንና ሰዓት በኋላ ዘግይቶ የሚመጣ የጨረታ ሰነድ ተቀባይነት የለውም፤
7. ድርጅቱ የተሻለ አማራጭ ካገኘ በከፊልም ሆነ በሙሉ ጨረታውን የመሰረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው።

**ስልክ ቁጥር 011-888-92-22**

**የኢትዮጵያ ባህር ትራንስፖርትና ሎጅስቲክስ አገልግሎት ድርጅት**
**ቃሊቲ ወደብና ተርሚናል ቅ/ጽ/ቤት**

## የጨረታ ማስታወቂያ

ገንደቆሬ ጤና ጣቢያ አገልግሎት የሚውል CBC ማሽን በጨረታ አወዳድሮ (LOT) ለመግዛት ይፈልጋል። በመሆኑም በጨረታው ለመሳተፍ የምትፈልጉ የጨረታው ሰነድ በማይመለስ ብር 100.00 (አንድ መቶ ብር) ከገንደቆሬ ጤና ጣቢያ ግ/ፋ/አስ/ቢሮ መግዛት ይችላሉ።

- የግዥ መለያ ቁጥር ገ/ቆ/ጤ/ጣ መደበኛ 01/2013
- ተጫራቾች ከሚያቀርቡት እቃ ጋር የተዛመደ በዘመኑ የታደሰ ህጋዊ የንግድ ፍቃድ ያለው
- የምዝገባ የምስክር ወረቀት
- ቲን ነምበር (TIN Number) ያለው
- የተጨማሪ እሴት ታክስ የምዝገባ የምስክር ወረቀት ግብር የተከፈለበት የቫት ምስክር ወረቀት ማቅረብ የሚችሉ መሆን አለባቸው።
- ተወዳዳሪ ላቀረበው ጠቅላላ ዋጋ 3000.00 (ሶስት ሺህ ብር) የጨረታ ማስከበሪያ (CPO) ወይም በጥሬ ገንዘብ ማስያዝ ይኖርበታል።
- ለተጨማሪ የጨረታ ማስከበሪያ የተያዘው ገንዘብ ለተሸነፈው ድርጅት ወዲያውኑ ይመለሳል።
- ያሸነፈው ተጫራች ድርጅት የውል ማስከበሪያ ከአጠቃላይ 10% ማቅረብ አለበት።
- ተጫራቾች ይህ ማስታወቂያ በአዲስ ዘመን ከወጣበት ቀን ጀምሮ ለተከታታይ 15 የስራ ቀናት በስራ ሰዓት በገንደቆሬ ጤና ጣቢያ በመገኘት ሰነዱን ለመግዛት ለዚሁ የተዘጋጀው የጨረታ ሳጥን ውስጥ በሰም በታሸገ ኤንቨሎፕ በማሸግ በተዘጋጀው ሳጥን ውስጥ ማስገባት አለባቸው። 16ኛው ቀን የስራ ቀን ካልሆነ በቀጣይ የስራ ቀን ይሆናል።
- የጨረታ ማስታወቂያ በአዲስ ዘመን ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ16ኛ ቀን ከጠዋቱ 3፡00ሰዓት ተዘግቶ በእለቱ ከጠዋቱ 4፡00 ሰዓት ተጫራቾች/ ህጋዊ ወኪላቸው በተገኙበት በገንደቆሬ ጤና ጣቢያ በግገር ፋይናንስ ክፍል ጨረታው ይከፈታል።
- ተጫራቾች የጨረታውን ሰነድ ኦሪጅናል እና ለየብቻው በሰም በታሸገ ኤንቨሎፕ በማሸግ ማቅረብ ይጠበቅባቸዋል
- የተጫራቾች አለመኖር ፖስታው ተሟልቶ እስከተገኘ ከመከፈት አይስተጓጎልም።
- ጤና ጣቢያው የተሻለ መንገድ ካገኘ ጨረታውን በሙሉ ወይም በከፊል ለመሰረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው።

ተጨማሪ ማብራሪያ ካስፈለገ በአካል በመቅረብ ወይም በሞባይል ቁጥር 0911815159 መጠቀም የምትችሉ መሆኑን እንገልፃለን።

**የድሬዳዋ አስተዳደር ጤና ጣቢያ**
**የገንደቆሬ ጤና ጣቢያ**